## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


# የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ
# (በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛ ለማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት


በ

ዘሪሁን አሰፋ



አዲስ አበባ

ጥር 2016 ዓ.ም

# የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ / በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት/

በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛ ለማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ  ጥናት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሣይንስና ሥነ-ሰብ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና  ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

በ

ዘሪሁን አሰፋ

አማካሪ፡ ግርማ ገብሬ(ዶ.ር)



አዲስ አበባ

ጥር/2016 ዓ.ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የማህበራዊ ሣይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ (በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በተመረጡ አምስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በዘሪሁን አሰፋ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

**በ**

**ዘሪሁን አሰፋ**

## የፈታኝ ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ---------------------------------- ፊርማ-----------------------ቀን--------------------

የውስጥ ፈታኝ------------------------- ፊርማ----------------------ቀን--------------------

የዉጭ ፈታኝ-------------------------- ፊርማ-----------------------ቀን-------------------

## ማረጋገጫ

በአማርኛ ቋንቋ ‹‹የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ በዘጠነኛ ክፍል እና በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር በተግባራዊ ሥነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡

ስም-----------------------------------------

ፊርማ--------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን-------------------------

# ምሥጋና

ይህ ጥናት አሁን ያለውን መልክ እንዲይዝ ውድ ጊዜያቸውን በመስዋት ያለመሰልቸት ጠቃሚ ምክራቸውን ለለገሱኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ግርማ ገብሬ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት በማደርግበት ወቅት ሙሉ ትብብራቸው ላልተለዩኝ ለአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች፣እንዲሁም ጥናቱን በማካሂድበት ወቅት አስፈላጊውን የቁሳቁስ መሳሪያዎችና የተለያዩ ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ መጻህፍትን በማዋስ የተባበሩኝን እንዲሁም ጥናቱን ጀምሬ እስከምጨርስ ድረስ በምልከታ ወቅትና በክፍል ውስጥ ትግበራ ጊዜ ያለመሰላቸትን ያለድካም ለተባበሩኝ ለሙያ ባላደረቦቼ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ይህንን ትምህርት እንድማር ላበረታቱኝ ለቤተሰቦቼ፣ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ ዝናቧ በስስት ለማያቸው ልጆቼ (ቤቢና ዱዱ) እና ጓደኞቼ በሙሉ ትምህርቴን እስካጠናቅቅ ድረስ ላደረጋችሁልኝ ወደር የሌለድጋፍ ፈጣሪ ብድሩን
ይክፈላችሁ፤ ያለ እናንተ ስኬቴ አይታሰብምና፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል እና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ምን እንደሚመስል መገምገም ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በዋናነት ምልከታ ሲሆን በተጨማሪ የጽሑፍ መጠይቆችን በመምህራንና በተማሪዎች በማስሞላት መምህራን ጽህፈት ስለሚያስተምሩበት የማስተማሪያ ዘዴ የሚጠቁሙ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ከተማሪዎች በተመረጡ ናሙናዎችና በተጠቀሱት የክፍል ደረጃ በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቆቹ እንዲሞሉ ተደርገዋል። በተደረገው ምልከታና ከመጠይቁ በተገኘው ምላሽ መምህራን ፅህፈትን የሚያስተምሩት በመፃፍ ሳይሆን በአብዛኛው ስነ-ልሳናዊ ዕውቀትን ለማስጨበጥ ትኩረት በመስጠት ነው። መምህራን ተማሪዎችን በተግባራዊ ሂደት እንዲማሩ ከማመቻቸት ይልቅ በገለፃ የሚያስተምሩ መሆናቸውን መረጃዎች አመልክተዋል። በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚደረገው የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ የፅህፈት ተግባቦትን የሚያዳብር እና ተማሪዎችን የሚያሳትፍ አይደለም። ተማሪዎች የተለያዩ ለጽሕፈት ክሂል መዳበር የሚረዱ ሂደቶችን አውቀው እየተገበሩ እንዲሻሻሉ የሚደረግ ጥረት ደካማ ነው። ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲማማሩ እና እንዲተራረሙ የሚሠራው ሥራ ውስንነት አለበት። በአብዛኛው መምህራን ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩት ተማሪው በተሰጠው ርዕስ ላይ ጽፎ ባቀረበው ውጤት ላይ ነው። ለችግሩ መኖር በዋናነት የተጠቀሰው መንስዔ መምህራን ስለ ጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ነው። በአጠቃላይ ለችግሮቹ መፍትሔ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚገመተው ከአዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር መምህራን እንዲተዋወቁ ሥልጠና መስጠት ጠቃሚ መሆኑ ተጠቁሟል።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


አጠቃሎ ........ i

ምዕራፍ አንድ ........ 1

1. መግቢያ ........ 1

የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 4

1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 4

1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5

1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 5

1.6 የጥናቱ ውስንነት ........ 5

ምዕራፍ ሁለት ........ 6

ክለሳ ድርሳናት ........ 6

2.1 የጽህፈት ክሂል ጽንሰ ሀሳብ ........ 6

2.1.1 የፅህፈት ትምህርት ማስተማር ዓላማ ........ 6

2.1.2 ጽህፈት እንዴት እናስተምራለን? ........ 7

2.2 የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ........ 10

2.2.1 ሂደት ተኮር የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ (Proces Approach) ........ 11

2.2.1.1 የሂደታዊ ዘዴ የአፃፃፍ ሂደት ደረጃዎች ........ 14

2.2.1.2 በሂደታዊ አቀራረብ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና ........ 15

2.2.1.3 በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የተማሪው ሚና ........ 16

2.2.2 ውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ........ 18

2.2.2.1 ውጤታማ አቀራረብ የፅሀፈት ደረጃዎች ........ 19

2.2.2.2 በውጤታማ አቀራረብ የፅሀፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና ........ 21

2.2.3 የዘውጋዊ የጽሀፈት ትምህርት አቀራረብ ........ 22

2.3 የቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት ........ 26

ምዕራፍ ሶስት ........ 30

3. የጥናቱ አጠናን ዘዴ ........ 30

3.1 የጥናቱ ስልት ........ 30

3.2 የናሙና አመራረጥ ........ 30

3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 30

3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 31

3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 31

3.2.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 31

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........ 32

3.3.1 ምልከታ ........ 32

3.3.2 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 32

3.4 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ........ 33

3.5 የመረጃዎች አተናተን ዘዴ ........ 33

ምዕራፍ አራት ........ 34

የመረጃ ትንተና ........ 34

4.1 መምህራን የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት ........ 34

4.1.1 የተተኳሪ መምህራንና የተማሪዎች አጠቃላይ ዳራ ........ 34

4.1.2 የፅሀፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ በአምስቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ........ 36

4.1.3 የፅሀፈት ትምህርት አቀራረብን ለመለየት የተደረገ ........ 36

4.1.4 በጽሀፈት ትምህርት አቀራረብ የመምህራንን ሚና ........ 37

4.1.5 በጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ሚና ...... 39

4.1.6 ከመምህራን መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...... 40

4.1.6.1 ፅህፈትን በማስተማር የመምህራን የትኩረት አቅጣጫ ...... 40

4.1.7 ጽህፈትን በማስተማር ረገድ የመምህሩ ኃላፊነት ...... 43

4.1.8 የመምህራን የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች ...... 45

4.1.9 ስለ ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህራን ስልጠናን ...... 47

4.2 ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ ምን ...... 48

4.2.1 የተማሪዎችን ተግባር ስለማሳወቅ ...... 48

4.2.2 ፅህፈትን በሂደት የማስተማር ዘዴና ጠቀሜታው ...... 50

4.3 የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ ምን ይመስላል? 53

4.3.1 የመምህራን የማስተማር ብቃት የሚያመለክቱ መረጃዎች ...... 53

4.3.2 የመምህሩን ኃላፊነት የሚያመለክቱ መረጃዎች ...... 54

ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና አስተያየት ...... 57

5.1 ማጠቃለያ ...... 57

5.2 አስተያየት ...... 59

ዋቢ ጽሁፎች ...... 63

አባሪ ...... 67

## የሠንጠረዥ ማውጫ

**ሠንጠረዥ አንድ** ፡- የተተኳሪ መምህራን አጠቃላይ ዳራ-------------------------------------36

**ሠንጠረዥ ሁለት** ፡- ተተኳሪ ተማሪዎች ከፆታ አንፃር----------------------------------------37

**ሠንጠረዥ ሦስት** ፡- ፅህፈትን በማስተማር ረገድ የመምህራን የትኩረት አቅጣጫ በተመለከተ ከመምህራን የተገኘ መረጃ----------------------------------43

**ሠንጠረዥ አራት** ፡- ጽህፈትን ለማስተማር የመምህሩ ኃላፊነት-------------------------------45

**ሠንጠረዥ አምስት**፡- ከመምህራን የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች አኳያ ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች ትንተና------------------------------------------------------------47

**ሠንጠረዥ ስድስት** ፡- ጽህፈትን ለማስተማር መከናወን ያለባቸው ተግባራትን ከመተግበር አኳያ ከመምህራን የተገኘ መረጃ----------------------48

**ሠንጠረዥ ሰባት** ፡- በጽህፈት ትምህርት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ተግባር ከማሳወቅ አኳያ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ-----------------------------50

**ሠንጠረዥ ስምንት** ፡- ከጽህፈት የማስተማሪያ ዘዴዎች አኳያ ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች-------------------------------------------------------------53

**ሠንጠረዥ ዘጠኝ** ፡- የመምህራኑ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የጽሁፍ ክሂል ስለማሻሻሉ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች-------------------54

**ሠንጠረዥ አሥር** ፡- ጽህፈትን በማስተማር ሂደት የመምህራንን የማስተማር ብቃት የሚያመላክቱ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች--------55

**ሠንጠረዥ አሥራ አንድ** ፡- ጽህፈትን በማስተማር ሂደት የመምህሩን ኃላፊነት በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ--------------------------------------------57

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን የማስተማር ተቀዳሚ ዓላማ ተማሪዎች የማዳመጥ፣የመናገር፣የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸው እንዲዳብር ማድረግ ነው፡፡ በቋንቋ አማካኝነት የሚተላለፈው መልዕክት እና የቀረበውን ጽሑፍ አንብቦ የመረዳት፣ሀሳብን ያለፍርሃት የመግለጽ፣በተጨማሪም ደረጃቸውን የሚመጥን የአጻጻፍ ስርዓት ተከትሎ ሀሳብን በጽሑፍ የመወከል ችሎታ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የሚዳብሩ ተግባራት ናቸው (በለጠ ፣2010)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቋንቋን መማር ማስተማር ሂደት በሚመለከት ከተደረጉ ንድፈ ሀሳቦች መካከል ማህበረ ግንባታዊያን፣አእምሯዊያን እና ማህበረ ባህላዊያን ይገኛሉ (አማረ ተሾመ፣2010)፡
፡

ፅህፈት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሆኖ አፍላቂ ክሂል (productive skills) በመባል ይታወቃል፡፡ የፅህፈት ክሂል እንደማዳመጥና መናገር በልምድ የሚገኝ ሳይሆን በመደበኛ ትምህርት ዐውድ የሚማሩት ነው:: ስለሆነም ይህን የክሂል ዘርፍ አፊ-ፊቶችም ሆኑ ኢ-አፊ ፊቶች በትምህርት አማካይነት ያገኙታል (Byren 1991 እና Norrish 1983):: የፅህፈት ትምህርት ከክሂል ትምህርቶች አንዱ እንደመሆኑ መጠን በሀገራችን የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንዱ ግብ ይህንን ክሂል ማሳደግ መሆኑን በሀገሪቱ የተቀረፁ የትምህርት መርሆዎች ሁሉ ያተኮሩበት ጉዳይ ነው፡፡ Richards (1990) በበኩላቸው ‹‹መምህራን ተማሪዎች ትክክለኛ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የተዋጣለት የአፃፃፍ ችሎታ ለመከተል እንዲችሉ ነገሮችን ማደራጀት እና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው›› ይላሉ፡፡

ተማሪዎች በክሂሉ በቂ እውቀት አግኝተው ፅህፈትን በቅርጹና በይዘቱ የተሟላ ሊያደርግ የሚችለውን የአፃፃፍ ዘዴ አውቀው መፃፍ እንዲችሉ መምህራን የተለያዩ የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢጠቀሙ ያቀዱት ወይም ያለሙት ውጤት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ፡
፡የክሂሉን የማስተማር ዘዴ በተመለከተ አስቴር(1998) መምህራን ፅህፈትን በማስተማር

ዓላማ ተማሪዎችን በማቀድ፣በመከለስ፣ በማርቀቅና በማረም ሂደት እንዲያልፉ ክትትል እንደማያደርጉና የሚሰጧቸውም ድጋፍ እንደሌለ ገልፃለች፡፡ አያይዛም በፅህፈት ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች በመወያየት፣ ማስታወሻ በመያዝ፣ ረቂቅ በመፃፍ፣ የብጤ እርማት በማካሄድ፣ በመከለስ፣ በማረምና መልሶ በመፃፍ ተግባራት በንቃት ሲሳተፉ በክፍል ውስጥም የፅሁፍ ተግባራትን በክንውን ሲለማመዱና ሲማሩ እንዳልታዩ ገልፃለች፡፡

ከላይ ለተዘረዘሩት ችግሮች መንስኤ ለየክፍል ደረጃዎቹ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች ውስጥ ጽህፈት የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶች አለመኖራቸው ሳይሆን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረጉ ላይ ነው፡፡ ይኸውም በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ በአንድ ክፍል ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ቋንቋውን ለመማር የተመደበው ጊዜ ማነስ፣ በመምህሩ ላይ የሥራ ጫና መክበድ ጽህፈትን ለማስተማር ፍላጎት አለመኖር፣ አለማፃፍ፣ የተፃፈውንም መልሶ አለማየት (አለማየሁ ክፍሌ1986፣ እና ተስፋዬ 1986) ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም ከእነዚህ ሁሉ ችግሮች በመነሳት በመምህራኑ የጽህፈትን ክሂል የማስተማሪያ ዘዴና በተማሪዎቹ ጽህፈት የመፃፍ ዘዴ መካከል ክፍተት ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

የማስተማር ሥነ-ዘዴ የትምህርቱን ይዘትና ተማሪውን የሚያገናኝ ድልድይ በመሆኑ አመራረጡም ሆነ ትግበራው በትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታትና አለመምታት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ይህም ትግበራውን መገምገምን ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ የማጠንከሩንና ደካማ ጎኖች ካሉ የማሻሻያ አስተያየት የመሻቱን አስፈላጊነት ይጠቁማል፡፡ ከዚህ አኳያ ጽህፈትን የማስተማር ሥነ-ዘዴ ትግበራ ወይም የመማር ማስተማር ክንውን ተፈትሾ ድክመትና ጥንካሬው አለመታወቁና በተማሪዎች ችሎታ ማነስ ላይ የፈጠረው ጫና መኖር አለመኖሩ አለመረጋገጡ ይህንን ጥናት ለማካሄድ አስፈላጊ ያደርገዋል፡ ፡በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በመገኘትና ጽህፈትን ለማስተማር የተመረጠውን ሥነ-ዘዴ፣ የሥነ-ዘዴውን ትግበራ በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩንና የተማሪውን ሚና መገምገምና መግለጽ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ለመጻፍ ክሂል መዳበር በእንቅፋትነት ከሚጠቀሱት መካከል አንዱ ተገቢ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ አለመምረጥ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ችግር ለማቃለልና ለመቅረፍ ደግሞ የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችን መገምገም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ስለሆነም

የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችን መርጦ መጠቀም የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ችሎታን ማዳበር የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን በጥናት አረጋግጦ ለማስተማሪያ ስነ ዘዴ ዝግጅት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ጠቃሚ ይሆናል።

ይህ ጥናት እንደ መርህ የሚከተለው የማህበራዊ ግንባታ ንድፈሀሳብ ሲሆን፣ተማሪዎች በየቀኑ ትምህርታቸው የነቃ ተሳትፎ በማድረግ በመጻፍ ክሂል ትምህርታቸው ወቅት ለተጨባጭ ለውጥ እንዲተጉ የሚያግዝ ንድፈ ሀሳብ ነው። ስለዚህ የመጻፍ ክሂል እንዲዳብርና ተማሪዎች ጥሩ ተግባቦትና የሃሳብ ፍሰት ያለው ጽሑፍ እንዲጽፉ ለማስቻል ጽሑፋዊ ምላሾች እገዛ ያደርጋሉ። ስለሆነም ጽሑፋዊ ምላሽየመጻፍ ክሂል እንዲጎለብት የሚያስችሉ፣በተለያዩ የጽህፈት ተግባራት ወቅት ሊተገበሩ የሚችሉ፣የጸሐፊውን ስህተት ለመቀነስ የሚያግዙ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ናቸው። በመሆኑም በጽሑፍ ምክንያት የሚሰጣቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መምህራን ካነበቡ በኃላ በጽሑፍ የሰፈረውን ሀሳብ በትክክል መጻፍ አለመጻፉን በመረጃ አስደግፈው የሚሰጡት የጽሑፍ ምላሽ ነው (Ramies 1990)::

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ይህን ጥናት ለማካሄድ የተነሳበት ዋናው ምክንያት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን በሚማሩበት ወቅት በቅርበት እንዳስተዋለው መምህሩ በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምር የሚጠቀመው የማስተማሪያ ስነ ዘዴ የተማሪውን የመጻፍ ክሂል እምብዛም ባለማዳበሩ የተነሳ ምናልባት የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ የተሻለውን መርጠው ቢጠቀሙ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታን ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው።

በመሆኑም ከላይ የቀረቡት ሀሳቦች አጥኚው ከነበረው ልምድና በየአጋጠሚው ስለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከሚሰማው ጋር ተዳምሮ “በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ በሚል ርዕስ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስቷል።

በተጨማሪም አጥኚው በሚሰራበት አካባቢ በዚህ ችግር ላይ የተሰራ ጥናትና ምርምር ባለመኖሩ በዚህ ርዕስ ጥናት ለማድረግ ተነሳስቷል፡፡ ይኸሁም ከዚህ በታች ጥናቱ ምላሽ ለመስጠት ያነሳቸው መሪ ጥያቄዎችም እንደሚከተለው ተጨምቀው ቀርበዋል፡፡ እነርሱም፡

1. ጽህፈትን ለማስተማር መምህራን የሚጠቀሙት ሥነ-ዘዴ ምንድን ነው?
2. ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ ምን ይመስላል?
3. የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

ይህ ጥናት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚገኙት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር የሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች የሚከወኑበትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች መገምገም ነው፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ዋና ዓላማ በተመረጡት የክፍል ደረጃዎች ናሙናነት የጽህፈት ክሂል ለማዳበር መምህራኑ የሚከተሏቸውን ሥነ ዘዴዎች ትግበራ መገምገም ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ንዑስ ዓላማዎችም አሉት፡-

1. መምህራን ጽህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙትን የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ መለየት፣
2. ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ መመርመር፣
3. የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ መገምገም ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በባለሙያዎችና በሌሎች ምሁራን የተጻፉ ጽሁፎችን በመፈተሽ በአምስት ትምህርት ቤት ተመስርቶ በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ በመታገዝ የሚከናወን ጥናት በመሆኑ ከዚህ በታች በዝርዝር የቀረቡና ሌሎች ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

**ሀ. ለሥልጠና አመቻች ባለሙያዎች፡-**ወርክሾፖችን፣የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠና መርሀ-ግብሮችን በማዘጋጀት በዘርፉ የሚታዩ ግኝቶችን፣አቀራረቦችንና ሥነ-ዘዴዎችን ለነባር መምህራን እንዲያስተዋውቁ በማሳሰብ እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ለ. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-** መምህራን የተማሪዎቻቸውን የጽህፈት አፃፃፍ ዘዴ በማወቅ የማስተማር ዘዴያቸውን ከተማሪዎች ችሎታና ፍላጎት ጋር እንዲያጣጥሙ አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

**ሐ. ለተመራማሪዎች፡-** በዋናነት በተመሳሳይ ርዕስ ለሚካሄዱ ጥናቶች የመነሻ ሀሳብና በምርምር ሂደቱም የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት ትኩረት አድርጐ የተነሳው በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከሚገኙ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል በተመረጡ አምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ ላይ የተገደበ እና የተወሰነ መሆኑ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

የዚህ ጥናት ዓላማ በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በተመረጡ አምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍሎች ተማሪዎች ላይ የሚተገበረው የመፃፍ ክሂል ብቻ ያተኩራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአራቱ መሰረታዊ ክሂሎች ውስጥ የመምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ግምገማ ላይ ብቻ በማተኮሩ ሌሎች ክህሎችን ግን ጥናቱ አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

ከቋንቋ ትምህርት ዘርፎች አንዱ የጽህፈት ትምህርት ነው፡፡ የጽህፈት ትምህርት ከቋንቋ ክሂሎች ውስብስብና ከበድ ያለው ሲሆን ከተማሪው ብዙ ተዛማጅ ግንዛቤዎችን የሚጠይቅ ነው፡፡ ጽህፈት ሃሳብን በቋንቋ የመወከል ሂደት ነው፡፡ ሂደቱም አካልንና አእምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህሪያቱን፣(ለምሳሌ ይዘትን፣ የአፃፃፍ ስልትን፣ የፅሁፍ መዋቅርን፣ የቃላት ምርጫን፣ የሀሳብ አንድነትን፣ ግጥምጥምነትንና ተከታታይነትን) ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወንና ከማሰብ ጋር የተቆራኘ ውስብስብ የአዕምሮ ሥራ ነው (Nunan 1989)፡፡ በዚህ ክፍል የተዛማጅ ጽሁፎች በስፋት ይቃኛሉ፡፡

## 2.1 የጽህፈት ክሂል ጽንሰ ሀሳብ

ጽህፈት በአንድ የተወሰነ ልማዳዊ ሥርዓት ምልክቶች ተቀናጅተው ቃልን፣ ቃላት ደግሞ ዐረፍተ ነገሮችን፣ አረፍተ ነገሮች ደግሞ አንቀጾችን አንቀፆች በተራቸው ተቀናጅተው አንድ ወጥ ቅርጽ ያለው ውህድ አሀድ (Text) የሚያስገኝና ከተራ ፊደላት ቅንጅት ላቅ ያለ እንደሆነ (Byrne 1991) ይናገራሉ፡፡ (Murray 1982) ስለጽህፈት ያላቸው አመለካከት ጽህፈት የህይወትን ፍች ለማሣወቅ ግለሰቡ የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ጽህፈት ደራሲ በህይወት ገጠመኙ ውስጥ ፍችን አግኝቶ ለሌላው ለማስተላለፍ ቋንቋን የሚጠቀምበት ስልት ነው፡፡ ወይም ጽህፈት የምንለው በቋንቋ አማካኝነት ፍች ለማግኘት የሚከናወነው ሂደትና ሂደቱም የሚያስገኘው ውጤት ነው፡፡ በአጠቃላይ ጽህፈት የተለያዩ ቃላትን፣ ሀረጋትን፣ አረፍተ ነገሮችን በማዛነቅ ወይም በማገጣጠም አንድ ወጥ አካልን ለመመስረት የሚደረግ የሃሳብ ቅንጅት ነው፡፡ በተጨማሪም የድርሰት ትምህርት ዓላማ ሊበጅለት ሊወሰንለትና ክንውኑ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል ይላሉ (Murray 1982)፡፡

### 2.1.1 የፅህፈት ትምህርት ማስተማር ዓላማ

ጽህፈትን መማር ዓላማው ሰዎችን ከተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ጊዜዎች ማገናኘትና ማስተባበር እንዲሁም ዓለምን መረዳትና የተረዱትን አቀናጅቶ መግለጽ እንደሆነ (Coline.et.al 1965) ይገልፃሉ፡፡ Brandly (1994) በበኩላቸው የጽህፈት ትምህርት ዓላማ

ደራሲ አስተሳሰብን በማብራራትና በመደገፍ አእምሮን ማጎልበት እንዲሁም የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎችንና መረጃዎችን በማጠራቀም ህብረተሰብን ማገልገል እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡በሌላ በኩል የጽህፈት ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ዕውቀትን መዝግበው እንዲይዙ መርዳት እንደሆነ (Byrne 1991) ያስረዳሉ፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ የጽህፈት ትምህርት ሲሰጥ ከተማሪዎች አንጻር ሦስት መሠረታዊ ዓላማዎች ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ( Kroll1998)ይገልጻሉ

እነዚህን መሰረታዊ ነገሮች ሲያብራራ ተማሪዎቹ ስለሚጽፏቸው ነገሮች ማለትም ስለሚያ መነጫቸው ሀሳቦች፣ ስለሚከተሏቸው ሂደቶች ወይም ቅድም ተከተሎች እና ስለሚጽፏቸው ማህበረ ባህል ሁኔታ መረዳት ይገባቸዋል ብለዋል፡፡ በሂደታዊ የድርሰት አጻጻፍ ተማሪዎች በግልና በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለአሰራር እንዲያመች የማመሳከሪያ ዝርዝርና የማረሚያ ቅጽ ለተማሪው ሊሰጥ ይችላል፡፡ የመምህሩ ተግባር ማስተባበርና በሚያስቸግራቸው ነገር መርዳት በመጨረሻም የተጠናቀቀውን ሥራ አይቶ መልስ መስጠት ነው፡፡

### 2.1.2 ጽህፈት እንዴት እናስተምራለን?

በዚህ ጥናት ውስጥ ድርሰት/ጽህፈት በመፈራረቅ የገቡና አንዱ ማለት ሌላው መሆኑን ማጤን ተገቢ ነው፡፡ MURRAY (1982) ጽህፈትን እንዴት ማስተማር እንደሚገባንና እንዴት እንደሚተገበር የራሳቸውን አስተያየት እንደሚከተለው ይሰጡናል፡፡እንደርሳቸው አመለካከት የድርሰት ትምህርት ከውጤት አኳያ ማስተማር ይጠቅማል፡፡

መሠረታዊ የሆነውን የአፃፃፍ ሂደት ሳናስተምራቸው በጽሁፍ ውጤት ላይ ብቻ በማተኮር ተማ ሪዎቻችንን ስለምናሰለቻቸው ትምህርቱን እንዲጠሉት እናደርጋቸዋለን፤በተጨማሪም እነሱንም በደካማነታቸው ስለምንተቻቸው ስሜቱ እንዳይኖራቸው፤ ጥሩ ጽሁፍም እንዳያመርቱ እንቅፋት እንሆንባቸዋለን፡፡ ስለዚህ ተጽፎ ያለቀለትን ጽሁፎችን ይዘን

ከምናስተምራቸው ተጽፎ ባላለቀ ጽሁፍ ወይም በመጻፍ ሂደት ላይ ባለ ጽሁፍ ተማሪዎቻችንን ልናስተምራቸው ይገባል፡፡

በዚህ መንገድ ተማሪውን ስናስተምረው በተግባር ላይ የሚውለውን ቋንቋ እንጠቀማለን፡፡ ለተማሪዎቻችን የቃላት አመራረጥና የቋንቋ አጠቃቀምን እናጋራቸዋለን ይህንን ሀሳብ

(Harles Duke 1983) ይደግፉታል፡፡ ተማሪው የሚጽፈው የአፃፃፍ ህግ የያዘ የመማሪያ መጽሐፍ ይዞ ሳይሆን የህይወት ገጠመኝን መሰረት አድርጎ ቃላትን በመምረጥና ቋንቋውን በመጠቀም ነው፡፡ ተማሪው ቋንቋውን ተጠቅሞ ሀቅ ለራሱ እንዲገለጥለት በማድረግ የተገለጠለትን ሐቅ ለሌሎች ለማስተላለፍ ይጥራል፡፡በዚህ ሂደት ውስጥ ይነቃቃል፣ይበረታታል፣ከጥረቱ እየተማረ በውጤቱ ይደሰታል፡፡ Murcia (1991) ባጠናቀሩት መጽሐፍ ውስጥ እና (Kroll 1990) የተማሪዎችን ልምምድ በክፍል ውስጥ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በቤት ሥራም በኩል ሊሰጣቸው ይችላል ይላሉ፡፡በዚህ ላይም አክለውም መምህሩ እንደሚተልመው ወይም እንደሚያስተውለው የትምህርትግብ የቤት ሥራውን ለተማሪዎች ይሰጣል፡፡ ለምሣሌ ከአደረጃጀት ከቅርጽ፣ ከየከይዘት፣ከምክንያትና ጤት ከንጽጽር፣ ከቅደም ተከተል ወዘተ አኳያ የቤት ስራውን ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ እንደተፈለገው የትምህርት ግብ ተማሪዎች የራሳቸውን ርዕስ ሊመርጡ ወይም መምህሩ መርጦ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

እንደ ሌሎቹ ባለሙያዎች ፍልስፍና ደግሞ ጽህፈት ማስተማር ተማሪዎች የተገለጠላቸውንና የደረሱበትን ነገር ማስተላለፍ የሚችሉበት መሳሪያ እንደሆነ አድርገው ይገልጻሉ፡፡የሚሰጣቸውም የቤት ስራ ግላዊ ገጠመኞቻቸውን መተንተንና ማንፀባረቅ እንዲችሉ የሚረዳቸው መሆን ይገባዋል ይላሉ፡፡ የዚሁ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ባለሙያዎች እንደሚሉት ከግል ገጠመኞች ተነስቶ ክሂሉን ያዳበረ ተማሪ ይህ ክሂል የተለያዩ አካዳሚያዊ ጽሑፎችን ለመጻፍ የሚያስችለው ይሆናል፡፡ በሌላ አባባል የክሂል ሽግግር (Skill Transfer) ሊያደርግ ይችላል፡፡

የክፍሉም ይሁን የቤት ሥራዎች ከተሰጡ በኂላ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች የሰሩት ሥራ ሁሉ በመምህራቸው እንዲታረምላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱን ነገር መመርመር እንደሚያስፈልግ (Byrne 1991) ያስገነዝቡናል፡፡ እንደ Byrne (1991) አመለካከት ተማሪዎች ያጠናቀቁት የጽህፈት ሥራ በመቀያየር በጥንድ ወይም በቡድን እንዲያርሙ ቢደረግ መልካም ነው፡፡ ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ፅሁፉን በሂሳዊ መንገድ የማንበብ ልምድ ከማዳበራቸውም በላይ የኂላ ኂላ የራሳቸውን ሥራ በዚሁ መልክ የማረም ልምድ ያዳብራሉ፡፡

የጽህፈት እርማት በተመለከተ Murcia (1991) የተቀመጠ ጽሁፍ እንዲሁም (Kroll 1990) እንዴት መሆን እንደሚገባው ዝርዝር መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ እንደርሳቸው አባባል

መምህሩ በዝርዝር ስህተቶች እርማት ላይ የሚያተኩር ከሆነ የጽህፈት ትምህርት ማስተማሩ ቀርቶ የሰዋሰው ትምህርት ማስተማር ይሆንበታል፡፡ በየአፃፃፍ ደረጃው የተለያዩ ስህተቶች ቢፈጠሩም የተማሪ ስህተት ማረሙ ትኩረት ሊያደርግበት የሚገባው በመጨረሻ በሚቀርበው ሥራው ላይ ቢሆን ይመረጣል፡፡

Kroll (1990) Chenowethን (1987) ጠቅሰው እንደሚሉት በየደረጃው የተማሪውን ስህተት መጎርጎር ተስፋ ሊያስቆርጠው ይችላል፡፡ ነገር ግን በማርቀቅ በመከለስና በማቃናት ወቅት ራሱና ጓደኞቹ ከድርሰቱ ዓላማ፣ ከተደራሲው፣ከይዘት፣ከአደረጃጀት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከሥርዓተ ነጥብ አገባብ ወዘተ አኳያ ብዙውን ስህተት ማረም ይችላሉ፡፡

Kroll (1990) ድርሰትን እንዴት ማረም እንደሚገባ ማወቅ ራሱ ውስብስብ ሥራ ነው ይላሉ፡፡ ነገር ግን መምህራን ከሚከተሉት መንገዶች መምረጥ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡ እነርሱም፡-

1. በህዳግ ላይ ለየት ያለ ምልክት በማድረግ የስህተቱን ዓይነት መጠቆም፤
2. በስህተቱ ምትክ ትክክለኛውን ጽፎ ማሳየት፣
3. ስህተት ብቻ መኖሩን ማመልከት፤ ለምሣሌ የቃላት አመራረጥ፣ የዓ/ነገር አወቃቀርና የአንቀጽ ቅደም ተከተል፤
4. ዝርዝር ስህተቶች ላይ ማተኮር፣

መምህሩ ከእነዚህ መንገዶች ሁለቱን ወይም አንዱን እንደዓላማው በመጠቀም ግብረ መልስ መስጠት አለበት፡፡ የመልስ ምገባው ዓላማ ተማሪው በጽሁፍ ክሂሉ ላይ መሻሻል እንዲያደርግ የሚረዳው መሆን እንዳለበት ( Kroll 1990) ያስገነዝባሉ፡፡ እንደርሳቸው አባባል በተማሪው ጽህፈት ላይ የመምህሩ መልሶ ምገባ በተለያዩ ስልቶች መቀየስና ተማሪዎችን ማሰልጠን ይጠበቅበታል ይላሉ፡፡ተማሪው በየትኛውም መንገድ የሚሰጠው መጋቢ ምላሽ ወደፊት ለሚጽፈው ድርሰት አጋዥ እንዲሆንለት ይጠበቃል፡፡ ግብረ መልስ በቃልና በጽሁፍ ሊሰጥ እንደምችል (Kroll 1990) ያመለክታሉ፡፡ በተለይ ተማሪዎች ብዙ በሆኑበት ክፍል ለእያንዳንዱ ተማሪ ግብረ መልስ ማድረግ የማይቻል ነው፡፡በዚህ ተጠቅሞ መጋቤ ምላሽ መስጠት ጠቃሚነት አለው ተማሪዎችንም ለዚሁ ተግባር ማዘጋጀት ይጠበቃል፡፡

እውነተኛ ጽህፈት የማስተማር ግብ ተማሪውን ቀስ በቀስ በማለማመድ ከመምህሩ ርቆ በሚሄዱበት ጊዜ ሀሳቡን በጽሁፍ በሥርዓት መግለጽ እንዲችል የሚያስፈልገውን የአጻጻፍ ስትራቴጅና መሣሪዎችን ማስጨበጥ ነው፡፡ እንግዲህ ይህንኑ መሣሪያ ለማስታጠቅ የሚቻልበትን መንገድ በመሻት ሂደታዊ ዘዴን በመሳሪያነት መምረጥ የተሻለ ነው፡፡

## 2.2 የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች

ቋንቋ ለማስተማር መምህራንን በጋራ የሚያስማማ ወጥነት ያለው አንድ የታወቀና ብቸኛ ዘዴ የለም፡፡ ቢሆንም ግን እንደማንኛውም ሥራ ጽሁፍም ዕቅድን ተከትሎ ቢከናወን የተሻለ ውጤት ላይ ሊደርስ እንደሚችል የሚሰማሙ አሉ፡፡ በዚህም ምንድነው የምጽፈው? ለማን ነው የምጽፈው? መቼ ነው የምጽፈው? ሀሳቤን፣ መረጃዬን የት ነው የማገኘው? እንዴትስ ነው የማደራጀው ለሚሉት ጥያቄዎች አስቀድሞ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል (ማረው 1998)፡፡


እንደ Richard (1990) and Murray (1982) ገለፃ ጽህፈት ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ የሚደረጉት የማስተማሪያ ስልቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነርሱም ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር ጽህፈትን የማስተማሪያ ስልቶች ናቸው፡፡ ውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ በጽህፈት ትምህርቱ ተማሪዎች በሚያመርቱት የመጨረሻ ረቂቅ ጽሁፍ ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም በተማሪዎች የመጨረሻ ውጤት ላይ ያለውን የሰዋሰው ትክክለኛነትን ይመረምራል፡፡ ሂደት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ እንደ ውጤት ተኮር አቀራረብ ባለቀለት ሥራ ላይ አተኩሮ ከማስተማር ይልቅ በመፃፍ ሂደት ላይ ባለ ሥራ ላይ አተኩሮ ማስተማርን ይከተላል፡፡ የዚህ ጥናት አብይ ርዕስ ጉዳይም የጽህፈት ትምህርት አቀራረብን የሚመለከት በመሆኑ በሰፊው ይዳሰሳል፡፡

አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ወይም ለተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት በሁለተኛ ቋንቋ ሲሰጥ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ ተማሪዎች ሂደት ተኮር ጽህፈትን የማስተማር ሥልት ይበልጥ ጠቃሚ እንደሆነ አጥኚዎች ይመሰክራሉ፡፡ ለአብነት ያህል Silva (1990) ቋንቋ ሣይንስ መሆኑን ጠቅሰው ጽህፈት ወይም ድርሰት በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ

ቋንቋነት ለሚማሩ እምብዛም ልዩነት እንደሌለው በመግለጽ አክለውም ሂደት ተኮር ስልት ለሁለቱም ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

### 2.2.1 ሂደት ተኮር የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ (PROCES APPROACH)

ሂደት ተኮር የጽህፈት ሥራ እንደፈጠራ ሥራ ጊዜና አዎንታዊ ግብረ መልስ ይፈልጋል፡፡ በአግባቡ እንዲተገበር መምህሩ ስለሂደቱ በቂ ማብራሪያ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ሂደታዊ አቀራረብ አገልግሎታዊ (Functional) የቋንቋ አተያይን፣ ተግባቦታዊ አቀራረብ (Communicative approach) እና ተማሪ ተኮር (learner Centered) ሥነ -ዘዴን መሠረት አድርጐ ከውጤታማ አቀራረብ በኋላ ተሻሽሎ የቀረበ መሆኑ ይታመናል፡፡ Richards (1990) እንደሚሉት ሂደት ተኮር አቀራረብ ለጽህፈት ትምህርት ክሂል ማስተማሪያነት እየዋሉ ካሉ አቀራረቦች ይበልጥ ውጤታማ ሆኖ ይታያል፡፡ ምክንያቱም አቀራረቡ ተማሪዎች ለጽህፈት ተግባራዊነት የራሳቸውን አካሄድ እንዲያዳብሩና በጥልቀት እንዲመራመሩ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ሂደት ተኮር የጽህፈት ሂደት የሚያልፍባቸው በርካታ ደረጃዎች እንዳሉት በመግለጽ (Hedge 1991) ሂደቱን በሚከተለው ሞዴል አስፍሯል፡፡




ከላይ እንደተመለከትነው የጽህፈት ሂደት ከማቀድ ጀምሮ እስከ አርትኦት ድረስ ቀጥ ብሎ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላው የሚሸጋገር ሳይሆን እንደገና ማቀድን ጨምሮ በማርቀቅና በመከለስ ወደፊትና ወደኋላ እየተመላለሱ የሚጽፉበት ሂደት መሆኑን (Hedge 1991) አክለው ገልጸዋል፡፡

በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ የሚወሰደው የቆይታ ጊዜም በጽሁፍ ዓይነት ላይ የተወሰነ እንደሆነም ይገለፃል፡፡ ለምሣሌ ለጓደኛ ስለጤንነቱና ስለቤተሰቡ ሁኔታ እንዲገለጽ የሚጻፍ ደብዳቤና የትምህርት ቤትን የሥራ እንቅስቃሴ የተመለከተ ዘገባ ለመጻፍ በማቀድ ላይ የሚወስደው የጊዜ መጠን እኩል አይሆንም፡፡

ሂደታዊ አቀራረብ በጽህፈት ማስተማር ሂደት ላይ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ያመጣ ሲሆን ለውጡም የተማሪዎችን ሚና የመምህሩን ሚና በአጠቃላይ በጽህፈት ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደውን እንቅስቃሴ ሁሉ ነክቶታል፡፡ በክፍል ውስጥ የማስተማር ሂደት በተማሪዎች መካከል እርስ በርስ ተባብሮ የመስራት ሁኔታ እንዲኖር የሚያበረታታ ለመጀመር የሚችሉበትን ሁኔታ (ርዕስ መምረጥ፣ሀሳብ ማመንጨት፣ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ የሚችሉበትን ስልት) እንዲያበለጽጉ ለማርቀቅ (መጨመር፣መቀነስ፣ማሻሻልና ሀሳብን መልሰው ማቀናበር እንዲችሉ) እና ለአርትኦት (በቃላት፣በዐረፍተነገር መዋቅር፣በሰዋስው፣ በሥርዓተ አፃፃፍ ላይ እንዲያተኩሩ) ሁኔታ ያመቻቻል (Silva 1990)፡፡

በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ እንደውጤታማ አቀራረብ ከተጠናቀቀ የጽሁፍ ረቂቅ ላይ እንዲሁም በቋንቋው ቅርጽ ላይ ከማተኮር ይልቅ የመፍጠር አዲስ ነገር የመፈለግ፣ትርጉምን የማስፋፋት ሂደትን የሚከተልና በጽሁፍ ይዘት (ፍቺ) ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ የመምህሩ ሚና ከውጤት ተኮር አቀራረብ የተለየ ነው፡፡ይኼውም ተማሪዎቹ አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑት ተግባር ሀሳብን የማፍለቅና ማደራጀት፣ለመጻፍ በተደጋጋሚ ረቂቅ መጻፍ፣ያረቀቁትን መከለስ፣ መሰረዝ፣መጨመር፣መቀነስን ደጋግሞ ሀሳብን የማደራጀት፣ ለማረም የቃላት መረጣን፣ የዐረፍተ ነገር አወቃቀርንና የአጻጻፍ ሥርዓትን መከታተልና መረዳት ላይ የሚያተኩሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ተማሪዎች የራሳቸውን ስትራቴጂ እንዲያዳብሩ የማስቻል ሚና አላቸው (Silva 1990 እና Hedge1991)፡፡

በአጨራረስ ሂደት ውስጥ ያለን አዕምሮታዊ ተግባር በንድፈ ሀሳብ ደረጃ Linda flower እና John, R. Hayes (1982) እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡፡

ይህ ንድፈ ሀሳብ (Cognitive Proess theory) በመባል ይታወቃል፡፡

1. የመድረስን ሂደት በይበልጥ የምንረዳው ደራሲው በሚደርስበት ጊዜ ራሳቸውን የቻሉ የአስተሳሰብ ሂደቶችን የሚያደራጁበት ጊዜ ነው፡፡
2. እነዚህ ሂደቶች በተዋረድ / Hierarchically / እንዳየናቸው ከሌላው ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ በመካተት ሊደራጁ የሚችሉ ናቸው፡፡

3. የመድረስ ሂደት ራሱ በዓላማ ላይ ያተኮረ የአስተሳሰብ ሂደት ሲሆን በራሱ በደራሲው ግብ የሚመራ ውስብስብ ሥርዓት ነው።
4. ደራሲዎች በመድረስ ሥራ ውስጥ ከተወሰነ ወይም በሂደት ሊቀየር ከሚችል ዓላማ አኳያ የራሳቸውን የድርሰት ግብ ይፈጥራሉ።

ሂደት ተኮር ጽህፈትን የማስተማር ሥነ - ዘዴ መተግበሪያ መንገዶች ወይም ደረጃዎች እንደተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ይሁኑ እንጂ በአብዛኛው ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት ነው። በዚህም ለተማሪዎች የተሻለ ሥነ ዘዴ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። Hedge(1991) እንደሚነግሩን ይህ ዘዴ በእንግሊዝና በሰሜን አሜሪካ በእንግሊዝኛ ትምህርት ተማሪዎች ጽህፈት መፃፍ የሚማሩበት ዘዴ ሆኗል። እንደርሳቸው አባባል ይህ ዘዴ ተጽፎ ያለቀለት ሥራ ከመመርመር ይልቅ የተሳካላቸው ደራሲያን እንዴት እንደሚጽፉ ይመረምራል። በዚህ መሠረት በዚህ ዘዴ የተማሪዎችን ሀሳብ እንደመጣላቸው መጻፍና እንዴት መከለስ እንደሚቻል እንዲያውቁና እንዲለማመዱ ማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው።

Raimes (1983) በበኩላቸው እንደሚሉት በዚህ ዘዴ የሚያስተምሩ መምህራን ሁለት ወሳኝ የሆኑ ድጋፎችን ለተማሪዎቻቸው እንደሚሰጡ ያስረዱናል። አንደኛ ተማሪዎች በሚሰሩዋቸው ረቂቆች ላይ ሀሳብ ማመንጨት እንዲችሉና የይዘት ግብረ መልስ እንዲያገኙ ጊዜ ይሰጡአቸዋል። ሁለተኛ የመፃፍ ሂደት፣የመፍጠር ሂደት እንዲሆንላቸው ተማሪዎቻቸውን ያግዛሉ።

Richards (1990) እንደሚሉት የጽህፈት ትምህርት ግባችን ተነባቢነት ያለው ድርሰት ተማሪዎች መጻፍ እንዲችሉ ከሆነ ደራሲዎች እንዴት ድርሰቶቻቸውን እንደጻፉ መመርመርና እኛም ከዚህ ፍንጭ በመነሳት ጽህፈት እንዴት ልናስተምር እንደሚገባን የማስተማር ዘዴዎችን ልንመረምር ያስፈልገናል። አክለውም የተሳካላቸው ደራሲዎች የተሻለ ጥራት ያለው ጽህፈት ለመጻፍ የቻሉት በተገቢ የአፃፃፍ ሂደት ስለሚጽፉ ነው ይላሉ። በተጨማሪ ደጋግመው ርዕስ ጉዳዩን በማብላላትና በማሰላሰል በተደጋጋሚ የማርቀቅና የመከለስ ደረጃዎችን በመጠቀማቸዉ በምጽፉት የጽህፈት ይዘትና ቅርጽ ላይ ጥሩ ውጤት አሳይተዋል። ይህም ውጤት በተማሪዎችና በመምህራን ሚና እንዲሁም በጽህፈት ትምህርት ወቅት በምንጠቀምባቸው ትምህርታዊ ልምዶች ላይ ሊንፀባረቅ ይችላል።

### 2.2.1.1 የሂደታዊ ዘዴ የአፃፃፍ ሂደት ደረጃዎች

Richards (1990) በሂደት ተኮር ዘዴ ጽህፈትን ማስተማር የተለያዩ የክንውን ደረጃዎች እንዳሉት ይነግሩናል፡፡ በተጨማሪ Murray (1982) ሂደታዊ የድርሰት አጻጻፍ በሶስት ደረጃዎች ውስጥ እንደሚያልፍ ያሳዩናል፡፡

#### ሀ. ቅድመ ጽህፈት ደረጃ

ቅድመ ጽህፈት የማሰላሰል ደረጃ ሲሆን መፃፍን ከመጀመር በፊት የሚከናወኑ ዝግጅቶችን በሙሉ ይይዛል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ሀሳባቸውን የሚያሰባስቡበት፣ ርዕስ የሚመርጡበት፣ስለሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ የተለያዩ ሀሳቦችን ከተለያየ አቅጣጫ የሚያሰባስቡበት፣ዕቅዳቸውን የሚነድፉበትና በአጠቃላይም ወደ ዋናው የጽህፈት ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነው፡፡ ስለ ምን ልፃፍ? እና እንዴት ልፃፍ? የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት በዚህ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ላይ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ይነጋገራሉ፡፡ መምህራን ለተማሪዎች መመሪያ በመስጠት የሚጽፉትን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ እንዲያውቁት ይመራሉ፣ ይከታተላሉ ይላሉ (Murray 1982 Hedge 1991 እና Richards 1990)::

#### ለ. ጊዜ ጽህፈት

ጊዜ ጽህፈት የማርቀቅ ደረጃ ሲሆን በዚህ ደረጃ ሀሳብ በማፍለቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማመቻቸትና የመጀመሪያ ረቂቅ መፃፍ፣ የተፃፈውን የማንበብና የመከለስ ፅሁፉ የሚዳብርበትን ሀሳብ የመፈለግ ተግባር ይከናወናል፡፡ ተማሪዎች በዚህ ጊዜ ለሰዋሰዋዊ ስህተቶች አይጨነቁም ሀሳብ እንደመጣላቸው ይፅፋሉ የማይፈልጉትን ሀሳብ አስወጥተው አዲስ ሀሳብ መተካት ይችላሉ፡፡ በጊዜ ጽህፈት ቅድሚያ የሚሰጠው ለይዘት ትክክለኝነት ሲሆን በቀጣይ በሚጽፉት የጽህፈት ረቂቅ ላይ ከይዘት ባሻገር ተማሪዎች የተጠቀሙባቸውን ስርዓተ ነጥቦች ሰዋሰው፣ ሆሄያት አጣጣል ወዘተ…የመመርመርና የማስተካከል ተግባርን ያከናውናሉ፡፡ Hedge (1991) በዚህ ደረጃ ፀሀፊው ያረቀቀውን ሀሳብ መግቢያ፣ ዋና አካልና መደምደሚያ በማለት ያከፋፍላል፡፡

### ሐ. ድህረ ጽህፈት

ድህረ ጽህፈት የክለሳ ደረጃ ሲሆን ፀሐፊው የፅሁፉን መልዕክት፣ቅርጽንና ተደራሲን ደግሞ የሚያስብበት የመልዕክቱን ግልጽነት የሚገመግምበትና የመጨረሻ ማስተካከያ የሚያደርግበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ፀሐፊው በፅሑፉ ውስጥ ለአንባቢያን ያስቸግራሉ የሚላቸውን የተለያዩ ቃላት ለይቶ በማውጣት ማስተካከያ ይሰጣል፡፡ የተፃፈውን ፅሑፍ ከሰዋሰው፣ ከስርዓተ ነጥቦችና ከሀሳብ አደረጃጀት አኳያ የሚመረምርበት በዚህ ደረጃ ነው፡፡በመሆኑም የፀሐፊው ተግባር እንደተደራሲው አንባቢ በመሆን ፅሑፉን ማንበብ ነው፡፡ ንባቡም ግልፅ በሆነ መንገድ አንባቢዎቹ ለማለት የፈለኩትን ሊረዱት ይችላሉ ወይ የሚለውን ለመገምገም ነው፡፡ በተጨማሪም ለፅሑፉ ቅርጽና ይዘት ትኩረት በመስጠት እርማት ያደርጋል፡፡ የተዛቡ ሀሳቦች ካሉ ይስተካከላሉ ፡፡ እርማቶችም የሚካሄዱት በተማሪው፣ በጓደኞቹና በመምህሩ አማካይነት ይሆናል፡፡

## 2.2.1.2 በሂደታዊ አቀራረብ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና

በሂደታዊ አቀራረብ ጽህፈትን የሚያስተምር መምህር ለተማሪዎች የእርስ በርስ መማማር ወይም ተራክቦ ቦታውን እንደሚሉት ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሰረት መምህሩ መማርን የማመቻቸትና የመከታተል፣ የተማሪዎችን የፅሑፍ ተግባቦታዊ ክህሎት የማዳበር ፣የተማሪዎችን ፅሁፍ የማንበብ፣ የመገምገምና የማማከር፣ እንዲማሩ የማገዝ፣ መማርን የማፋጠን ሚና ይጫወታሉ (Hedge 1991 እና Leki 1996) ፡፡ በአፃፃፍ ሂደትም ተማሪዎች በማሰላሰል፣ በማቀድ፣ በማርቀቅ፣ በመከለስ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ጽህፈት በሚጽፉበት ጊዜም የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች የሚጽፉበትን ምቹ ሁኔታ ማዘጋጀት፣ የጥሩ ጽህፈት ሞዴል የሚሆኑ ፅሁፎችን ማሳየት፣ በቂ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ ወዘተ…ይጠቀሳሉ፡፡

ሂደታዊ የጽሕፈት አቀራረብ በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የመምህሩ የማስተማር ዘዴ በተመለከተ (Richards 1990) የሚከተለውን ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ መምህሩ ተማሪውን እንደውጤታዊ አቀራረብ ዘዴ ያለቀለት ሥራ እንዲያቀርብ የተወሰነ ነገር የሚጠይቀው ሳይሆን ተማሪው ትክክለኛ ፅሑፍ ለመፃፍ የሚያስችለውን ዘዴ

የሚቀይስና የሚያመቻች እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በሂደታዊ የፅሕፈት ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና የፅሕፈት ክሂል ለማዳበር ምቹ መሆን እንዳለበት (Richards 1990; Hughay & et.al 1983) ን ጠቅሰው የሚከተሉትን ነጥቦች ይዘረዝራሉ፡፡

1. የጽሕፈቱ ሥራ ግልጽ፤ ቀላልና ቀጥተኛ እንዲሆን በማድረግ የአፃፃፍ ሂደቱን ያስተምራል ፡፡
2. የጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር የሚያስችል የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብ ያዘጋጃል፡፡
3. የጽህፈቱን ውጤት ይተነትናል ፣ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸውን ሀሳቦች ይጠቁማል፡፡
4. የክፍል ውስጥ ክንውንን በግልና በቡድን እንዲሰሩ በማከፋፈል የክፍሉን ተማሪ በእኩል ተሳታፊ ያደርጋል፡፡
5. ተማሪዎች እርስ በርስ የሚማማሩበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
6. የንባብን፤ የማዳመጥንና መናገርን ክሂሎች የሚያዳብሩ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡
7. ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርት ሂደት ውስጥ ሀሳባቸውን በተለያየ መንገድ እንዲያፈልቁ ያግዛል፡፡
8. ተማሪዎች የተለያዩ አስተሳሰቦች፤ የሃሳብ ቅደም ተከተሎችንና የመሳሰሉትን በተገቢው መንገድ መፃፍ የሚችሉበትን የጽህፈት አፃፃፍ ህጎችን ያስተምራል፡፡
9. ተማሪዎች በጽህፈት ሂደት ላይ እያሉ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

### 2.2.1.3 በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የተማሪው ሚና

በትምህርቱ ሂደት የተማሪው ሚና መማር ነው፡፡ መማርን ማከናወን ያለበትም የነገሩትን በማድመጥና የሰጡትን በጭፍን በመወከል ሳይሆን በመስራት፣ በመመርመር፣ በመሞከርና በማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም በተማሪው የመማር ሚና ላይ የሚከሰተው ልዩነት

ለተማሪው ከሚሰጠው ትኩረት የሚመነጭ ሲሆን በመማሩ ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መገመት ይቻላል፡፡

የተማሪው ሚና በመማር ሂደቱ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በማስተማር አቀራረቦችና ሥነ-ዘዴዎች ውስጥ በግልፅም ሆነ በውስጠ ታዋቂነት ይታያል፡፡ ይህም በትምህርቱ ሂደት ተማሪው በሚያከናውናቸው ተግባራት አይነቶች ለትምህርት በሚቀርበው አይነት ላይ በሚኖረው ተነሳሽነት እና በሚሰራበት ቡድን ውስጥ ባለው ተሳትፎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ (Richards and Rodgers; 1986)::

በሂደታዊ የጽህፈት ማስተማር ዘዴ የጽህፈት ትምህርት ከውጤት ወደ ሂደት መለወጡን ተማሪዎች በሚያከናውኗቸውተግባራት ላይ ትኩረት መደረጉን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ Richards (1990) Zamel (1987)ን በመጥቀስ በሂደታዊ አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች ምን መፃፍ (ትረካ፤ ገለፃ፤ ንፅፅር..ወዘተ) እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው ትኩረት የመስጠትና የራሳቸውን ሥራ ራሳቸው በማረም ተሳትፎ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል በሂደታዊ አፃፃፍ ተማሪዎች በፅሑፋቸው ይዘት ዓላማና ተደራሲ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው Richards (1990) Carey (1986)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ፡፡ በመማሩ ሂደት ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርዕስ ይመርጣሉ፤ በህብረት እንዲጽፉ ይበረታታሉ፡፡ በዚህ ሂደትም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተራክቦአዊ አሰራርን ያዳብራሉ፡፡ ርዕስን ከቤትና ከትምህርት ቤት ገጠመኞቻቸው በመምረጥ በህብረት በሚፅፉበትጊዜ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚያውቋቸውንና የሚጠቀሙባቸውን ነገሮች በምንጭነት ይጠቀማሉ፡፡ ይህ በእውናዊና በራስ ገጠመኝ ላይ መፃፍ የመማር ተነሳሽነት ለማጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ጎበዝና ደካማ ተማሪዎችን በመተጋገዝ እንዲሰሩ፤በመማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችንም በጋራ እንዲፈቱ ያስችላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በሂደታዊ አቀራረብ ዘዴ ጽህፈትን መማር ተማሪዎች በራሳቸው የመማር፣ ሃላፊነት የመውሰድ፣ የብዙ ሰዎችን አስተያየት የመጠቀምና በጽህፈት አማካይነት ሀሳብን የመሰብሰብ የማጥናት ወዘተ…ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ የራሳቸውን ዕውቀት በራሳቸው ቋንቋ ለመግለጽ የማሰላሰል፣ የማቀድ፣ የመወያየት፣ ለማንና ለምን እንደሚጽፉ የመወሰን፣ ረቂቅ የመፃፍ፣ የመከለስና የማረም ሂደቶችን ያከናውናሉ፡፡

## 2.2.2 ውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ

ውጤታማ አቀራረብ ከረጅም ጊዜ አንስቶ ፅህፈትን በማስተማር ሂደት ሲያገለግል የኖረና በአሁኑ ጊዜም ለተለያዩ አላማዎች በማገልገል ላይ ነው። ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት የመጨረሻ ውጤትና በቋንቋው ቅርጽ ላይ ነው።

(Richards 1990)። ይኸውም ተማሪዎች ለሚጽፏአቸው ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናሉ ወይም

ጥሩ ተጽፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ፅሁፎችን ሞዴልነት አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣የአፃፃፍብልሃትን ወዘተ…በማሳየት ተማሪዎች እነዚያኑ አስመስለው እንዲጽፉ የሚያለማምድ ነው (Nunan 1989 እና Richards 1990):: በዚህ ዘዴ ዓላማ መሰረት ተማሪዎች የሚጽፉት የሰዋሰው፣ የስርዓተ ፊደልና ሌሎች ስህተቶችን ለማስተካከል ሲሆን፣በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የጽህፈት ተግባራት በቋንቋው ሰዋሰው ላይ ያተኩሩ ናቸው። ፡ተማሪዎቹ በሞዴልነት በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ፆታን፣ጊዜን፣ ቁጥርን፣ ወዘተ… በመቀያየር የሚለማመዱባቸው ጠቋሚ መልመጃዎች ይቀርባሉ። በመምህሩ ተመርጦ በሚሰጣቸው ርዕስ ድርሰት ሲፅፉ መጀመሪያ ትኩረታቸውን በቋንቋው መዋቅር ላይ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ሰዋሰዋዊ ስህተቶችንም ለማስወገድ ሲሉ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይረዳል (Leki 1996)::

በከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የዚህ አቀራረብ ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀፆችና አውዶች መዋቅርና አደረጃጀት ላይ ነው። ዓላማውም ትክክለኛ ፅሁፎችን ማፍለቅ ነው።ዋና ዋና ባህሪያቱና መርሆዎቹ የሚከተሉት መሆናቸውን (Richards 1990) ይገልፃሉ።

1. አፃፃፍ የድርሰት መመሪያዎችንና የሰዋሰው ህጎችን በተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በማሳየት ተማሪዎቹ በተግባር እንዲለማመዷቸው ያደርጋል።
1. የፅህፈቱ ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸውን ፅሑፎች መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። በተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች ቅርፅና

አደረጃጀት ላይ ያተኩራል ፡፡

3. ትክክለኛ የዐረፍተ ነገር መዋቅር መስራት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው፡፡ ስለዚህ የሰዋሰው ችሎታ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፡፡
4. ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲጽፉና ስህተት እንዳይሰሩ ለማድረግ ይሞከራል፡፡ የእጅ ፅሁፍ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት አገባብ፣ የፊደል አጣጣል፣ ወዘተ…እውቀቶች በትምህርትነት ይሰጣሉ፡፡

በውጤታማ ዘዴ የትምህርቱ አቀራረብ ቅደም ተከተል የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን በተናጠል ከመመስረት አንስቶ አንቀጾችን መገንባት ከዚያም የተለያዩ ድርሰቶችን ወደ መጻፍ የሚሄድ ነው፡፡ በዚህም ሰዋሰዋዊ ሕግጋት ፣የአንቀጽ አገባብ ዕውቀትና የተለያዩ ድርሰት አይነቶች ( (ገላጭ፣ ተራኪ፣ ሥዕላዊ፣ አመዛዛኝ፣ ወዘተ..) በትምህርትነት ይሰጣሉ፡፡ ልምምዶቹም ሞዴሎችንና የዓረፍተነገር አመሠራረት ሰዋሰዋዊ ሕግጋትን መሠት ያደረጉ ናቸው፡፡

### 2.2.2.1 ውጤታማ አቀራረብ የፅህፈት ደረጃዎች

በውጤታማ አቀራረብ ጽሕፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህን ተግባራት ውስን ጽሕፈት
ምር ጽሕፈትና ነፃ ጽሕፈት ደረጃዎች ናቸው (Raimes 1983 እና Richards 1990)፡፡

### ሀ. ውስን ፅህፈት (Controlled Writing)

ለመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ለሚዛሄድ የጽሕፈት ትምህርት የሚቀርብና የውስንነት ደረጃው ፍጹም ወይም አንጻራዊ የሆነ ክንውን ነው፡፡የዚህ የጽሕፈት ሥራ ዋና አላማ ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መንገድ ከሥህተት የጸዳ ጽሑፍ እንዲጽፉ ማድረግ ነው፡፡ በውስን የጽሕፈት ደረጃ ጽሕፈትን ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ውስን ማሰብንና ማፍለቅን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በውስን ጽሕፈት ደረጃ ባዶ ቦታዎችን መሙላ ፣በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት ዓረፍተነገር መሥራት ቅደም ተከተላቸው የተፋለሰ ከላትን በማስተካከል ዓረፍተ ነገር መሥራት በአንቀጽ ውስጥ የቁጥር፣የጾታ፣የጊዜ፣ወዘተ…ለውጥ በማድረግ እንደገና መጻፍ የመሣሰሉት ይገኙባቸዋል (Doff 1988 እና Karoll 1991)፡፡ በዚህ ዘዴ የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች ወደ

ብዙ ሥህተት እንዳያመሩ ቁጥጥር የሚያደርጉ ሲሆን አብዛኛው ትኩረታቸው በሰዋሰው አገባብና አጻጻፍ ዜደ ላይ በመሆኑም ከርቱዕነት ይልቅ ለትክክለኛ ቋንቋ አጠቃቀም ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡

### ለ. ምር ፅህፈት (Guided Writing)

ምር ጽሕፈት በውስንና ልቅ ጽሕፈት መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ይሄውም ተማሪዎች በውስን ጽሕፈት ደረጃ ካዳበሩት መሠረታዊ የዓረፍተነገር አጻጻፍ ኪሂል በተጨማሪ የአጻጻፍ ሥልትን ለመለየት የምያግዙና ወደ ነጻ ጽሕፈት የሚያሸጋግሩ ይዘቶችን የምይዝ በመሆኑ ነው፡፡በዚህ ደረጃ ተማሪዎች መምህሩ ለሚያቀርብላቸው ሞዴል መሠረት ጠጽሕፈት ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ መምህሩ ሞዴሉን መሠረት እያደረገ የሞደሉን አገልግሎትና የአጻጻፍ ሥልቶች በመግለጽ ምሣሌ በማሳየት የቀረበውን ሞዴል አንብበው ባሕርያቱን እንድገመግሙ በማድረግ መጠነኛ በሆነ ልዩነት ተመሣሣይ ጽሑፍ እንዲጽፉ ያበረታታል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚካሄዱ ውይይቶች ድርሰትን ለመጻፍ የሚያገለግሉ ምር የጽሕፌት ተግባራት መሆናቸውን (Doff 1988 እና Raimes 1983) ይገልጻሉ፡፡

### ሐ. ነጻ (ልቅ) ፅህፈት (Free Writing)

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በአብዛኛው መምህሩ በሚሰጣቸው ወይም ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሃሳብ አፍልቀው በራሳቸው ቋንቋና አገላለጽ ጽህፈት የምጽፉበት ነው (Raimes 1983)፡፡ ጽህፈት የመጻፉ ሥራ የሚጀመረው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ቅርጾች በመለማመድ ነው፡፡ ከልምምድ ቀጥሎ ለሚጽፉት የድርሰት ዓይነት ሞዴል ይቀርባል ፡፡ ሞዴሉን በአጻጻፍ ሥልቱም ሆነ በይዘቱ መነሻ በማድረግ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ጽህፈት እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡ ነፃ ጽሕፈት ለሰዋሰዋዊ አጠቃቀም እና ለሥራዓተ አጻጻፍ ትኩረት የሚሰጥ እንዲሁም በትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሃሳብ የሚገልጹበት እድል ይሰጣል (Raimes 1983)፡፡ ስለሆነም ይህ ደረጃ በአንጻራዊነት በርካታ የጽሕፈት ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡

ነጻ ጽሕፈት ተማሪዎች ሃሳባቸውን ለመግለጽ የሚጽፉበት ደረጃ ቢሆንም የጽሑፋቸው መለኪያ ምን ፣እንዴት፣ለማንና ለምን ተጻፈ? የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ የሚነሱት ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ጽሑፍ ቀረበ ወይ? የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም

የተማሪዎቹ ትኩረት የሚያርፈው ሃሳባቸውን በመግለጽ ላይ ሳይሆን በጽሑፋቸው ጥራት ወይም ንጽሕና ላይ ነው (Byren 1991) ::

ውጤታማ አቀራረብ ተማሪዎችን ከውን ጽሕፈት ወደ ነፃ የአጻጻፍ ልምድ እንዲሸጋገሩ ስለሚያደርግ ብዙ ጊዜ ለስህተት አያጋልጣቸውም። አብዛኛውን ግዜ ከትክክለኛ የአጻጻፍ ልምድ ጋር ስለሚያስተዋውቃቸው ምሣሌውን ተከትለው የራሳቸውን ሀረግንና ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር መመስረትና ሃሳብን በጽሑፍ ማስተላለፍ እንዲችሉ ያግዛቸዋል (Richards 19)

ነገር ግን በዚህ ዘዴ የሚማሩት ተማሪዎች ሁል ጊዜ የተጠናቀቀ ነገርን ብቻ እንዲጠቀሙ ስለሚያደርግ በጽሕፈት ክሕል ትምህርት ሂደት የሚታለፍባቸውን ማቀድን፣ማርቀቅን፣ መከለስንና ማረምን የዘነጋ መሆኑን (Raimes 1983) በመጠቆም ደካማ ጎኑ መሆኑን ያስረዳል።

### 2.2.2.2 በውጤታማ አቀራረብ የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና

በውጤታማ አቀራረብ የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና በአብዛኛው የቋንቋውን ሰዋሰውንና ህጎችን ማስተማር የተማሪዎችን የመጨረሻ ውጤት ሰብስቦ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን የአፃፃፍ ስርዓተ ግድፈቶችን ማረም የጽሁፉን ጥሩነትና መጥፎነት ከትክክለኛ አንፃር መገምገም ለመማር የሚያበረታታ አስተያየት ወይም ውጤት መስጠት ነው። በውጤታዊ አቀራረብ ፅህፈትን ለማስተማር የሚዘጋጅ መምህር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ዝግጅት ሊያደርግ እንደሚገባ (Byrne 1991) ይገልፃል።

1. ለፅህፈት ክሂል የተመረጡት መልመጃዎች ለተማሪዎች ቀርበው ከመተግበራቸው በፊት ተገቢነታቸውን፣ ቀስቃሽነታቸውን፣ ግልጽነታቸውንና ለአውዱ ተገቢ መሂናቸውን ያረጋግጣል።

2. መልመጃዎቹ ግልጽ መመሪያ ያላቸውና ከሌሎች ከሂሎች ጋር ቅንጅት ያላቸው መሆኑን ያሳውቃል።
3. የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት ለተማሪዎች በማሳወቅ በጽሁፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያደርጋል።
4. ተማሪዎች ለጽህፈት ትምህርት ቅድመ ዝግጅት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

5. የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ እየተከታተለ ደረጃውን ጠብቆ ተገቢ መልመጃዎችን በማዘጋጀትና በማለማመድ ለምሳሌ ከውሱን መልመጃ ወደ ምር የጽህፈት ደረጃ አሸጋግሮ ከዚያም ከምር ወደ ነፃ የጽህፈት ደረጃ ያሳድጋል፡፡
6. በተሰጣቸው መመሪያ ወይም ሞዴል መሰረት ፅፈው እንዲያመጡ በማድረግ ተማሪዎችን በየደረጃው ይመራል፡፡ይቆጣጠራል፡፡
7. መልመጃዎችን በግል በጥንድና በቡድን ለማሰራት በሚያስችል መልኩ በማዘጋጀት ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ያሰራል፡፡
8. ተምሪዎች ራሳቸውን ችለው ከፃፉ በኋላ ስራዎቻቸውን ተለዋውጠው እንዲተራረሙና አስተያየት እንዲሰጣጡ ያበረታታል፡፡
9. በመጨረሻም የተማሪዎችን ፅሁፍ በማንበብ በፅሁፉ ማጠቃለያ ላይ አስተያየት ይሰጣል (Kroll 1990)፡፡

### 2.2.3 የዘውጋዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ

ተማሪዎችን የተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶች ማስተማር የበለጠ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው ይችላል ከሚለው አተያይ ጋር በተያያዘ፣ዘውግ ተኮር የማስተማሪያ ስልት በ1980ዎቹ ውስጥ የበለጠ ታዋቂነትን እያገኘ መምጣት ጀምሯል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶችን አየጠኑ ሲሄዱ በተጓዳኝነትም የተለያዩ መዋቅራዊና ቅርፃዊ የአፃፃፍ ስልቶችን በመረዳት በጽሁፋዊ ስራዎቻቸውም ውስጥ የተማሯቸውን የአፃፃፍ ስልቶች ተግባራዊ ሊያደርጓቸው ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ዘውግ አቀራረብ፣አካዳሚያዊ ጽሁፎች በሚዘወተርባቸው በክፍል ውስጥ ጽሁፋዊ ልምምዶች ላይ፣መምህራኑ በገሃዱ አለም ውስጥ የሚተገበሩትን ልዩ ልዩ የጽሁፍ አይነቶች ለምሳሌ፡- ልዩ ልዩ ዘገባዎች (ሪፖርቶች)፣የሥራ ደብዳቤዎች፣ ርዕሰ አንቀፆች፣ የህይወት ታሪኮች፣ ወዘተ… በክፍል ውስጥ በመልመጃነት እንዲለማመ ዱ የሚያበረታታ የአፃፃፍ ዘዴ መሆኑን በመጠቀም Yan(2005) በኦነ cope እና kalantzis (1993) የቀረበውን ማብራሪያ ዋቢ አድርገው እንደገለጹት በዘውግ አቀራረብ የሚዘጋጁ ጽሁፋዊ ስራዎች ሶስት አበይት ደረጃዎችን ተከትለው ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህም፡-

1.የታቀደውን የጽሁፍ አይነት የሚያስገነዝብ ማሳያ ሞዴል ለተማሪዎቹ ይቀርባል፡፡
2.የጽሁፋዊ ሥራው ጅማሮ በመምህርና በተማሪዎች ትብብር ይገነባል፡፡
3.የመጀመሪያው ረቂቃዊ ጽሁፍ በእያንዳንዱ ተማሪ (በግል) ይከናወናል፡፡

ይህ አቀራረብ ጽህፈት በማህበራዊ አውድ ውስጥ ይከናወናል የሚለውን ሀሳብ ያዳብራል። በተጨማሪም የተወሰነ ዓላማም ያንፀባርቃል። ይህም ዓላማ መማር ሊኖር የሚችለው በሙሉ ንቃተ ህሊና (consciously) በሚከናወን ማስመሰል እና ትንታኔ ነው የሚል ሲሆን፣ዘውግ አቀራረብ ግልጽ የሆነ የማስተማር ሂደትን ያመቻቻል።

በምዕራባዊያን ሀገራት ዘውግ ወይም የፅሁፍ ዓይነት በንግግር ወይም በፅሁፍ ብዙ ጊዜ የሚገለጸው ወይም የሚመደበው በቀዳሚነት በማህበራዊ ዓላማ ነው። እንደ Swales (1990) አስተያየት ተመሳሳይ ዓላማ የሚጋሩ ዘውጎች ተመሳሳይ የፅሁፍ ዓይነት ያመለክታሉ ሲሉ በጽሁፉ ውስጥ Drewianka (2003) በመጥቀስ ደግሞ ማህበራዊ ዓላማዎች ቀዳሚ በማድረግ ስድስት ሁኔታዎችን ማለትም ፡-

1. ታሪክ መንገር ፡-( Narrative) ለማዝናናት ታሪክ መንገር
2. መዘርዘር (Recount) የሆነውን መንገር
3. የመረጃ ዘገባ (Information report) እውነተኛ መረጃዎችን መስጠት
4. መመሪያ (Instruction) ለአንባቢ ወይም ለአድማጭ ምን እንደሚያደርግ መንገር
5. ማብራሪያ (Explanation) ጽሁፍ አንድ ነገር ለምን ወይም እንዴት እንደተከናወነ መንገር
6. የማብራሪያ ጽሁፍ (Expositors Text) አመለካከትን ማቅረብ ወይም መንገርን ለይተው አቅርበዋል።

እነዚህ ማህበራዊ ዓላማ ያላቸው የዘውግ ፅሁፎች የፅሁፍን ሥነ-ልቦናዊ ግብአት ይዟል:- የስነ ልሳን ደንቦችን ብዙ ጊዜ በሠንጠረዥ በተደገፈ የመዋቅር ቅርጽ ስነ ልሳናዊ ገፅታን ይሆናሉ። በተለየ ሁኔታ በሠንጠረዥ የተደገፈ መዋቅር ውስጣዊ መዋቅር ወይም በመግቢያ መልክ የተደራጀ ፅሁፍ ዋነኛው ፅሁፍ እና ማጠቃለያ እንዲሁም ከስነ ልሳን አንፃር የተገነቡ የቋንቋ ገፅታዎች ይዟል:- ሰዋሰው፣ ቃላት፣ አያያዦች፣ ወዘተ ፀሐፊው መረጃዎችን ለመተርጎም ወይም ሀሳብን ወደ ሚነበብ ፅሁፍ ለመለወጥ መጠቀም አለበት።

የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ስለቋንቋ ያለን ዕውቀት ለተማሪዎች በቀላሉ ወይም ግልፅ በሆነ መንገድ ማቅረብ ላይ ነው፡፡ ዘውግ የሚያመለክተው የጽሁፉን ይዘት እና ቅርፅ ክፍል ነው፡፡ በሌላ በኩል ዘውግ እንደ ጽሁፍ ባህሪ ሊገለጽ ይችላል፡፡ እንደ Swales (1990) ገለፃ Stan (2000)ን በመጥቀስ ዘውግ ሥርዓታዊ ሂደት ሲሆን በየጊዜው እንደነበሩት ንድፈ ሀሳቦች (contemporary theories) ሁል ጊዜ የሚለዋወጥ ነው፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ባህሎችን እና የማህበረሰብ ፍላጎቶችን ለማሟላት ወጥነት ባለው መልኩ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህ መሠረት ዘውግን ስንተነትነው ዋነኛው እና ማዕከላዊው ነጥብ ዓላማ ነው፡፡ የተለያዩ ዓይነት ፅሁፎች ወይም ዘውጎች ይኸውም፡- የቅሬት ደብዳቤ፣የግብዣ ወረቀት፣የህግ ዘገባዎች ለተለያየ ዓላማ ይውላሉ፡፡ Swales (1990) ዘውግን ሲገልጹ ተመሣሣይ ተግባቦታዊ ዓላማዎችን የሚጋሩ ሰዎች ተግብቦታዊ ሁነቶች የሚታዩበት ነው፡፡

የዘውግ ተኮር አቀራረብ በዋናነት ገንቢ በሆነ መልኩ የተለያዩ ዓላማዎችን ለመርዳት በማህበራዊ አውዶች መፃፍን ስናስተምር መዋቅሮችን እና ስነ-ልቦናዊ ገፅታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን (Yan 2005)፡፡በሌላ በኩል አገባብ፣ መዋቅር፣ ዓላማ እና ስነ-ልሳናዊ ገፅታዎችን እንደዘውጋቸው በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ መንፀባረቅ ያለባቸው ሲሆን በዚህ አቀራረብ ለአንባቢው እና ለጽሁፍ ዓላማ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

የተማሪዎች ስነ-ልሳናዊ ገፅታ እና መዋቅራዊ ደንቦች የተለያዩ ዘውጎች መሠረት አድርገው የሚፈጠሩት ተግባቦቶች ብዙ ጊዜ ውሱንነት ያለባቸው በመሆኑ በመፃፍ ትምህርቱ ጊዜ መምህሩ ተማሪዎችን በመምራት፣ በመደገፍ እና በመርዳት በኩል የተለያዩ ዘውጎች መነሻነት ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር ሲነጻጸር ግብአትን በተመለከተ በመካከላቸው ግልፅ መመሳሰል ይታያል፡፡ Yan (2005) Badger and White (2000) ጠቅሶ እንደገለፀው የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ ሆነው የሚማሩት የተለያዩ ምሳሌዎች እና ፅሁፎች ሲቀርብላቸው መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

ከዚህ ቀደም ዘውግ የሚለው ቃል በሥነ-ጽሁፍ፣ በሥነ-ቃል እና በፊልም ጥናት ላይ ትኩረት ያደርግ የነበር ሲሆን አሁን ደግሞ በሥነ-ልሳን ዘርፍ ላይም ጥቅም ላይ እየዋለ

ይገኛል ፡፡ በሌላ በኩል Swales (1990) የዘውግን ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል፡-

1. ዘውግ ከተግባቦታዊ ሁነቶች የሚመደብ ነው፡፡እንደ Swales (1990) አስተያየት ተግባቦታዊ ሁኔታዎች ቋንቋ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ሚና እንዲጫወት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ተግባቦታዊ ሁነቶች የሚከሰቱበት ሁኔታ ይለያያል፡፡ ይኸውም ተግባቦታዊ አገልግሎት በሚገኙባቸው ቦታዎች መካከል ልዩነት ይታያል፡፡ ተግባቦታዊ ሁነቶች በንግግር ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ የንግግሩን ሚና እና አካባቢያዊ እንዲሁም ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነቶችንም ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው፡፡

2. ተግባቦታዊ ሁነቶች የተግባቦትን አላማ የዘውግን ግብ ለማሳካት ያገለግላሉ፡፡ እንደ Swales (1990) አገላለጽ አላማን መለየት ቀላል ጉዳይ አይሆንም፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ተግባቦታዊ ዓላማዎች ግልፅ ይመስላሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ ዘውግ ለምሳሌ፡- በጦርነት ውስጥ የሚሰጥ ጋዜጣዊ መግለጫ ከአንድ በላይ ዓላማ ሊኖረው ይችላል፡፡ በዚሁ መሰረት አንዳንድ ዘውጎች ከአንድ በላይ ተግባቦታዊ ዓላማ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለምሣሌ የቴሌቭዥን ማስታወቂያ የአግባቢነት ሚና፣አጀንዳ የመቅረጽ እና ለግንኙነት መልካም እይታን ለመፍጠር የሚያግዙ ዓላማዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

3. የዘውግ ምሣሌዎች መሰረታዊ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለተግባቦታዊ ዓላማ የዘውግ አባላትን ማፍራት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የተወሰኑ የዘውግ አባላትን ለመመስረት ተጨማሪ ገፅታዎች ያስፈልጋሉ፡፡Swales እንዳቀረቡት እነዚህን አቀራረቦች ከተለያዩ ገለፃዎች አንፃር መመልከት ይኖርብናል፡፡ በየዕለቱ በተግባር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙናል፡፡ ለምሳሌ፡- አትክልትና የቤት ዕቃዎችን ተሸከርካሪዎችን ወዘተ ለመግለጽ አስቸጋሪ ሊሆንብን ይችላል፡፡

4. ዘውግ ይዘት፣ ካለበት ሁኔታ እና ከቅርፅ አንፃር ሰፊ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡ Swales እንዳብራሩት የዘውግ ዓላማ በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ይህ ተቀባይነት ምክንያታዊነትን ሲያመለክት በተመሣሣይ በስምምነቶች ላይ የሚፈጠሩ እንቅፋቶችን ይቃወማል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች ቀስ በቀስ እያደጉ የሚሄዱ

ናቸው። የሣሙና እና የዱቄት ማስታወቂያ በምሳሌነት ብንወስድ፡- የማስታወቂያው ዓላማ በግልጽ ተቀባይነት ያለው እና የማስታወቂያው ስምምነት ቅርፅ በማስታወቂያው ጣልቃ መግባትን ለመቀነስ ይሞክራል። ምክንያቱም ስምምነቶች በተጣሱ ቁጥር የዘውግ ተግባቦት ዓላማም እየቀነሰ ይሄዳል። በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚሰጠው የቃላት ስያሜ ለዘውግ ጠቃሚ ነው። በዘውግ ውስጥ ያለ የስምምነት ዕውቀት በጊዜያዊነት ተሳትፎ ከሚያደርጉት ይልቅ ባለሙያ ሆነው በዘውግ ላይ የሚሳተፉ የበለጠ ጠቃሚ ናቸው። ተማሪው በሚገኝበት ማህበረሰብ የተለያዩ ተግባቦታዊ ሁነቶች ማለትም ገለፃ፣ንግግር፣ ወርክሾፕ፣ ቱቶሪያል ፣ ሴሚናር ወዘተ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

## 2.3 የቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት

በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ትምህርትን አስመልክቶ የተለያዩ የመማሪያ ክፍሎችን ተተኳሪ ያደረጉ ጥናቶች ተካሂደዋል። በዚህ ክፍሎች ለማሳየት የተፈለገው ከአሁን በፊት በሀገር ውስጥ የተሰሩ ሥራዎች ከርዕሳቸው፣ ከአላማቸው፣ ከአጠናን ዘዴያቸውና ከጥናቱ ውጤት ትንታኔያቸው አኳያ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያላቸውን ልዩነትም ሆነ ተመሣሣይነት ነው። ይኸውም እንደሚከተለው ተጠናቅሮ ቀርበዋል። በተዘዋዋሪ ከሚመሳሰሉት ሥራዎች ውስጥ ተመስገን ፈቀደ (2001) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ብልሃት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል። የጥናቱ ዓላማ የ11ኛ ክፍል መምህራን የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ነው። በዚህም በአንድ በኩል የመምህራኑን የማስተማር ዘዴ ከፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች አኳያ መመርመር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መፈተሽ ነው። ይህንን ጥናት ከተመስገን ፈቀደ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር የሚያመሳስለው የሁለቱም ጥናቶች መሰረት ፅህፈት መሆኑና በፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ማተኮራቸው ነው። ከዚህ ውጭ ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩባቸው መሰረታዊ ነገሮች አሉ። ይኸውም ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የመምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን መገምገም ሲሆን የተመስገን ፈቀደ

ጥናታዊ ጽሁፍ ግን የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ከመምህራኑ የማስተማር ዘዴ ጋር ያለውን ዝምድና ይመለከታል፡፡ ከዚህም ሌላ ሁለቱ ጥናቶች ካላቸው ዓላማ የተነሳ በክፍል ደረጃ፣በአጠናን ዘዴ፣በጥናቱ ቦታና በተጠኚዎች አይነትና መጠን ይለያያሉ፡፡

ይህንን ጥናት ከእነዚህ ጥናቶች ጋር የሚያመሳስለው በጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ማተኮሩ ነው፡፡በዋናነት ጥናቱ የሚለየው በክፍል ደረጃ፣በቦታ፣ በተተኳሪ መጠን፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፣ የጥናቱ ዘመንና ዓላማ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስልና በክፍል ውስጥ ስለመጠቀም አለመጠቀማቸው እንዲሁም በትምህርቱ ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ ማመልከት ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚፈልግ በመሆኑ ነው፡፡

በተዘዋዋሪ ከሚመሳሰሉት ስራዎች መካከል ግርማ ገብሬ (1990) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ተቋም አማርኛን በማስተማር (Team) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡" በአማርኛ ድርሰትን የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብራዊ ስልት" (interactive approach) ተግባራዊነትና ውጤታማነት" በሚል ርዕስ ሙከራዊ ጥናት አድርገዋል፡፡

ግዛቸዉ በላይ (1991) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዩጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍ ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ " ከዘጠነኛ እስከ አስራ አንደኛ ክፍሎች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብ" በሚል ርዕስ ከዘጠነኛ እስከ አስራ አንደኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ መጽሀፍት ዝግጅት ውስጥ የጽህፈት ክሂል አቀራረብ በሂደታዊ የጽህፈት ክሂል በማስተማሪያ ዘዴ የሚቀርቡ ቢሆን የተሻለ ውጤት ያስገኛል በሚል አላማ ጥናት አካሂደዋል፡፡

በጥናቱም ያገኙት ውጤት በመማሪያ መጽሀፍት የሚቀርቡት መልመጃዎች በሂደታዊ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ቢቀርቡ ለጽህፈት ክሂል መዳበር ጥሩ ውጤት የሚያስገኙ ይሆናል፡፡ ይህ ጥናት በቀጥታ የሚመሳሰለው ጥናታዊ ጽሁፍን ስንመለከት የሰይድ ይመር (1993) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ተቋም አማርኛን በማስተማር (Team) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ርዕስ በዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ መማሪያ

መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች የማስተማሪያ ስነ- ዘዴ ትግበራ። በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡

የጥናቱ አላማ የጽህፈትን ክሂል ለማዳበር የተመረጡትን ይዘቶች ለማስተማር መምህራን የሚጠቀሙባቸው የማስተማር ስነዘዴዎች አተገባበር ምን እንደሚመስል መገምገምና በተማሪዎች ችሎታ ላይ ያለውን አንድምታ መግለጽ ነው።በጥናቱ ያገኙት ውጤት የሚያመለክተው ጽህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት የሚቀርቡት ይዘቶችና መልመጃዎች እንዲሁም ክሂሉን ለማዳበር ሥራ ላይ የሚውሉት ስነ-ዘዴዎች ትግበራ ፅህፈትን የማያለማምዱና ለክሂሉ መዳበር አስተዋጽኦ የሌላቸው መሆናቸውን ነው።

በሙሉዬ (2009) ‹‹የተማሪዎች የአንቀጽ አፃፃፍ ተገቢነትና ግንዛቤ›› በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቧል። የጥናቱ ዋና አላማም በየትኖራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን የአንቀጽ አፃፃፍ ተገቢነትና ግንዛቤ መመርመር የሚል ሲሆን በአንቀጽ መፃፍ ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በመጠናዊ የትንተና ስልትና ከቃለ መጠይቅና ክፍት ጥያቄዎች የተገኙት መረጃዎች ደግሞ በአይነታዊ የትንተና ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። በመሆኑም በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳው የተማሪዎች የአንቀጽ አፃፃፍ ስርዓት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ የሆነበት ምክንያትም የትምህርቱ አቀራረብም በንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፣ተማሪዎች ስለ አንቀጽ ግጥምጥምነት፣የሀሳብ አንድነትና የሀሳብ አጽንኦት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን የጽህፈት መለማመጃዎች የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያላስገቡ መሆናቸው ሲገልጽ በመጨረሻም ጥናቱ የመፍተሄ ሀሳብ ይሆናሉ ያላቸውን ሀሳቦች አስቀምጧል።

ሰለሞን ዮሐንስ (1991) በአድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን ለ2ኛ ድግሪ ማሟያ የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅና የመምህራኑ የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል።የጥናቱ ዓላማ በሀዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ስትራቴጅና መምህራን በሚስተምሩበት ዘዴ መካከል ያለውን ግንኙነት መፈተሸ ነው።ይህ አዲስ የሚጠናው ጥናት ከሰለሞን ዮሐንስ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የመምህራንን የማስተማር ዘዴዎች መመልከቱ ሲሆን ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩበት ደግሞ የሰለሞን

ዮሐንስ ጥናት በሀዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ እና 10ኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የሚካሄድ ነው፡፡ ሌላው የሰለሞን ዮሐንስ ጥናት የተማሪዎችን የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅ ከመምህሩ የማስተማር ዘዴ ጋር ያለውን መጣጣም የመረመረ ሲሆን ይህ ጥናት የመምህራንን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን መገምገም ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ አጠናን ዘዴ

ይህ ክፍል የጥናቱን ፍተሻ ሥራ ከዳር ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የመረጃ ምንጮች የጥናቱ ስልት፣የናሙና አመራረጥ ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደትና የጥናቱን አተናተን ስልት በዝርዝር የሚቀርብበት ነው፡፡

## 3.1 የጥናቱ ስልት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በተመረጡ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን መገምገም ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመው አይነታዊ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ አይነታዊ ምርምር በገለፃና በአሃዝ የመረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኚው ለሚገልፀው የመረጃ ትንተና አመቺ ሆኖ ስላገኘው ተመርጧል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

የዚህ ንዑስ ክፍል ዓላማ የጥናቱ ናሙና እንዴት እንደተመረጠ መግለጽ ነው፡፡ስለሆነም የጥናቱ ቦታና የጥናቱ ተሳታፊዎች በምን ዓይነት የንሞና ዘዴ እንደተመረጡ ተብራርቷል፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺ ናሙናነት ሲመረጡ እነሱም ካንቻሜ፣ ሼሌ፣ ሻራ፣ ጫኖ እና ላንቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት ምክንያት ሌሎቹ ከቦታና ከጊዜ አንጻር አመቺ ባለመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም በዛ ያሉ የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል ምድቦች የያዘ መሆኑና ብዛት ያላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መኖር ሌላው ትኩረት

እንዲሰጠው ያደረጉ ጉዳዮች ናቸው። ስለዚህ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል በአመቺ ናሙና እንዲመረጡ ተደርጓል።

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ አምስት የተመረጡት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በርካታ ተማሪዎችን የሚያስተናግድ ነው። በመሆኑም የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ከፍ እያሉ በሚሄዱበት ጊዜ ትምህርቱ እንዳይከብዳቸው መሰረት የሚይዙበት በመሆኑ እና ለጥናቱ አመቺ በመሆናቸው በአመቺ ናሙና አመራረጥ ተመርጠዋል።

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በ2014 ዓ.ም በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ወረዳ በተመረጡ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የዚህ ጥናት አካል ሆነዋል። በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ትምህርት ቤቶች በጠቅላይ ናሙና ዘዴ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳሪ ሆነዋል። መምህራኑ በቁጥር አምስት ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ ወንድ ሶስት እና ሴት ሁለት ናቸው። አምስቱም የዚህ ጥናት አካል ሆነዋል።

### 3.2.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት ትምህርት ቤቶች ማለትም ከአምስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ አርባ ሰባት አርባ ሰባት ተማሪዎች ከሚማሩ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ረድፋዊ የናሙና ዘዴን በመምረጥ ሁለት መቶ ሠላሣ አምስት ተማሪዎች ተመርጠው የጥናቱ አካል ይሆናሉ። የናሙና አወሳሰዱም ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል። በሃያ አምስቱ የዘጠነኛ ክፍል እና የአስረኛ ክፍል ምድቦች በእያንዳንዳቸው ከስድሳ እስከ ስድሳ ስምንት ተማሪዎች በአንድ እንደሚማሩ በተወሰደው ትክክለኛ መረጃ መሰረት ከተማሪዎች የስም መቆጣጠሪያ በማረጋገጥ ከእያንዳንዱ ክፍል ከዘጠኝ እስከ አስር ተማሪዎች ማለትም በስም መቆጣጠሪያው ሰባት ሰባት የረድፍ ርቀት ወሳኝ ቁጥርን በማለፍ ምርጫ ተካሂዷል።

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለጥናቱ ከተመረጠው ርዕስ ጋር ያላቸው ተጣጥሞና ጥንካሬ የጥናቱን መረጃ ተአማኒነት ከፍ በማድረግ ረገድ ድርሻው ላቅ ያለ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም በተመረጡ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን የጽህፈት ትምህርት ሲያስተምሩ የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች ግምገማ ለማካሄድ ምልከታ እና የጽሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት ውለዋል፡፡

### 3.3.1 ምልከታ

ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ አተኩረው የሚካሄዱ ምርምሮች ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተመራጭ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ መሆኑን (Van 1988) ይጠቁማሉ፡፡ ተመራማሪው በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ሊያገኝ የሚችለውን ተፈጥሯዊ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ድባብ ተከታታይ በሆነ የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ምልከታው የሚካሄደው መምህራን የፅህፈት ትምህርት የሚሰጡበትን ጊዜ ከትምህርት ዕቅዳቸው ላይ አስቀድሞ በማየትና የጊዜ መርሀ ግብር በማዘጋጀት ነው፡፡ ከምልከታው አስቀድሞ የመከታተያ ቅፅ ተዘጋጅቶ ምልከታውም ለሶስት ተከታታይ ጊዜያት ተደርጓል፡፡ የጥናቱን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚመልሱ ሀሳቦችም ተካተዋል፡፡

### 3.3.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያግዛል ተብሎ በመታሰቡ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የጽሁፍ መጠይቆች ለተማሪዎቹም ሆነ ለመምህራን በማዘጋጀት በምልከታ የሚገኘውን ውጤት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ የተዘጋጁት ጥያቄዎች የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መመለስ የሚያስችሉ እንዲሆኑ በጥልቀት ታስቦበታል፡፡ የጥያቄዎቹ ዓይነት ምርጫና ገለፃ ሲሆን ቁጥራቸው ልምድ ያላቸውን ሌሎች ባለሙያዎችን በማስገምገምና በማወያየት ጭምር ተዘጋጅቷል፡፡

## 3.4 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤት አጥኚው በአካል በመገኘት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያስተምሩበትን የክፍል ምድብና የክፍለ ጊዜ ድልድል በመመልከት፣ ከመምህራኑ ጋር ውይይት በማካሄድ ምልከታውን ለማካሄድ አመቺ የሆኑ ክፍለ ጊዜያትን በመወሰን መረጃ ይሰበሰባል፡፡ የክፍል ምልከታው የሚካሄደው ለአንድ ወር ጊዜያት በድግግሞሽ ሲሆን መሠረት የሚያደርገው በተዘጋጀው የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ የሠፈሩትን የመገምገሚያ ነጥቦች ነው፡፡

ከዚህም ሌላ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚዘጋጀው የፅሑፍ መጠይቅ ከትምህርት ቤቱ ለተመረጡት ተተኳሪ ተማሪዎችና መምህራን ተበትኖ እንዲሞላ ይደረጋል፡፡ ውጤቱም ተተንትኖ ይቀርባል፡፡

## 3.5 የመረጃዎች አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ (QUALITATIVE RESEARCH) የምርምር ዘዴን ይከተላል፡፡ ጥናቱ ቃኚን (SERVEY) ስልትን የተከተለም ነው፡፡አይነታዊ ምርምር አካሄድን የመከተሉ ምክንያት ከጥናቱ ርዕስ ወይም አብይ ዓላማ የሚመነጭ ነው፡፡መረጃዎችን ለመተንተን ደግሞ ገለፃ ይጠቀማል፡፡ ከተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታና ከጽሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች በመነሳት በዓላማው ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ትንተና ይካሄዳል፡፡ ትንተናው ከመረጃዎች ብዛትና ስፋት አኳያ በየክፍሉ ይደራጃል፡፡ በክፍል ውስጥ በተከታታይ ምልከታ የተገኘው መረጃ በገለፃ የሚተነተን ሲሆን ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ በሚያነሳው መሰረታዊ ጉዳይ ተለይቶ በሠንጠረዥና በመቶኛ ስሌት ይተነተናል (ያለው እንዳወቀ 2007)፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በምዕራፍ አንድ ስር እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የክፍል ውስጥ ምልከታና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች የጥናቱን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ይተነተናሉ፡፡

## 4.1 መምህራን የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማስተማር ስነ ዘዴ ምንድን ነው?

### 4.1.1 የተተኳሪ መምህራንና የተማሪዎች አጠቃላይ ዳራ

**ሠንጠረዥ 1፡- የተተኳሪ መምህራን አጠቃላይ ዳራ**

| የተጠኚ ብዛት | ዕድሜ | | የአገልግሎት ዘመን | | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት መስክ | | የሙያ ማሻሻያ | የክፍለ ጊዜ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 23-29 | 30-35 | 1-5 | ከ5 በላይ | ዲግሪ | አብይ አማርኛ | ንዑስ እንግልዘኛ | ተከታታይ ኮርስ (CPD) | ከ15-20 | ከ20 በላይ |
| በቁጥር | 3 | 2 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 2 |
| በመቶኛ | 60% | 40% | 20% | 80% | 100% | 100% | 100% | 100% | 60% | 40% |

በሰንጠረዥ (1) ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ከእድሜ አንፃር ሶስቱ መምህራን ከ 23-29 የዕድሜ ክልል ውስጥ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ከ30-35 ዕድሜ ክልል ውስጥ ናቸው፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸውን በተመለከተ አንድ መምህር ከ1-5 አገልግሎት ሲኖረው አራቱ ደግሞ ከአምስት ዓመት በላይ አገልግሎት አላቸው፡፡ የስልጠና ሁኔታ በተመለከተ ሁሉም መምህራን አብይ የትምህርት ዘርፍ አማርኛ፣ በንዑስ እንግሊዘኛ በድግሪ መርሀ ግብር የተመረቁ ናቸው፡፡ ሁሉም መምህራን የስራ ላይ ስልጠና ስለመውሰዳቸው ተጠይቀው በተከታታይ ኮርስ (CPD) ብቻ የሚሰለጥኑ ሲሆን ከዚህም ሌላ ምንም አይነት ስልጠና የወሰዱ አለመሆኑን ከምላሻቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ሁሉም መምህራን በስራ ላይ እያሉ ስለ ማስተማር ዘዴዎች፣ስለ አዳዲስ የመማር ማስተማር ግኝቶች የተሰጣቸው ስልጠናም እንደሌለ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ሀሳብ አኳያ በመጠይቁ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው መምህራን በስራ ላይ እያሉ ከአዳዲስ የትምህርት ግኝቶች ጋር ለመተዋወቅ የሚያስችላቸውን ዕድል ያላገኙ በመሆናቸው በመምህራን ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ለመገመት ያስችላል፡፡ በዚሁ ሰንጠረዥ ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚጠቁመው የክፍለ ጊዜ ብዛትን በተመለከተ ሶስት መምህራን በአማካኝ በቀን ሦስት ክፍለ ጊዜ ሲያስተምሩ ሁለት መምህራን ደግሞ በቀን አራት ክፍለ ጊዜ እንደሚያስተምሩ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ከፍተኛ የክፍለ ጊዜ ብዛት ወይም የሥራ ጫና እንደሌለባቸው መገመት ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ 2 ተተኳሪ ተማሪዎች ከፆታ አንፃር**

| ምድብ/ት/ቤት/ | ወንድ | | ሴት | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1. /ሻራ 2ኛደ/ት/ቤት/ | 29 | 60.42% | 19 | 39.58% | 47 | 100% |
| 2. /ሸሌ 2ኛደ/ት/ቤት/ | 30 | 62.5% | 18 | 37.5% | 47 | 100% |
| 3. /ካንቻማ 2ኛደ/ት/ቤት/ | 23 | 50% | 23 | 50% | 47 | 100% |
| 4. /ጫኖ 2ኛደ/ት/ቤት/ | 27 | 57.44% | 20 | 42.55% | 47 | 100% |
| 5. /ላንቴ 2ኛደ/ት/ቤት/ | 23 | 48.55% | 23 | 51.45% | 47 | 100% |
| የምድብ ብዛት 5 | 132 | 56.97% | 103 | 43.03% | 235 | 100% |

ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ የተተነተኑት ተማሪዎች በናሙናነት ለመረጃ ሰጪነት የተመረጡት አጠቃላይ ካሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ መረጃውን በተቀላጠፈ መንገድ ለመሰብሰብ ያመች ዘንድ በአምስት ምድብ በመከፋፈል በውስብስብ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ውስጥ ረድፋዊ የናሙና አመራረጥን በመከተል ካሉት 5 ት/ቤቶች ውስጥ 235(100%) ተማሪዎች ተመርጠው የጥናቱ ናሙና ሊሆኑ ችለዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ተተኳሪ ተማሪዎች በአምስቱ ምድብ ት/ቤቶች ውስጥ ከፆታ አንፃር 132 (56.97% ) ወንዶች ሲሆኑ 103 (43.03%) ደግሞ ሴት ተማሪዎች ናቸው፡፡

### 4.1.2 የፅሁፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ በአምስቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው የተለያዩ የፅሁፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች እንዳሉ ተገልጸል፡፡ በመሆኑም በሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑት፣ሀሳብን ማፍለቅና ማደራጀት፣ ለማርቀቅ በተደጋጋሚ ረቂቅ መጻፍ፣ ያረቀቁትን ለመከለስ መሰረዝ፣ መጨመር፣ መቀነስና ደጋግሞ ሀሳብን ማደራጀት፣ ለማረም የቃላት መረጣን፣ የዓረፍተ ነገር አወቃቀርን፣ የአጻጻፍ ስርዓትን መረዳትና መከተል ላይ የሚያተኩር ሲሆን ውጤታዊ የጽህፈት አቀራረብ ደግሞ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ እየተከታተለ ደረጃውን ጠብቆ ተገቢ መልመጃዎችን በማዘጋጀትና በማለማመድ ከውስን መልመጃ ወደ ምር የጽህፈት ደረጃ አሸጋግሮ ከዚያም ከምር ወደ ነጻ የጽህፈት ደረጃ የሚያሳድግ ሲሆን ዘውግ ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ መምህራን በገሀዱ ዓለም ውስጥ የሚተገበሩትን ልዩ ልዩ የጽሁፍ አይነቶች ለምሳሌ፡- ልዩ ልዩ ዘገባዎች (ሪፖርቶች)፣የሥራ ደብዳቤዎች፣የህይወት ታሪኮች ወዘተ…በክፍል ውስጥ መልመጃነት እንዲለማመዱ የሚያበረታታ የአፃፃፍ ዘዴ ነው፡፡

በማስከተል በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት ሥነዘዴ ምንድን ነው? የጽህፈት ክሂል በክፍል ውስጥ ሲተገበር የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል? የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጉዳዮች ለመፈተሽ ከሁሉም

### 4.1.3 የፅሁፈት ትምህርት አቀራረብን ለመለየት የተደረገ የምልከታ ትንተና

በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ እንደ ውጤታማ አቀራረብ ከተጠናቀቀ የጽህፈት ረቂቅ ላይ እንዲሁም በቋንቋ ቅርጽ ላይ ከማተኮር ይልቅ አዲስ ነገር የመፈለግ፣ትርጉምን የማስፋት ሂደትን የሚከተልና በጽሁፍ ይዘት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ከዚሁ አንጻር ተተኳሪ በሆነው በምድብ 1 ተግባራዊ የነበረው የጽህፈት ትምህርት አቀራረብን ስንመለከት ከአጻጻፍ ደረጃዎች ቅድመ ጽህፈት ብቻ ተከናውኗል፡፡ በትምህርቱ ሂደት ርዕስ የመምረጥና አስተዋፅኦ የመንደፍ ተግባር ተፈጽሟል፡፡ የመከለስ ወይም የማቃናት ደረጃዎች ግን ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ በአብዛኛው የትምህርቱ አቀራረብ በተማሪዎች የመጨረሻ ሥራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ለጽህፈት ትምህርት መጎልበት የሚከናወኑ ተግባራት ሀሳብን ማፍለቅና ማደራጀት፣ ለማርቀቅ በተደጋጋሚ መጻፍ፣ያረቀቁትን ለመከለስ መሰረዝ፣መጨመር፣መቀነስ፣ ደጋግሞ ሀሳብን ማደራጀት ለማረም፣የቃላት መረጣን፣ የዓረፍተነገር አወቃቀርን መከተል ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ከዚህ ንድፈ ሀሳብ እውነታ አንጻር በምድብ 6 የተከናወነውን የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ሁኔታን ስንመለከት በአብዛኛው ገለጻን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በፅህፈት ትምህርቱ የተከናወነው የመጻፍና የመከለስ ደረጃዎች ናቸው፡፡ የቅድመ ጽህፈት ተግባርም ተከናውኗል፡፡

በምድብ 11 በተከታታይ ሶስት ምልከታዎች የተመዘገቡ መረጃዎችን ስንመለከት የጽህፈት ትምህርቱን ለማስተማር የቅድመ ጽህፈትና የማርቀቅ ደረጃዎች ተከናውነዋል፡፡ ርዕስ የመምረጥና አስተዋጽኦ የመንደፍ ተግባርም ተከናውኗል፡፡ ተማሪዎች በመከለስ ደረጃ ጽሁፉን ደጋግመው በማንበብ የማሻሻል ስራ እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡ በምድብ 16 በተከናወኑ ሶስት ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የጽህፈት ትምህርቱ በአብዛኛው በተማሪዎች የመጨረሻ ሥራ /ውጤት/ ላይ ያተኮረ ነው፡ ፡ በትምህርቱ ሂደት የማሰላሰል፣ የመከለስ ደረጃዎች አልተከናወኑም፡፡

በምድብ 21 በተከታታይ ሶስት ምልከታዎች የተመዘገቡ መረጃዎችን ስንመለከት የጽህፈት ትምህርቱን ለማስተማር የቅድመ ጽህፈትና የማርቀቅ ደረጃዎች ተከናውነዋል፡፡ ርዕስ የመምረጥና አስተዋጽኦ የመንደፍ ተግባርም ተከናውኗል፡፡ ተማሪዎች በመከለስ ደረጃ ጽሁፉን ደጋግመው በማንበብ የማሻሻል ስራ እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡

### 4.1.4 በጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የመምህራንን ሚና ለመለየት የተደረገ የምልከታ ትንተና

በዚህ ምድብ 1 መምህርቷ የተጠቀሙት ሥነ-ዘዴ ወደ ሂደታዊ ያዘነብላል፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ የመምህሩ ድርሻ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡ ፡ የመጻፍ ክሂልን ለማለማመድ የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብ ይተልማሉ፡፡ የጽህፈት ህጎችንና መርሆችን ያስተምራሉ፡፡ የክፍል ውስጥ ክንውኑን ለግለሰቦችና ለቡድኖች በማከፋፈል ሚዛናዊ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በምድብ 1 የመምህሩን ሚና በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው መምህርቷ የጽህፈት አጻጻፍ ደረጃዎችን አስተምረዋል፡፡

የአጨራረስ ሂደትን አሳይተዋል፡፡ ለተማሪዎች በክፍልና ከክፍል ውጪ የሚለማመዱበት መልመጃ አዘጋጅተዋል፡፡ ተማሪዎች አስተዋፅኦ እንዲያዘጋጁ አዘዋል፡፡ መምህርቷ በተማሪዎች ስራ ላይ ቃላዊ መጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡የተማሪዎችን ስራ ለማስተማሪያነት ተጠቅመዋል፡፡

መምህርቷ የጽህፈት ልምዶችንና መርሆችን አስተምረዋል የአፃፃፍ ሂደቱን አሳይተዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ለመለማመድ የሚያስችል መልመጃ አቅርበዋል የትምህርቱን ክንውን በቡድን ወይም በህብረት በመከፋፈል በውይይት እንዲሰሩ አድርገዋል፡፡ በተማሪዎች ስራ ላይ ቃላዊ መጋቢ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ /አባሪ ሀን ይመልከቱ/ በዚህ ምድብ 6 መምህርቷ የጽህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ በመጀመሪያ ለተማሪዎች የአፃፃፍ ሂደት ደረጃዎችን በቅደም ተከተል አብራርተዋል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች የሚጽፏቸውን ርዕሶችን በቡድን በመከፋፈል አድለዋል፡፡ ተማሪዎችም ጽሁፉን ከመጀመራቸው በፊት ቢጋር አንዲያዘጋጁ አዘዋል፡፡ ተማሪዎች ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግን መምህርቷ ቃላዊም ሆነ ጽሁፋዊ ምላሽ አልሰጡም፡፡/አባረ ለን ይመልከቱ፡፡

በዚህ ምድብ 11 መምህሩ የአፃፃፍ ሂደትን አላስተማሩም፡፡ ነገር ግን ለተማሪዎች ርዕስ በመስጠት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ትዕዛዝ አስተላልፈዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ለሚሰሩት ስራ ግን የጊዜ ገደብ አላሳወቁም፡፡

መምህሩተማሪዎች ስራቸውን እርስ በእርስ እንዲተራረሙ እና እንዲያስተካክሉ አላደረጉም፡፡ መምህሩ በተማሪዎች ስራ ላይ ቃላዊም ሆነ ጽሁፋዊ መጋቤ ምላሽ አልሰጡም፡፡ /አባሪ ሐን ይመልከቱ፡፡/

ተተኳሪ በሆነው ምድብ 16 መምህሩ የአፃፃፍ ሂደትን አላስተማሩም፡፡ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ እንዲጽፉ ዕድል ሰጥተዋል፡፡ የተማሪዎች ሥራ የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ አሳውቀዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የመፃፍ መልመጃዎችን አዘጋጅተዋል፡፡ የተማሪዎችን የመጨረሻ ስራ /ውጤት/ ላይ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ /አባሪ መን ይመልከቱ፡፡/

በዚህ ምድብ 21 መምህሩ የአፃፃፍ ሂደትን አላስተማሩም፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲለማመዱ መልመጃ አዘጋጅተዋል፡ የተማሪዎችን ሥራ ለተማሪዎች መማሪያ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ በውይይቱ እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች ድጋፍ አላደረጉም፡፡ መምህሩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰሩት ስራ ግን የጊዜ ገደብ አላሳወቁም፡

፡ መምህሩ ተማሪዎች ስራቸውን እርስ በእርስ እንዲተራረሙ አላደረጉም፡፡ መምህሩ በተማሪዎች የመጨረሻ ስራ ላይ ቃላዊም ሆነ ጽሁፋዊ መጋቤ ምላሽ አልሰጡም፡፡ /አባሪ ሰን ይመልከቱ፡፡/

## 4.1.5 በጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ሚና ለመፈተሽ የተደረገ የምልከታ ትንተና

በጽህፈት ትምህርት ወቅት ተማሪዎች ጽህፈትን በተገቢው መንገድ እንዲለማመዱና በሚያዘውና በተዘጋጀው መመሪያና ደንብ መሰረት ሰፊ እድል ተመቻችቶላቸዋል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የሚጠየቁት ለጽሁፋቸው የሚሆን በራሳቸው ርዕስ እንዲመርጡ እድሉ ተሰጧቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በተተኳሪው ምድብ 1 ተማሪዎች በትምህርቱ ተግባራዊነት ከመጻፍ ደረጃዎች ቅድመ ጽህፈት ተግባራትን ርዕስ የመምረጥና አስተዋጽኦ የመንደፍ ተግባርን አከናውነዋል፡፡ የመከለስ ደረጃንም በተግባር አከናውነዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች የሠሩትን ስራ ደጋግመው እንዲያርሙና እንዲያሻሽሉ እድል አግኝተዋል፡፡ በትምህርቱ ሂደት የተማሪዎች ሚና በተወሰነ ደረጃ ጎልቶ የታየበት ሂደት ነው፡፡

በምድብ 6 ተማሪዎች የመምህሩን ገለጻ በማዳመጥ ማስታወሻ ይዘዋል፡፡ ለሚጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በመጻፍ ሂደት አስረጂ ጽሁፍ ጽፈዋል፡፡ የቡድን ስራቸውን እርስ በእርስ በመተራረም ለቢጤዎቻቸው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻም የመከለስ ደረጃን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ በምድብ 6 ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ደረጃን በመጠኑ ቢሆን ለመተግበር ሙከራ አድርገዋል፡፡

ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ተሳትፎ አላደረጉም፡፡ መምህሩ በመረጠው ርዕስ ላይ ብቻ ጽሁፋቸውን አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ አቅርበዋል፡፡ መምህሩም ተማሪዎች ባቀረቡት ስራ ላይ ጽሁፋዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ በምድብ 11 ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎች የአጻጻፍ ደረጃዎችን ሳይከተሉ የጽህፈት ትምህርቱን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

ምድብ 16 በተደረጉ ሶስት ተከታታይ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱ ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ የመጻፍ ተግባርን ብቻ አከናውነዋል፡፡ በትምህርቱ ሂደት የማሰላሰል ደረጃን እና የመከለስ ደረጃን በተግባራዊ ስራቸው ሲያከናውኑአልተስተዋሉም፡፡

አጠቃላይ መረጃው እንደሚያመለክተው በጽህፈት ትምህርቱ ተማሪዎች የአፃፃፍ ሂደትን በማወቅ ለመተግበር ሙከራ አለማድረጋቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ በሚሰሯቸው ረቂቆች ላይ ሀሳብ ማመንጨትና የይዘት መልሶ ምገባ እንዲያገኙ አያደርጋቸውም፡፡ በትምህርቱ ክንውንም አዲስ ነገር የመፈለግ፣ የመፍጠር ክህሎት እንዲኖራቸው ስለማያስችላቸው ተጽፎ ያለቀለትን ጽሁፍ ይዘን ከምናስተምራቸው ተጽፎ ባላለቀለት ጽሁፍ በሂደት ላይ አተኩረን ተማሪዎችን ልናስተምራቸው እንደሚገባ ምሁራን ይመክራሉ፡፡ ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ የጎላ ተሳትፎ አላደረጉም፡፡ በመረጡት ርዕስ ላይ በቡድን የሰሩትን በክፍል ውስጥ አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ የመከለስ የማረምና የማስተካከል ሂደቲችን ሲያልፉ አልታዩም፡፡

በዚሁ በምድብ 21 ውስጥ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው ተማሪዎች የፅህፈ ት ትምህርቱን ሂደት በሂደት እየተማሩ እንዳልሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 4.1.6 ከመምህራን መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.1.6.1 ፅህፈትን በማስተማር የመምህራን የትኩረት አቅጣጫ

መምህራን ድርሰትን ለማስተማር ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ዘዴ በተመለከተ ለመምህራን ከቀረበ ልቅ ጥያቄ የተገኘው መረጃ ድርሰትን በማስተማር ረገድ አንድ መምህር ሂደት ተኮር ሥነ-ዘዴን እንደሚጠቀሙበት ሲገለጹ አንድ መምህር ደግሞ ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮርን በማቀያየር እንደሚጠቀሙ ቀሪ ሦስት መምህራን ደግሞ ውጤት ላይ በማተኮር በተማሪዎች የመጨረሻ ስራ ላይ ትኩረት በማድረግ የሚያስተምሩ መሆኑን ከመረጃው መንዘብ ይቻላል፡፡ ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው በአብዛኛው ተጠኚ መምህራን የሚያተኩሩትና የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ሀሳባቸውን አፍልቀው በጽሁፍ መግለጽ እንዲችሉ የሚያበረታታ ሳይሆን የቋንቋውን ስርዓት ትክክለኛነት ለማሳወቅ የሚያስችል ዘዴ ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡ ተማሪዎች ርዕስ መርጠው ሀሳብ አፍልቀው መጻፍ የሚችሉትን ዘዴ በማመቻቸት ተማሪዎች በተግባራዊ

ሂደት በማሳተፍ የማስተማር ግንዛቤ እና ልምድ እንደሌላቸው ከምላሻቸው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

**ሠንጠረዥ 3 ጽህፈትን በማስተማር ረገድ የመምህራን የትኩረት አቅጣጫ በተመለከተ ከመምህራን የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ አደርጋለሁ | | አልፎ አልፎ አደርጋለሁ | | አላደርግም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በትምህርቱ ሂደት የአጨራረስ ሂደትን ያስተምራሉ ? | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |
| 2 | ጽህፈትን ሲያስተምሩ በቃላት አገባብ ትክክለኛነት ላይ ያተኩራሉ ? | 3 | 60% | 1 | 20% | 1 | 20% |
| 3 | የጽህፈትን ትምህርት ሲያስተምሩ በአብዛኛው የሚጠቀሙት ዘዴ ውጤት ተኮር ነው? | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |
| 4 | ተማሪዎች ጽህፈት በሚጽፉበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለተማሪዎች ይጠቁማሉ ? | 1 | 20% | 4 | 80% | - | - |
| 5 | በጽህፈት ትምህርት ሂደት መምህሩ በአብዛኛው በማቃናትና በማረም ላይ ያተኩራሉ? | 1 | 20% | 3 | 60% | 1 | 20% |

ከሠንጠረዥ (3) መገንዘብ እንደሚቻለው ለጥያቄ 1(20%) መምህራን ሁልጊዜ ጽህፈትን ሳስተምር የአጨራረስ ሂደትን አስተምራለሁ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 1(20%) አልፎ አልፎ የጽህፈት ሂደታዊ ደረጃዎችን እንደሚያስተምሩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 3(60%) ደግሞ የአጨራረስ ሂደትን እንደሚያስተምሩ መረጃው ይጠቁማል፣ ይህም ማለት በጽህፈት ትምህርት ክፍል ጊዜ ፈጽሞ የአጨራረስ ሂደትን እንደማያስተምሩ ምላሹ ያሳያል፡፡

በጥያቄ 2 ምላሽ መሠረት 3(60%) መምህራን ጽህፈትን ሲያስተምሩ በቃላት አገባብ ትክክለኛነት ላይ ሁልጊዜ እንደሚያተኩሩ ምላሽ የሰጡ ሲሆን 1(20%) አልፎ አልፎ ጽህፈትን ሲያስተምሩ በቃላት አገባብ ትክክለኛነት ያተኩራሉ፡፡ ቀሪ 1(20%) ግን በጽህፈት ትምህርት በቃላት አገባብ ትክክለኛነት ላይ አተኩረው የሚያስተምሩ አለመሆኑን የሰጡት ምላሽ ይጠቁማል፡፡

ለጥያቄ 3 በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በዚሁ ጥያቄ ስር ለቀረበው መምህራን የሰጡት ምላሽ ደግሞ 3(60%) ጽህፈትን ለማስተማር ትኩረት አድርገው የሚያስተምሩ ተማሪዎች በሚያቀርቡት የመጨረሻ ውጤት ላይ እንደሆነ ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ይቻላል፡1 (20%) ደግሞ ውጠየት ተኮርን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙት ያሳያል፡፡ ቀሪ 1(20% ) ግን ጽህፈትን ለማስተማር ውጤት ላይ አተኩረው እንደማያስተምሩ መረጃው ይጠቁማል፡፡

በዚህ ሠንጠረዥ ከጥያቄ 4 ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ከተጠኚ መምህራን 1(20%) ለተማሪዎች ጽህፈት በሚጽፉበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ሁልጊዜ እንደሚጠቁሙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ 4(80%) ደግሞየተማሪዎችን ችግር ለተማሪዎች የመጠቆም ተግባር አልፎ አልፎ እንደሚያከናውኑ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አብዛኛውን ጊዜ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በራሳቸው እንዲፈቱ እድል የሚሰጧቸው አለመሆኑን ይጠቁማል፡፡

ለጥያቄ 5 መምህራን በሰጡት ምላሽ በጽህፈት ትምህርት ሂደት ሁልጊዜ የተማሪዎችን ስህተት በማረምና በማቃናት ላይ የሚያተኩሩ 1(20%) ሲሆኑ 3(60%) ደግሞ የተማሪዎችን ስህተት አልፎ አልፎ የማረምና የማቃናት ስራ ይሰራሉ ፡፡ ቀሪ 1(20%) በጽህፈት ትምህርቱ የተማሪዎችን ስህተት የማረም ተግባር የማያከናውኑ ናቸው፡፡ ይህ የሚያሳየው ሶስት መምህራን ተማሪዎች ጽህፈት ሲጽፉ የሚፈጥሩትን ችግር ለማረም ጥረት የሚያደርጉ ሲሆን አንዱ መምህር ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲተራረሙ እድል የሚሰጡ ናቸው፡፡

### 4.1.7 ጽህፈትን በማስተማር ረገድ የመምህሩ ኃላፊነት

**ሠንጠረዥ 4፡- ፅህፈትን ለማስተማር የመምህሩ ኃላፊነት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ አደርጋለሁ | | አልፎ አልፎ አደርጋለሁ | | አላደርግም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 6 | የጽህፈት ህጎችን፣የአጻጻፍ ስልቶችን ያስተምራሉ ? | 1 | 20% | 3 | 60% | 1 | 20% |
| 7 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣የፈጠራ ስራና ወዘተ ተወያይተው እንዲጽፋ ይበረታታሉ? | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |
| 8 | ተማሪዎች ጽህፈትን ሲጽፋ እርስ በርሳቸው እንዲያርሙ ያለማምዷቸዋል? | 1 | 20% | 3 | 60% | 1 | 20% |
| 9 | ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድ ተነስተው የሚጽፋበት ርዕስ እንዲፈልጉ ያበረታታሉ? | 1 | 20% | 3 | 60% | 1 | 20% |
| 10 | ተማሪዎች ጽህፈት ሲጽፋ የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ያሳውቃሉ? | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |

በሰንጠረዥ 4 በጥያቄ 6 ላይ እንደተመለከተው የድርሰት ህግጋትና ልምዶች የጽሁፍ መርሆችን ሁልጊዜ አስተምራለሁ የሚል ምላሽ የሰጡ 1(20%) ሲሆኑ 3(60%) ደግሞ አልፎ አልፎ ተግባራዊ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡ ቀሪ 1(20%)ቱ ደግሞ በድርሰት ትምህርት የድርሰት መርሆችንና ልምዶችን የማይተገብሩ መሆኑን ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል ፡፡

በጥያቄ 7 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣ የፈጠራ ስራና ወዘተ ተወያይተው እንዲጽፉ ሁልጊዜ የሚያበረታቱ 2(40%) ናቸው፡፡ 3(60%) ደግሞ በክፍል ውስጥ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣የፈጠራ ስራ የመሳሰሉትን ጽሁፎች አልፎ አልፎ እንዲጽፉ የሚያበረታቱ ናቸው ፡፡

ለጥያቄ 8 በድርሰት ትምህርት ተማሪዎች ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ሁልጊዜ ጥቆማ የሚያደርጉ 1(20%) ሲሆኑ 3(60%) አልፎ አልፎ የሚተገብሩ ሲሆን 1(20%) ግን በድርሰት ትምህርት ተማሪዎች በራሳቸው ስህቶቻቸውን እንዲለዩ የሚያደርጉ ናቸው፡ ፡ በዚሁ ሰንጠረዥ በጥያቄ 9 ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ከራሳቸው ልምድና እውቀት ተነስተው ርዕስ እንዲፈለጉ ሁልጊዜ የሚያበረታቱ 1(20%) ናቸው። 3(60%) ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ የመፈለጉን ተግባር እንዲያከናውኑ አልፎ አልፎ ዕድል የሚሰጡ ናቸዉ ቀሪ 1(20%) ደግሞ በፍጹም ዕድል የማይሰጡ ናቸው። ይህ

የሚያሳየው አንድ መምህር ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ሀሳባቸውን በማሰባሰብ የማሰላሰል ደ ረጃን እንዲተገብሩ የማበረታታቱ ሁኔታ ውሱኑነት ያለበት መሆኑን ያስገነዝበናል።

በጥያቄ 10 ለቀረበው ምላሽ ደግሞ ጽህፈትን ከማስተማር አኳያ ተማሪዎች ድርሰትን ሲጽፉ ስራቸው የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ሁልጊዜ የሚያሳውቁ 1(20%) ሲሆኑ1 (20%) ደግሞ አልፎ አልፎ የጊዜ ገደብን የማሳወቅ ተግባር ያናውናሉ። ቀሪ 3(60%) ግን ተማሪዎች ድርሰትን በሚጽፉበት ጊዜ የጊዜ ገደብን ወስነው የማይናገሩ መሆኑን ከምላሻቸው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ይህ የሚያሳየው መምህራን በድርሰት ትምህርቱ ያላቸውን ኃላፊነት በተገቢው ሁኔታ እየተወጡ አለመሆኑን ነው።

### 4.1.8 የመምህራን የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች

ሰንጠረዥ 5 ከመምህራን የፅሀፈት የማስተማሪያ ዘዴዎች አኳያ

ከመምህራን የተገኘ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ አደርጋለሁ | | አልፎ አልፎ አደርጋለሁ | | አላደርግም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 11 | ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ እንዲጽፉ በርዕሰ ጉዳዩ ከብጤዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ ያበረታታሉ ? | 1 | 20% | 4 | 80% | - | - |
| 12 | በድርሰት ትምህርት ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ስለሚጽፉት ርዕስ፣ይዘት፣አላማና ተደራሲ ወስነው ይናገራሉ? | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |

በሰንጠረዥ 5 በጥያቄ 11 ተማሪዎች የጽህፈት ስራ እንዲሰሩ በሚደረግበት ጊዜ በመረጡት ርዕስ እንዲጽፉና ከብጤዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ እድል የሚሰጡ 1(20%) ሲሆኑ 4(80%) ደግሞ ተማሪዎች ተወያይተው እንዲጽፉ የሚያበረታቱት አንዳንዴ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴን በተመለከተ መምህራን ጽህፈትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ፣ በመረጡት ርዕስ ዙሪያም ከብጤዎቻቸው ጋር ተወያይተው ድርሰት እንዲጽፉ በአጠቃላይ ሂደታዊ ስነ ዘዴን የሚያበረታቱና የሚያግዙ ስለመሆናቸው ቢገልጹም ከምልከታው የተገኘው መረጃ ግን አንድ መምህር ብቻ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በጥያቄ 12 ላይ እንደተገለጸው ጽህፈትን ከማስተማር አኳያ በድርሰት ትምህርት ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ስለሚጽፉት ርዕስ፣ ይዘት፣ አላማና ተደራሲ ለማሪዎች ወስነው የሚያሳውቁ 2(40%) ሲሆኑ 3(60%) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚያሳውቋቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡ ይህ የሚያመለክተው በአብዛኛው ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ የመምረጥና ዓላማን የመወሰን ደረጃን ሁልጊዜ ተግባራዊ አለማድረጋቸውን ነው፡፡ ለዚህም

(Mrra፣1982) የተባሉ ምሁር በድርሰት ትምህርት ሂደት ለጥሩ አተገባበር የተማሪው ኃላፊነት ስለሚጽፍበት ርዕስ ዓላማና ተደራሲ መወሰን እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡

**ሰንጠረዥ 6 ፅህፈትን ለማስተማር መከናወን ያለባቸው ተግባራት**

**ከመተግበር አኳያ ከመምህራን የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ አደርጋለሁ | | አልፎ አልፎ አደርጋለሁ | | አላደርግም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 13 | ተማሪዎች አንድን ነገር ተመልክተው ወይም አጥንተው ሀሳብ በማሰባሰብ ጽፈው እንዲያቀርቡ ያዛሉ ? | 1 | 20% | 3 | 60% | 1 | 20% |
| 14 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በማቀድ በማርቀቅና በማረም ሂደት በማለፍ መጻፍ እንዲችሉ በማበረታታት ያስተምራሉ ? | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |
| 15 | በአጻጻፍ፡ሂደት፤ማቀድ፣ማርቀቅ፣መከለስ፣ ማቃናት ተግባራትያስተምራሉ? | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |
| 16 | ድርሰትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያበረታታሉ ? | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |

በሰንጠረዥ 6 በጥያቄ 13 ድርሰትን ለማስተማር ሁልጊዜ ተማሪዎች አንድን ነገር ተመልክተው ወይም አጥንተው ሀሳብ በማሰባሰብ ጽፈው እንዲያቀርቡ የሚያበረታቱ 1(20%) ሲሆን 3(60%) ደግሞ አልፎ አልፎ ስለ አንድ ነገር አጥንተው ሀሳብ የማሰባሰብ ተግባር እንዲያከናውኑ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ቀሪ 1(20%) መምህራን ግን ሀሳብን ከተለያየ ቦታ በማሰባሰብ እንዲሰሩ የሚያበረታቱ ተግባራትን አያከናውኑም፡፡

በዚሁ ሰንጠረዥ በጥያቄ 14 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በማቀድ፣በማርቀቅና በማረም ሂደት በማለፍ መጻፍ እንዲችሉ የማድረጉ ተግባር ሁልጊዜ የሚያስተምሩ 1(20%) ሲሆኑ 1(20%) ግን አልፎ አልፎ የጽህፈት ደረጃዎችን የሚያሳውቁ ናቸው፡፡ ቀሪ 3(60%) ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን የአፃፃፍ ደረጃዎች ለተማሪዎች የማያሳውቁ ናቸው፡፡

በጥያቄ 15 በድርሰት ሂደት የአጻጻፍ ሂደትን/ የማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስና ማቃናት/ ተግባራትን አብዛኛው እንዲተገብሩ የሚያደርጉ 1(20%) ናቸው፡፡ 1(20%) ደግሞ አልፎ አልፎ የድርሰት ሂደት ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያስተምራሉ፡፡ ቀሪ 1(60%) በድርሰት ሂደት የተግባር ደረጃዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የማያበረታቱ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ድርሰትን በማስተማር ሂደት ለማስተማር መከናወን ካለባቸው ተግባራት ውስጥ አብዛኛዎቹ ተግባራዊ አለመሆናቸውን ነው፡፡

በጥያቄ 16 ድርሰትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ሁልጊዜ አካላዊና ስነልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያበታቱ 2(40%) ሲሆኑ ቀሪ 3(60%) ተማሪዎች ዝግጅት የሚያደርጉበትን ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚያመቻቹ ስለመሆናቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡ ይህ የሚያሳየው መምህራን በድርሰት ትምህርት ተማረዎች አካላዊ እና ስነልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ የማበረታታት ሁኔታው ውሱኑንነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

## 4.1.9 ስለ ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህራን ስልጠናን በተመለከተ

ስለ ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች ስልጠና የወሰዱ ስለመሆናቸው ከመምህራን ልቅ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ለቋንቋ ትምህርት መምህርነት በቂ ስልጠና እንደተሰጣቸው አንድ መምህር አወንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ሁለት መምህራን ግን ስልጠናው በቂ መሆኑን እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡ አንድ መምህር ደግሞ በመጠኑ የሚስማሙ መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ መምህራን ስለ ጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸዉ የተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃውም ያረጋግጣል፡፡

## 4.2 ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ ምን ይመስላል?

### 4.2.1 የተማሪዎችን ተግባር ስለማሳወቅ

ሰንጠረዥ 7 በፅህፈት ትምህርት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ተግባር ከማሳወቅ አኳያ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ ያደርጋሉ | | አልፎ አልፎ ያደርጋሉ | | አያደርጉም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በጽህፈት ትምህርት ስለምትጽፋበት ርዕስ ፣ አላማ ፣ ቅርጽ እራሳችሁ እንድትወስኑ እድሉን ይሰጧችኋል? | 92 | 40% | 46 | 20% | 92 | 40% |
| 2 | ጽህፈትን ከመጻፋችሁ በፊት የአጨራረስ ሂደትን ያስተምሯችኋል? | 50 | 21.73 % | 65 | 28.27 % | 115 | 50% |
| 3 | በጽህፈት ሂደት የቃላት ምርጫ፣ የአቀራረብ ስልት፣የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓተ ነጥቦችን ደጋግማችሁ በማየት እንድታርሙ ያዟችኋል? | 48 | 20.87 % | 52 | 22.61 % | 130 | 56.52 % |
| 4 | መምህራችሁ ሰው ጠይቃችሁ ወይም ጥናት አድርጋችሁ ሀሳብ በማሰባሰብ እንድትጽፋ ያዝዛሉ? | 120 | 50.21 % | 62 | 28.92 % | 48 | 20.87 % |
| 5 | ከጽህፈት ትምህርታችሁ በፊት እንድታሰላስሉ ያበረታቷችኋል? | 68 | 29.57 % | 92 | 40% | 70 | 30.43 % |

ከሰንጠረዥ 7 እንደምንገነዘበው በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ተግባር ከማሳወቅ አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኘ ምላሽ በጥያቄ 1 በጽህፈት ትምህርት ስለምትጽፋት ርዕስ፣ዓላማ፣ቅርፅ እራሳችን እንድንወስን ዕድሉን ይሰጡናል የሚል ምላሽ የሰጡ 92(40%) ሲሆን 46(20%) ደግሞ ርዕስ የመምረጥ፣ዓላማ

የመወሰን ተግባር በእራሳችን እንድንወስን የሚያደርጉን አልፎ አልፎ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 92(40%) ተማሪዎች ግን በድርሰት ትምህርት ርዕስ የመምረጥ የመወሰን ኃላፊነት እንዲኖራቸው ስለመደረጉ አይስማሙም ይህ ማለት የተጠቀሱትን ተግባራት የመፈጸም ኃላፊነት እንዲኖራቸው መምህራን ስለሚደረግላቸው የማይስማሙ ናቸው፡፡

ለዚህም Murry (1982 )የተባሉ ምሁር በጽህፈት ትምህርት ጊዜ የተማሪው ኃላፊነት ስለሚፅፍበት ርዕስና አላማ መወሰን መቻል አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

ጥያቄ ቁጥር ሁለትን በተመለከተ 50(21.73%) መላሾች መምህራን የአጨራረስ ሂደቶችን ያስተምሩናል ሲሉ 65(28.27%) ደግሞ ጽህፈት ከመጻፋችን በፊት የአጨራረስ ሂደትን በመጠኑ ያስተምሩናል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 115(50%) ግን ጽህፈትን ከመጻፋቸው በፊት የአጨራረስ ሂደትን ስለመማራቸው አይስማሙም፡፡ በዘህም መምህራን ተማሪዎች ከመፃፋቸው በፊት የአጨራረስ ሂደትን የማስተማር ውሱኑነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

በጥያቄ 3 መምህራን የተማሪውን ተግባር ከማሳወቅ አኳያ በጽህፈት ሂደት የቃላት ምርጫ፣የአቀራረብ ስልት ፣የቋንቋ አጠቃቀም፣ ስርዓተ ነጥቦችን ደጋግመን በማየት እንድናርም ያዙናል በሚል ምላሽ የሰጡ 48(20.87%) ሲሆኑ 52(22.61%) በጽህፈት ሂደት የቋንቋ አጠቃቀምን፣ ስርዓተ ነጥቦችን ደጋግሞ በማየት የማስተካከል ተግባር እንዲያከናውኑ አልፎ አልፎ ስለመታዘዛቸው የሚስማሙ ናቸው፡፡ 130(56.52%) ደግሞ ጽህፈትን በመጻፍ ሂደት ተማሪዎች የጻፉትን ረቂቅ ደጋግመው እንዲያርሙ ስለመታዘዛቸው የማይስማሙ ናቸው፡፡ የጻፉትን ረቂቅ ደጋግሞ የማረም ተግባር እንዲያከናውኑ በመምህራቸው ትዕዛዝ የማይሰጣቸው ቁጥር በርካታ መሆኑን ከምላሹ መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ሰንጠረዥ በጥያቄ 4 መምህራን ለተማሪዎች ሰው ጠይቀው ወይም ጥናት አድርገው ሀሳብ በማሰባሰብ እንዲጽፉ የሚያዘዙ ስለመሆኑ120(50.21%) ተማሪዎች በጣም እንደሚስማሙ ሲገልጹ 62(28.92%) በመጠኑ ማለትም አልፎ አልፎ ትዕዛዝ ይሰጠናል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 48(20.87%) ተማሪዎች ደግሞ ሰው ጠይቀው

ወይም ጥናት አድርገው ሀሳብ በማሰባሰብ እንዲጽፉ ስለመታዘዛቸው ፈጽሞ አይስማሙም፡፡ በዚህ ረገድ መምህራን የተሻለ አፈፃፀም እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ለጥያቄ 5 በጽህፈት ትምህርት ጽህፈት ከመጻፋችን በፊት የማሰላሰል ደረጃን እንዲናከናውን መምህራን ስለማስተማራቸው የሚስማሙ 68 (29.57%) ሲሆኑ 92(40%) በመጠኑ ይስማማሉ ማለትም መምህራን አልፎ አልፎ ድርጊቱን ይፈጽማሉ በማለት መልሰዋል፡፡ 70(30.43%) ደግሞ የማሰላሰል ሂደት ደረጃን እንዲያከናውኑ ወይም ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ፈጽሞ አይስማሙም፡፡ ይህ የሚያመለክተው ብዙ ጊዜ በጽህፈት ትምህርቱ የማሰላሰል ደረጃ ተግባራዊ አለመሆኑን ነው፡፡

### 4.2.2 ፅህፈትን በሂደት የማስተማር ዘዴና ጠቀሜታው

ሰንጠረዥ 8 ከፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች አኳያ ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ ያደርጋሉ | | አልፎ አልሮ ያደርጋሉ | | አያደርጉም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 6 | መምህራችሁ የምትጽፋበትን ርዕስ በማቅረብ ርዕሱን ያስተዋውቃሉ ? | 95 | 41.30% | 74 | 32.17% | 61 | 26.53% |
| 7 | የጽህፈት መልመጃዎችን በግል ፣ በጋራ ፣ በቡድን እንድትጽፋ አዘጋጅተው ያቀርባሉ? | 50 | 21.73% | 65 | 28.27% | 115 | 50% |
| 8 | ጽህፈትን ከማርቀቃችሁ በፊት ቢጋር እንድታዘጋጁ ይነግሯችኋል? | 68 | 29.13% | 41 | 17.82% | 121 | 53.05% |

ከሰንጠረዥ 8 መረዳት እንደሚቻለው ጽህፈትን ከማስተማር አኳያ ለከቀረበው ጥያቄ 6 መም ህራችሁ የምትጽፋበትን ርዕስ በማቅረብ ርዕሱን ያስተዋውቃሉ ወይ ተብለው ተጠይቀው 9 5(41.30%) በጣም ተስማምተዋል፡፡ 74 (32.17%) በመጠኑ ተስማምተዋል 61 (26.53%) ደግሞ ፈጽሞ ባለመስማማት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ እንደምንረዳው መምህራኑ ተማሪዎች የሚጽፉበት ርዕስ ከማቅረብ አንፃር ጥሩ አፈፃፀ ም እንዳለ ነው፡፡ተማሪዎች በጥያቄ 7 የጽህፈት መልመጃዎችን በግል፣ በጋራ፣ በቡድን እንድትጽፉ አዘጋጅተው ስለማቅረባቸው ተማሪዎች ተጠይቀው 50(21.73%) በጣም ተስማምተዋል፣ 65(28.27%) በመጠኑ ተስማምተዋል፡፡ 115(50%) አልተስማሙም፣ ይህም ማለት ጽሕፈትን በጋራና በቡድን እንዲሰሩ መምህራን መልመጃዎችን ያቀርባሉ በሚለ ው ሀሳብ አለመስማማታቸውንበምላሻቸውአረጋግጠዋል፡፡

ሰንጠረዥ 8 ጽህፈት ከማርቀቃቸው በፊት ቢጋር እንዲያዘጋጁ ስለመደረጉ ተማሪዎች ተጠ ይቀው 68(29.13%) በጣም ተስማምተዋል፣41(17.82%) በመጠኑ ተስምተዋል፣ 121 (53.05%) አልተስማሙም፡፡ በዚህ መሠረት ተማሪዎች ከጽሕፈት በፊት ቢጋር እንዲያዘጋጁ በማድረግ ረገድ ውሱንነት አለ ማለት ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 9 የመምህራኑ የማስተማሪያ ዘዴ በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ ያደርጋሉ | | አልፎ አልሮ ያደርጋሉ | | አያደርጉም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 9 | መምህራችሁ ጽህፈትን ሲያስተምሩ እንድትለማመዱ በሚያስተምሯችሁ ጽህፈትን የማስተማሪያ ዘዴው ለመጻፍ ክሂላችሁ አስተዋጽኦ አበርክቷል? | 39 | 16.95% | 63 | 27.13% | 128 | 55.9% |
| 10 | መምህራችሁ በክፍል ውስጥ በግል በቡድንና በብጤ ውይይት ወቅት ተጠቅማችሁ የጽህፈት ክሂላችሁን ማዳበር የምትችሉበትን ሁኔታ አመቻችተው በማስተማራቸው የመጻፍ ክሂላችሁን አዳብሮላችኋል? | 16 | 6.96% | 72 | 31.31% | 142 | 61.7% |

ከሰንጠረዥ 9 መረዳት እንደሚቻለው በጥያቄ 9 39(16.95%) ተማሪዎች መምህራቸው በሚያስተምሩበት ጽህፈትን የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂላቸው ስለመሻሻሉ በጣም የሚስማሙ ሲሆን 67(27.13%) ደግሞ በመጠኑ የመጻፍ ክሂላቸው መሻሻሉን ይስማማሉ፡፡ ቀሪ 128(55.92%) ደግሞ ተግባራዊ በሚደረገው ጽህፈትን የማስተማሪያ ስልት የመጻፍ ክሂላቸው ስለመሻሻሉ የሚስማሙ አይደሉም፡፡ ይህም ማለት መምህራን እየተጠቀሙ ያሉት የማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል ውሱኑነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

በዚሁ ሰንጠረዥ በጥያቄው 10 መምህራችሁ በክፍል ውስጥ በግል ወይም በቡድንና በብጤ ውይይት ተጠቅማችሁ የመጻፍ ክሂላችሁን ማዳበር የምትችሉበትን ሁኔታ አመቻችተው በማስተማራቸው የመጻፍ ክሂላቸው መዳበሩን የሚስማሙ 16(6.96%) ሲሆኑ 72(31.31%) ደግሞ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ውይይት የመጻፍ ክሂላቸውን ለማዳበር አመቻችተው መምህራቸው ስለማስተማራቸው በመጠኑ የሚስማሙ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 142(61.73%) ደግሞ በቡድንና በብጤ ውይይት የመጻፍ ክሂላቸውን ለመዳበር ምቹ ሁኔታ አለመኖሩንና የመጻፍ ክሂላቸውም አለመሻሻሉን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚደረገው የቡድን ውይይት የተመቸ ባለመሆኑ የመጻፍ ክሂላቸው ፈጽሞ አለመሻሻሉን የሚጠቁሙ ናቸው ማለት ነው፡፡

ይህም የሚያመላክተው ተጠኚ መምህራን ጽህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሙት ማስተማሪያ ዘዴ የጽህፈት ክሂልን ስለማዳበሩ ከምልከታና ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአብዛኛው አሉታዊ ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህራን የጽህፈት ክሂልን በማስተማሩ ሂደት እየተጠቀሙበት ያለው ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ጠቀሜታ በአብዛኛው ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## 4.3 የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ ምን ይመስላል?

### 4.3.1 የመምህራን የማስተማር ብቃት የሚያመለክቱ መረጃዎች

ሰንጠረዥ 10 ጽህፈትን በማስተማር ሂደት የመምህራን የማስተማር ብቃት የሚያመለክቱ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ ያደርጋሉ | | አልፎ አልፎ ያደርጋሉ | | አያደርጉም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 11 | መምህራችሁ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ የጽህፈት ልምምድ እንድታደርጉ በቂ መልመጃዎች ያዘጋጃሉ? | 40 | 17.40% | 47 | 20.43% | 143 | 62.17% |
| 12 | መምህራችሁ ሲያስተምሩ የተለያዩ የጽህፈት ስራዎችን ከቀላል ወደ ከባድ በማሸጋገር ደረጃ በደረጃ እንድታሻሽሉ የሚያግዙ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው ትስማማላችሁ? | 42 | 18.27% | 45 | 19.56% | 143 | 62.17% |
| 13 | በክፍል ውስጥ ስለምትጠይቁት የጽህፈት አጻጻፍ ሂደት ጥያቄዎች ግልጽና ተገቢ ምላሽ ይሰጣሉ ? | 35 | 15.22% | 80 | 34.78% | 115 | 50% |

ከሰንጠረዥ 10 ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ለጥያቄ 11 ከተጠኚ ተማሪዎች 40(17.40%) መምህራችን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ የጽህፈት ልምምድ እንዲናደርግ በቂ መልመጃዎች እንደሚያዘጋጁ የሚስማሙ ሲሆን 47(20.43%) ደግሞ መምህራቸው የጽህፈት ልምምድ እንዲያደርጉ በቂ መልመጃዎች እንደሚያዘጋጁ በመጠኑ ይስማማሉ፡፡ 143(62.17%) ግን የጽህፈት ልምምድ እንዲያደርጉ በቂ መልመጃዎች እንደሚያዘጋጁ የማይስማሙ ናቸው፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች የጽህፈት ልምምድ እንዲያደርጉ በመምህራን በቂ እገዛ የሚደረግ አለመሆኑን ነው፡፡

በጥያቄ 12 መምህራችሁ ሲያስተምሩ የተለያዩ የጽህፈት ስራዎችን ከቀላል ወደ ከባድ በማሸጋገር ደረጃ በደረጃ እንዲያሻሽሉ ስለማድረጋቸው በጣም የሚስማሙ 42(18.27%)

ሲሆኑ 45(19.56%) ደግሞ በመጠኑ ይስማማሉ፡፡ ቀሪ 143(62.17%) ግን የጽህፈት ስራዎች ከቀላል ወደ ከባድ በማሸጋገር ደረጃ በደረጃ እንዲያሻሽሉ የሚያግዙ ስለመሆናቸው አይስማሙም፡፡ በተማሪዎቹ ምላሽ መሠረት የጽህፈት ትምህርት በደረጃ ከከባድ ወደ ቀላል የጽህፈት ትምህርትን ለማሻሻል በሚያግዝ መልኩ እየቀረበ አለመሆኑን ነው፡፡

በጥያቄ 13 በክፍል ውስጥ ስለምጠይቀው የጽህፈት አጻጻፍ ጥያቄዎች ግልጽና ተገቢ ምላሽ ይሰጣል የሚል ምላሽ የሰጡ 35(15.22%) ሲሆን 80(34.78%) ለጥያቄዎች ግልጽና ተገቢ ምላሽ እንደሚሰጣቸው በመጠኑ የሚስማሙ ናቸው ፡፡ 115(50%) ደግሞ በጽህፈት አጻጻፍ ለሚነሱ ጥያቄዎች መምህራቸው ግልጽና ተገቢ ምላሽ ስለመስጠታቸው የማይስማሙ ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ተጠኚ መምህራን ከተማሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ ቢሆንም የጽህፈት ትምህርቱን ከቀላል ወደ ከባድ የማሸጋገርና ለተማሪዎች የጽህፈት ልምምድ እንዲያደርጉ የሚያግዙ በቂ መልምጃዎችን የማዘጋጀት ብቃት የሌላቸው መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

### 4.3.2 የመምህሩን ኃላፊነት የሚያመለክቱ መረጃዎች

**ሰንጠረዥ 11 ፅህፈትን በማስተማር ሂደት የመምህሩን ኃላፊነት በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ ያደርጋሉ | | አልፎ አልፎ አደርጋለሁ | | አላደርግም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 14 | ጽህፈት ስትጽፉ ጽፋችሁ የምትጨርሱበትን ጊዜ ወስነው ይነግሯችኋል? | 55 | 23.13% | 67 | 29.13% | 108 | 47.74% |
| 15 | መምህራችሁ ጽህፈት ለመጻፍ በመረጣችሁት ርዕስ ላይ ከብጤዎቻችሁ ጋር የሀሳብ ልውውጥ እንድታደርጉ ያዛሉ ያበረታታሉ ጽሁፋችሁን እንድታስተካክሉ ይረዷችኋል? | 30 | 13.10% | 40 | 17.34% | 160 | 69.56% |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | መምህራችሁ በክፍል ውስጥ በጽሀፈት ትምህርት ሂደት በራሳችሁ የመለማመድ የተግባር ልምድ እንዲኖራችሁ ያግዟችኋል ? | 35 | 15.22% | 69 | 30% | 126 | 54.78% |
| 17 | መምህራችሁ በጽሀፈት ትምህርት የጽሀፈት ህጎችንና ልምዶችን፣የጽሁፍ መርሆዎችን ያስተምሯችኋል? | 27 | 11.73% | 42 | 18.26% | 161 | 70% |
| 18 | በጽሀፈት ትምህርት ሂደት የማሰላሰል ደረጃ፣የማርቀቅ ደረጃ የመከለስ ደረጃ ተግባራትን እንድታከናውኑ ያዟችኋል? | 43 | 18.69% | 59 | 25.65% | 128 | 55.66% |

ከሰንጠረዥ 11 መረዳት እንደምንችለው ድርሰት በማስተማር ሂደት የመምህሩን ሚና በተመ ለከተ ለተማሪዎች ከቀረበላቸው መጠይቅ በጥያቄ 14 ጽሀፈት ሲጽፉ የሚጨርሱበትን ጊዜ መምህራቸው ወስነው ስለመናገራቸው ተማሪዎቹ ተጠይቀው 55(23.13%) በጣም እስማማለሁ ሲሉ 67(29.13%) መምህራን አልፎ አልፎ ያደርጋሉ ብለዋል 108(47.74%) ግን አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው መምህራን በአብዛኛው ለተማሪዎች ድርሰት ጽፈው የሚያጠናቅቁበትን ጊዜ በግልጽ እንደማያሳውቁ ነው፡፡

በጥያቄ 15 ለመጻፍ በመረጡት ርዕስ ላይ ከብጤዎቻቸው ጋር የሀሳብ ልውውጥ እንዲያደ ርጉ፣ ጽሁፋቸው እንዲያስተካክሉ መምህራቸው ስለማዘዛቸው ተማሪዎች ተጤቀው 30 (13.10%) በጣም ተስማምተዋል፡፡ 40(17.34%) በመጠኑ ድርጊቱ እንደከናወን ተስማምተዋል፡፡ 160(69.56%) ግን መምህራን ድርጊቱን እንደሚያከናውኑ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተጠኚ መምህራን ብዙ ጊዜ በድርሰት ትምህርቱ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

በጥያቄ 16 የመምህሩን ሚና በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው 35(15.22%) መምህራን በራስ የመለማመድ ተግባር የሚያግዙ

ሲሆን 69(30%) በመጠኑ ክንውን እንዳለ ገልጸዋል 126(54.78%) ግን መምህራን በራስ መለማመድን እንደማያበረታቱ መግለጻቸውን የተሰበሰበው መረጃ ያመለክታል፡፡

በጥያቄ 17 መምህራቸው በጽህፈት ትምህርት ህጎችንና ልምዶችን፣የጽሁፍ መርሆችን ስለማስተማራቸው ተማሪዎች ተጠይቀው 27(11.73%) ተስማምተዋል፡፡ 42(18.26%) አልፎ አልፎእንደሚደረግ ተስማምተዋል 161(70%) ግን የጽሁፍ መርሆዎችን ስለመማራቸ ው አልተስማሙም፡፡ በዚህ በኩል በመምህራን ዘንድ ውሱኑነት እንዳለ ያሳያል፡፡

በጥያቄ 18 በጽህፈት ትምህርት ሂደት የማሰላሰል ደረጃን የማርቀቅ ደረጃን የመከለስ ደረጃን እንዲያከናውኑ ስለመማራቸው ተጠይቀው 43(18.69%) ተማሪዎች አዎ በማለት ተስማምተዋል፣ 59(26.65%) አልፎ አልፎ እንደሚማሩ ተስማምተዋል፣ 128(53.66%) ደግሞ እነዚህን ደረጃዎች እንዲያናውኑ ስለመታዘዛቸው ፈጽሞ አልተስማሙም፡፡ እነዚህን ደረጃዎች ከመተግበር አኳያ ከምልከታውና ከተማሪዎች መጠይቅ የተሰጡ ምላሾች የሚያመላክቱት አብዛኛዎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ሀሳብን ለመግለጽ የሚያስችሉ ጽሁፎችን እንደማይጽፉ፣ ተማሪዎች በማቀድ፣ በማርቀቅ፣ በመከለስና በማረም ሂደት አልፈው የሚጽፉ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ አይነቱ የማስተማሪያ ዘዴ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ሂደታዊ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴን የማይጠቀሙ መሆናቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከምልከታና ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የጽህፈት ትምህርቱ በአብዛኛው ውጤታዊ አቀራረብን የተከተለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የጥናቱን ማጠቃለያና አስተያየቶችን መግለጽ ነው፡፡፡ ስለሆነም የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥናቱ የተካሄደበትን አውድ፤የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያና መረጃ የተተነተነባቸው መንገዶች፤የመረጃ ትንተናው ዋና ዋና ግኝቶች ተጨምቀው ቀርበዋል፡፡ ከዚያም በጥናቱ ግኝቶች ላይ የተመሰረቱ የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሻራ፣በጫኖ፣በላንቴ፣በሽሌና በካንቻማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፈት ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎችን መገምገም ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይዞ ተነስቷል፡፡

1. ጽህፈትን ለማስተማር መምህራን የሚጠቀሙትን የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴን መለየት፣
2. ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ መመርመር፣
3. የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተራክቦ መገምገም ነው፡፡

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሁለት የጽህፈት ትምህርት አቀራረብን የተመለከቱ በተለያዩ ምሁራን የተጠቆሙ ጽንሰ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ሶስት በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ ከተማሪዎችና ከመምህራን መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች በምዕራፍ አራት ተተንትነዋል፡ትንተናው መምህራን ስለ ጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ካላቸው ግንዛቤ፣ኃላፊነት፣ ውጤታማ የጽህፈት ማስተማር ዘዴን ከመተግበርና በስራ ላይ ለማዋል መምህራንና ተማሪዎች መወጣት ከሚጠበቅባቸው የስራ ድርሻ አንጻር ትንተናው በሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ ደርሷል፡፡

ከጥናቱ ዝርዝር አላማዎች አንዱ መምህራን የጽህፈት ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙት የማስተማር ስነ-ዘዴ መለየጥ ሲሆን በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኚው ባደረጋቸው ጥናት የተቃኙት መምህራን ግን የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙት ስነ ዘዴ ውጤት ተኮርንና

ሂደት ተኮርን ሲሆን በአብዛኛው ግን ውጤት ተኮር ላይ ያተኮረ መሆኑን ከምልከታ፣ ከተማሪዎችና ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

ሁለተኛ የጥናቱ ዝርዝር አላማ ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርቱ ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ መመርመር ሲሆን መምህራን የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር እና ውጤታማ የሀሳብ ተግባቦት እንዲኖር ተማሪዎች ሀሳብ በማፍለቅ መጻፍ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት በቂ ልምምድ የሚያደርጉበትን የክፍል ስራና የቤት ሥራ እንዲሁም መልመጃዎችን አዘጋጅቶ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ተጠኚ መምህራን ለደረጃው የሰለጠኑ ቢሆንም እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት የተማሪዎች የጽህፈት ተግባቦት የሚዳብርበትን፣ተማሪዎች በመጻፍ መጻፍን የሚማሩበትን የማስተማር ዘዴ ተጠቅመው በተገቢው ሁኔታ በማቅረብ በኩል ውስንነቶች እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ አብዛኛዎቹ መምህራን ጽህፈትን ለማስተማር የተለያዩ ሂደቶችን ያካተቱ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ አልተገኙም፡፡ በመሆኑም መምህራን ጽህፈትን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማስተማር ስነ ዘዴ የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂላቸውን ለማሻሻል የሚያደርገው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነዉ፡፡

ሶስተኛዉ የጥናቱ ዝርዝር አላማ የጽህፈት ክሂል በመማር ማስተማር ወቅት የመምህሩና የተማሪውን ተራክቦ መገምገም ሲሆን በተጠኚ መምህራን ውስጥ የፅህፈት ትምህርት ይሰጥ የነበረው ጽህፈትን በማስተማር አላማ ላይ ተማሪዎች በማቀድ፣ በመከለስ፣በማርቀቅና በማረም ሂደት እንዲያልፉ ድጋፍ በማድረግ አልነበረም፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ ጽህፈትን በተግባራዊ ሂደት ለማስተማር የተደረገ ጥረት ጎልቶ አልታየም፡፡ በአብዛኛው በክፍል ዉስጥ ምልከታ ተግባራዊ ሲሆን የታየው ተማሪው በሚያመርተው የመጨረሻ ውጤት ላይ ያተኮረ የማስተማሪያ ዘዴ እንደነበር መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርት ያላቸዉ ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን በተደረገው ጥናት ተረጋግጧል፡፡

መምህራን ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በቡድን በመወያየት መጻፍን፣ በመተራረም፣ በመረዳዳት ወደ ተሻለ የመጽሀፍ ልምምድ የሚሸጋገሩበት የቢጤና የቡድን ስራ እንዲጠቀሙ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል ፡፡ በክፍል ውስጥ የቡድን ሥራ ለማሰራት የሞከሩት መምህራንም ቡድኖቹን በአግባቡ አደራጅተው፣የሥራ ድርሻ በመስጠት ውጤታማ የቡድን ስራ የሚያሰሩ አለመሆናቸውን ፣ ብሎም መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን

ሂደቶች በፅህፈት ትምህርት አቀራረቡ ለመጠቀም በዚ ግዜ ግንዛቤ እንደሌላቸው በተከታታይ ምልከታና በጽሁፍ መጠይቁ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የተሸለ ለተማሪዎች መሻሻል የሚረዳ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብን በማወቅና በአግባብ ተጠቅሞ ተግባራዊ ክንውን የሚካሄድበት ነው ማለት አያስደፍርም ፡፡

የመምህራኑ ትኩረት ለተማሪዎች ስነልሳናዊ እውቀትን ለማስጨበጥ የታለመ፣ በቃላቶችና ሀረጎች ፍቺና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ነው እንጂ፣እነዚህን ስነ- ልሳናዊ እውቀቶች ተጠቅመው ሀሳባቸውን በጽሁፍ መግለጽ የሚችሉበት የማስተማሪያ ዘዴ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም፡፡ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብን የተለያዩ ሂደቶችን በማካተት ለተማሪዎች ውጤታማነት መምህራን በትጋት እንዲሰሩ ለማድረግና የግንዛቤ እጥረትን በመቅረፍ በምሁራን የተደገፈ የተሻለ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብን በተገቢው ሁኔታ ለመተግበር ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን አስተያየቶችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝተል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ቀደም ሲል በማጠቃለያው ለማሳየት እንደተሞከረው በተጠኚው የክፍል ደረጃ ተጠኚ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ወደ ውጤት ተኮር ሥነ-ዘዴ ያዘነበለና ሂደት ላይ ትኩረት አለማድረጉን ተመልክተናል፡፡ በዚህም የጥናት ውጤት ውስጥ ከአጥኚው ርዕስ ጋር ከይዘት እና ከጥናት ውጤት አንጻር የሚመሳሰሉትና የሚቀራረቡት ተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝቶች ውስጥ የሰይድ (ይመር 1993 እና የግዛቸው በላይ 1991) ናቸው፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ተመራማሪዎች ጥናቱን ካካሄዱ በኃላ ያገኙትን ውጤት ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ስናነጻጽር ሰይድ ያገኘውን ውጤት ስንመለከት መምህራን የጽህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት ይዘቶችና መልመጃዎችን እንዲሁም ክሂሉን ለማዳበር ስራ ላይ የሚውሉት ስነዘዴዎች ትግበራ ጽህፈትን የማያለማምዱና ለክሂሉ መዳበር አስተዋጽኦ የሌላቸው መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡

በተጨማሪም የግዛቸው በላይ የጥናት ውጤትን ስንመለከት በመማሪያ መጻህፍት የሚቀርቡት መልመጃዎች በሂደታዊ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ቢቀርቡ ለጽህፈት ክሂል መዳበር ጥሩ ውጤት የሚያስገኙ ይሆናል፡፡ ተማሪዎችም በክሂሉ በሚፈለገው ደረጃ ሊጠቀሙ ያችላሉ፡፡ ውጤት ተኮር አቀራረብ ግን ለጽህፈት ክሂል ምዘና ብቻ ቢውል ጊዜውን ስለሚቆጥብ ጠቃሚ

መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ከላይ ከተጠቀሱት ተመራማሪዎች ዉስጥ ከአጥኚው የጥናት ውጤት ጋር የሚያመሳስለው የግዛቸው በላይ የጥናት ውጤት ሲሆን ይኸውም አጥኚው በክፍል ውስጥ ባደረጋቸው ተከታታይ ምልከታ መምህራን የጽህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማስተማር ስነዘዴ ሂደት ተኮርንና ውጤት ተኮርን ሲሆን ከነዚህ የማስተማር ስነ ዘዴዎች ግን መምህራን በአብዛኛዉ ወደ ውጤት ተኮር ስነዘዴ ያዘነበሉና ሂደት ተኮር የማስተማር ስነዘዴ ላይ ትኩረት አለማድረጋቸውን በተደረገው ክፍል ውስጥ ምልከታ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም በተደረገው የክፍል ውስጥ ትግበራ ውጤትን ደግሞ ስንመለከት ለ መምህራን ጽህፈትን ሲያስተምሩ የአፃፃፍ ሂደትን በማሳየት ተማሪዎች በተግባራዊ ስራቸው እንዲያከናውኑት የተደረገው ጥረት ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በዋነኛ ምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለው የግንዛቤ እጥረት መኖሩ ነው፡፡ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብን የተለያዩ ሂደቶችን በማካተት ለተማሪዎች ውጤታማነት መምህራን በትጋት እንዲሰሩ ለማድረግና የግንዛቤ እጥረትን በመቅረፍ በምሁራን የተደገፈ የተሻለ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብን በተገቢው ሁኔታ ለመተግበር ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝተል፡፡

ይህን ውጤት መሰረት በማድረግም ጠቃሚ የሆኑት ተጠናክረው ቢቀጥሉ፣ ድክመት የታየባቸው ደግሞ እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ ከጥናቱ የመፍትሄ ሃሳቦች ጋር በማዛመድ አመላካች ሀሳቦችን ለባለ ድርሻ አካላት ተጠቁሟል፡፡

**ለመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች፡-** በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ከአራቱ ክሂሎች ውስጥ በተለይ ለመጻፍ ክሂል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ፣ሁሉም ክሂሎች በእኩል መልክ መሰጠት ቢችሉ፣ለአንዱ ትኩረት ተሰጥቶ ለሌላው ችላ መባሉ በተማሪዎች ቋንቋ ችሎታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠሩ…ወዘተ በዚህም ምክንያት በተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለባቸው በቅርበት መገንዘብ ስለተቻለ መማሪያ መጽሃፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ እና ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ጽሁፍ ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ዕድሜና ከትምህርት ደረጃቸዉ ጋር የሚጣጣም መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ቢዘጋጅና ለመጻፍ ክሂልም ትኩረት ቢሰጥበት፣

**ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-** የመጻፍ ክሂልን ማስተማሪያ የሚሆኑ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ጽሁፎች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂላቸዉን ለማዳበር ያላቸው ሚና አጋዥ መሆናቸውንም ጭምር ማረጋገጥ ቢቻልና ክፍተቶችን ለመሙላት ከፍተኛ ጥረት ቢደረግ፣

መምህራን የመጻፍ ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅትም ሁሉንም አሳታፊ የማስተማር ስነ-ዘዴን በመጠቀምና፣እንዲሁም ለተማሪዎች መተላለፍ የሚገባውን መልዕክት በትክክል መረዳታቸውንና መገንዘባቸዉን በማረጋገጥ ተከታታይ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ትምህርቱን ቢያጠናክሩ፣

**ለስልጠና አመቻች ባለሙያዎች፡-** የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የመምህራን ተከታታይ የክህሎት ስልጠና እንደሚያስፈልግ አያጠራጥርም፡፡ በመሆኑም የትምህርት ባለሙያዎች የመምህራን ዕውቀት በቃ የሚባል ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እየተለወጠ የሚሄድ በመሆኑ፣ አዕምሮም እየጎለበተ ስለሚሄድ በተቻለ መጠን አጫጭር ስልጠናዎች ለመምህራን ቢመቻችላቸው በመማር ማስተማር ሂደት ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ሊቀረፉ ይችላሉ፡፡

## ጥናት ሊካሄድባቸዉ የሚገቡ ጉዳዮች ጥቆማ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን መገምገም ነዉ፡፡ ስለሆነም፡-

- የመጻፍን ክሂል ለማዳበር ሂደታዊ የማስተማር ስነ ዘዴን መምህራን ቢጠቀሙ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂላቸዉን ሊያዳብር ስለሚችል ጥልቅ ጥናት ቢደረግ፣
- አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ከማዳበር አንፃር መምህራን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የተማሪዎችን ክሂል በሚገባ ሊያዳብር የሚችለውን የማስተማር ዘዴዎችን እየመረጡ ቢጠቀሙና ይህንን በተመለከተ ጥናት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል የሚሉት የዚህ ጥናት ጥቆማዎች ናቸዉ፡፡
- በአጠቃላይ ጽህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት ጎልተው የታዩ ችግሮች፡-
- የፅህፈት ክሂልን ለማስተማር ሰፋ ያለ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ይታመናል፡፡ይሁን እንጂ ለትምህርት ደረጃው የተመደበው ክ/ጊዜ ማነስ ተግባራዊነቱን ቀንሶት ታይቷል፡፡
- በአብዛኛው በጽህፈት ትምህርቱ መምህራን በመጻፍ ሂደት ላይ ከማተኮር ይልቅ በተማሪዎች የመጨረሻ ስራ / ውጤት / ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት መምህራን ማከናወን የሚገባቸውን እንዳያከናውኑ ተጽዕኖ መፍጠሩ ተስተውሏል፡፡

በአጠቃላይ በሻራ፣በጫኖ፣በላንቴ፣በሸሌና ካንቻማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍል የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በመጻፍ ሂደት ላይ እያሉ የሚፈጸሙ የተለያዩ ደረጃዎችን መሰረት ያደረገ ትምህርት አለመቅረብ እንደ ዋና ችግር የሚጠቀስ ሲሆን ለችግሮቹ የመፍትሔ ሃሳቦች ደግሞ፡-

- ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የሚውለው ክፍለ ጊዜ ለአንድ ክፍል በሳምንት ሁለት መሆኑ ቀርቶ የሚሻሻልበት ቢመቻች፣
- የተሻለውን የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ መርጦ ለማስተማር እርስ በርሳቸው የልምድ ልውውጥ ቢያደርጉ፣
- በፅህፈት ክሂል ማስተማር ወቅት መከናወን የሚገባቸው ክንዋኔዎች ለማከናወን በክፍል ውስጥ የተማሪው ቁጥር ቢቀንስ የሚሉ ናቸው፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ሙልዬ በቀለ (2009) ዓ.ም)፡፡ *የተማሪዎች የአንቀጽ አፃፃፍና ግንዛቤ፣* በየት ኖራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት(*ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት*) ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፡ ደብረ ማርቆስ፡፡

ማረው አለሙ፡፡ (1988) *የጽህፈት ክሂል ማስተማር፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ዮሐንስ፡፡ (1991) *የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለአማርኛ ማስተማር ማስተ ርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ሰይድ ይመር፡፡ (1993) *"በ9ኛ ክፍል በአማርኛ መመሪያ መጽሀፍ የቀረቡት የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት/*ያልታተመ*/፡፡

በለጠ ሰጣርጌ (2010) ዓ. ም)፡፡ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሑፎች ላይ የመምህራን ግብረ መልስ አሰጣጥ ፍተሻ፡፡ (*ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት*) ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፡ ደብረ ማርቆስ፡፡

በድሉ ዋቅጅራ (1996)፡፡ *በስነ ጽሁፍ ቋንቋ ማስተማር*፡ አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ተመስገን ፈቀደ (2001)፡፡ *የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ብልሃት ተዛምዶ፡፡*አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ (1986) ፡፡ *አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር፡* አዲስ አበባ፣የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡

አለማየሁ ክፍሌ (1986) ፡፡ *‹‹በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምንጮች ትንተና፡፡››* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡(*ያልታተመ*)፡፡

አማረ ተሾመ (2010 ዓ.ም)፡፡ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ ቤት(*ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት*)

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ አዲስ አበባ፡፡

አስቴር ሳሙኤል፡፡ (1998) ፡፡ ‹‹የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2007) ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ግርማ ገብሬ፡፡ (1990)፡፡ "በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብራዊ ስልት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ  ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ግዛቸው በላይ፡፡ (1991)፡፡ "ከ9ኛ-11ኛ ክፍሎች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዲግሪ የቀረበ ጥና ት /ያልታተመ/፡፡

Brindly, Susan. (1994). Teaching English. London: Rouledge. P.169

Burack, Boris. (1965). "Composition: Why? What? How?" English Language Hournal 54. PP. 504, 506

Byrne, Dounn. (1991). Teaching writing Skill. London Langman Group. UK Limited, PP; 119, 6, 27, 33.

Celece-Murica, Marianne. (1991). Teaching English As a Second Language. Boston: Mass Massachusetts, Heinle and Heinle Publishers, PP. 215216.

Coline, etal, (1965) Resources for Modern Grammar and Composition. New York American Book Campany P,

Flower, Linda and R. Hayes, John. (1982). "A Cognitive Theory of Writing "College Composition and Communication.

Doff, A. (1988). Teach English;A Training course for Teachers. Cambridge; Cambridge University Press.

Duke, harles, (1983), Writing Through Sequence a Process ApproaOxford Oxford University Press. PP v and 3

Hedge, T. (1991). Writing.Oxford: Oxford University Press.

Kroll, Barbara. (1990). Second Language Writing, Research in sight for the classroom. Campridge: Campridige University Press.

Kroll, Barbara. (1998) “Teaching Writing in the ESL Context” Teaching English as Second Language. (ed.) in. M Celee. Boston: Massachusetts Heinle and Heinle Publishers. PP, 224-261

Leki, L. (1996).Coaching From The Margins; Issues in Written Response. Cambridge; Cambridge University Press.

Murray, Donlad. (1982). “Learning by Teachin” Selected Articles Writing and Teaching Portsmouth: Hesinman Educational Book. Inc PP3,4,8,15,27,77,140-142.

Nunan, David. (1989) Language Teaching Methodology: a Text Book for teachers Singl wood cliffs prentice Hall International (UK) Ltd.

Raimes, Ann (1983) Techniques in Teaching Writing. New York: Oxford University Press.

Richards, J.C. (1986) Approach and Methods in Language. Teaching. Cambridge: Languag Teaching Library.

Richards, J.C. (1990) The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge Universi Press. PP. 108-114.

Silva, Tony. (1990). “Second Language composition Instruction Developments. Issues and Directions in ESL” Second Language Writing (ed). Barbara Kroll: Cambridge Cup. P11

Swales, J. (1990). Genre Analysis English in Academic and Research Settings.Cambridge,UK Cambridge university press.

Van, L. (1988) The Classroom and the Language Learner. London: Longman.

Yan, (2005). Aprocess genre approach to teaching writing;http:// WWW.researchgate.net publication.

# አባሪዎች

# አባሪ

# የምልከታ መረጃዎች

## አባሪ ሀ

### 4.2.1. በምድብ 1 የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 1

ምልከታ የተካሄደበት ቀን 25-6-2015 ዓ.ም

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 1ኛው

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህርት አንድ

የመጀመሪያ ምልከታ

መምህርቷ ለተማሪዎች የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡

ርዕስ፡- ክፍል 4 ጽሕፈት የአስተዋፅኦ ምንነት ተማሪዎችን በፍቃደኝነት ጠየቁ፡፡ ሁለት ተማሪዎች የራሳቸውን ግንዛቤ ገለፁ፡፡ መምህርቷ ጥሩ ነው ብለው ተማሪዎቹን አበረታቱ፡፡ ከዚያም ለተማሪዎቻቸው ስለ አስተዋጽኦ ምንነትና የጽህፈት አፃፃፍ ደረጃዎች (ማሰላሰል፣ ማርቀቅ፣ መከለስ)፤ በማሰላሰል ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ርዕስ መምረጥ፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ በማርቀቅ ደረጃ በፅሁፍ ላይ ያሉ የተለያዩ ስህተቶችን ነቅሶ በማውጣት የቃላት ድግግሞሽ፣የሀሳብ መጣረዝ፣ የፊደል ግድፈትና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን የሚያርሙበት ደረጃ እንደሆነ ማብራሪያ አቀረቡ፡፡ በመጽሐፉ የተቀመጠውን የአስተዋፅኦ አነዳደፍ ምሳሌ ለተማሪዎች አስረዱ፡፡

በመጨረሻም የክፍለ ጊዜው ማብቂያ ደወል በመደወሉ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ በመፅሀፋቸዉ ገጽ 66 ላይ የቀረበውን ምሣሌ መሠረት በማድረግ አስተዋፅኦ እንዲነድፉ በተጨማሪ ጋብቻ በጎሩ ብሔረሰብ እና የልቅሶ ሥርዓት በጎሩ ብሔረሰብ ከሚሉ ሁለት ርዕሶች እንዱን መርጠው

አስተዋፅኦ በመንደፍ ከሦስት አንቀጽ ባልበለጠ አስረጂ ጽሁፍ ፅፈው እንዲመጡ የቤት ሥራ ከሰጡ በኋላ እኔም መምህርቷም ተከታትለን ከክፍል ወጣን፡፡

ምድብ 1

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 27-6-2011 ዓ.ም

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 4ኛው

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህርት አንድ

ሁለተኛ ምልከታ

መምህርቷ ለተማሪዎች የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ ጥቁር ሰሌዳውን አፀዱ፡፡ ቀንና የትምህርቱን ዓይነት ፃፉ፡፡ ያለፈውን በማስታወስ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ባለፈው ትምህርታችን ስለ አስተዋፅኦ አነዳደፍና ስለ ጽህፈት አፃፃፍ ደረጃዎች ተነጋግረን የቤት ስራ ሰርታችሁ እንድትመጡ የቤት ስራ ሰጥቻችሁ ነበር በማለት ለማረጋገጥ ጠየቁ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ተሰጥቶናል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ዝም አሉ፡፡ የቤት ስራ የሰራችሁ እጃችሁን አውጡ በማለት ተናገሩ፡፡ ጥቂት ተማሪዎች እጃቸዉን አወጡ፡፡ ላልሰሩ ተማሪዎች እናንተ በሚቀጥለው ቀን ሰርታችሁ ካልመጣችሁ ከክፍል አስወጣችኋለሁ በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጡ፡፡

ከዚያም የፃፈውን ገላጭ ድርሰት የሚያነብልኝ በማለት በፍቃደኝነት ጠየቁ፡፡ ተማሪዎቹ እኔ ላንብብ በማለት ተንጫጩ፤ከዚያም እድሉን ለአንዲት ሴት ተማሪ ሰጡ፡፡ ተማሪዋ እኔ የፃፍኩት በጋብቻ ሥርዓት ላይ ነው በማለት ያዘጋጀችውን አስተዋፅኦና ረቂቅ አነበበች፡፡ መምህርቷ በተማሪዋ አስተዋፅኦና ረቂቅ ላይ ጥሩ ነው፤ ነገር ግን አስተዋፅኦው በጣም ጠባብ በመሆኑ ዝርዝር ጽሁፍ ለመጻፍ አስቸጋሪ ሆነብሽ፤በማለት ቃላዊ መጋቢ ምላሽ ሰጡ፡፡ በመቀጠል ተረኛ ለሆነው ወንድ ተማሪ እድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪው የፃፈውን አስተዋፅኦና ረቂቅ ጽሁፍ አንብቦ እንደጨረሰ መምህርቷ በተማሪው ስራ ላይ ምንም አይነት መጋቢ ምላሽ ሳይሰጡ አቋርጠው ለሁለት ደቂቃ ስለ አስተዋጽኦ አፃፃፍ ማስታወስ ጀመሩ፡፡

ከዚያም ለቀጣዩ ተማሪ እድሉን ሰጡ፣ተማሪው ረቂቁን ማንበብ ጀመረ፣ከዚያም መምህሩ በቅድሚያ አስተዋፅኦውን ማንበብ እንዳለበት አስታወሱት፣ ተማሪውም ስለ ጎፋ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ያዘጋጀውን አስተዋፅኦ እና ረቂቅ ጽሁፍ አነበበ፡፡

ቀጣዩ ተማሪ ደግሞ ስለጋብቻ ሥርዓት የሚያሳይ አስተዋፅኦና ረቂቅ ጽሁፍ አሰማ፤መምህርቷ በፊት ከተነበቡት ጽሁፎች ሁሉ የተሻለ እንደሆነ በመግለጽ ለቀጣዩዋ ተማሪ እንድታነብ ፈቀዱ፡ ፡ ተማሪዋ አስተዋፅኦ እንዳላዘጋጀች ተናገረች፤ መምህርቷም አስተዋፅኦ ባትጽፍም ረቂቁን እንድታነበው አዘዙ፤ተማሪዋ ስለ ጎፋ ብሔረሰብ ለቅሶ ሥርዓት የሚገልጸውን ረቂቅ ጽሁፍ አንብባ እንደጨረሰች ጥሩ ነው፤ ነገር ግን አስተዋፅኦውን አስቀድመሽ ብትሰሪ የተሻለ ጽሁፍ መጻፍ ትችያለሽ በማለት አስተያየት ሰጡ፡፡ መምህርቷ ለተረኛዋ ተማሪ ዕድሉን ሰጡ፤ተረኛዋ ተማሪም እኔም አስተዋጽኦ አልሰራሁም በማለት ተናገረች፤ከዚያም ስለ ጋብቻ ሥርዓት የሚገልጸውን ጽሁፍ አንብባ ጨረሰች፡፡ መምህርቷ ለተማሪዋ ድርሰት በሚጻፍበት ጊዜ የሀሳብ ትስስር እንዲኖረው ለማድረግ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን መጠቀም እንዳለባት አስተያየት ሰጡ፡፡

በመጨረሻም መምህርቷ አንዲት ሴት ተማሪ እንድትነሳ አዘዙ፣ተማሪዋ ደብተሯ ላይ የሞከረችው ነገር ባለመኖሩ የምትናገረው ነገር ከንግግር ቃላት የዘለሉ አይደሉም፡፡ ንግግሯ ይቆራረጣል፡፡

ተማሪዎች በመሀል ሳቁ፡፡ መምህርቷ አንብቢ የጻፍሽውን በማለት በድጋሚ ጠየቁ፤ተማሪዋ የቤት ስራውን ባለመስራቷ በቃል መግለጽ ስላልቻለች አቋርጣ ተቀመጠች፡፡ በመጨረሻም የእለቱ ክፍለ ጊዜ በመጠናቀቁ ምንም አይነት ማጠቃለያ ሀሳብ ሳይሰጡ ደወል በመደወሉ ምክንያት ተሰናብተው ከክፍል ወጡ፡፡

ምድብ 1

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 1

ምልከታ የተካሄደበት ቀን 29-6-2011 ዓ.ም

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 1ኛው

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህርት አንድ

ሶስተኛ ምልከታ

መምህርቷ ለተማሪዎች የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኂላ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡

ርዕስ፡- ክፍል 4 ጽሕፈት የአስተዋፅኦ ምንነት ተማሪዎችን በፍቃደኝነት ጠየቁ፡፡ ሁለት ተማሪዎች የራሳቸውን ግንዛቤ ገለፁ፡፡ መምህርቷ ጥሩ ነው ብለው ተማሪዎቹን አበረታቱ፡፡ ከዚያም ለተማሪዎቻቸው ስለ አስተዋጽኦ ምንነትና በጽህፈት አፃፃፍ ደረጃዎች(ማሰላሰል፣ ማርቀቅ፣ መከለስ)፣ በማሰላሰል ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ርዕስ መምረጥ፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ በማርቀቅ ደረጃ በፅሁፍ ላይ ያሉ የተለያዩ ስህተቶችን ነቅሶ በማውጣት የቃላት ድግግሞሽ፣የሀሳብ መጣረዝ፣ የፊደል ግድፈትና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን የሚያርሙበት ደረጃ እንደሆነ ማብራሪያ አቀረቡ፡፡ በመጽሐፉ የተቀመጠውን የአስተዋፅኦ አነዳደፍ ምሳሌ ለተማሪዎች አስረዱ፡፡

በመጨረሻም የክፍለ ጊዜው ማብቂያ ደውል በመደወሉ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ በመፅሀፋቸዉ ገጽ 76 ላይ የቀረበውን ምሣሌ መሠረት በማድረግ አስተዋፅኦ እንዲነድፉና በተጨማሪም ተማሪዎች በአከባቢያቸው ካዩት ነገር ርዕስ መርጠው አስተዋፅኦ በመንደፍ ከሁለት አንቀጽ ባልበለጠ አስረጂ ጽሁፍ ፅፈው እንዲመጡ ትዕዛዝ ተሰጣቸውና ሰዓቱ ስለተጠናቀቀ ተሰናብተው ወጡ፡፡

# አባሪ ለ

## 4.2.2. በምድብ 6 የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 6

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 23-7-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 4ኛው

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህርት ሁለት

የመጀመሪያ ምልከታ

በቅድሚያ የተከበረውን ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ርዕስ የአስተዋፅኦ አነዳደፍ ስልት መምህርቷ ስለ አጻጻፍ ስልቶች ገለጻ አደረጉ፡፡ ስለገላጭ ድርሰት ምንነትና ባህሪያት ጥያቄ ጠየቁ፡፡ ተማሪዎች መልስ ሰጡ፡፡ ከዚያም ተጨማሪ ማብራሪያ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፉ፡፡ ተማሪዎች ማስታወሻ ያዙ፡፡ በመቀጠል ስለ ድርሰት አጻጻፍ ደረጃዎች ጠየቁ፡፡ ተማሪዎች ምላሽ ሰጡ፡፡ መምህርቷ ስለቅድመ ጽህፈት ደረጃ እና ተግባራት በቅድመ ጽህፈት መከናወን ያላባቸውን ተግባራት ርዕስ መምረጥ፣ ሀሳብ ማሰባሰብ፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ በመጻፍ ሂደት ደግሞ አስተዋጽኦውን መሰረት በማድረግ መጻፍ፣በድህረ ጽህፈት ደግሞ የጻፉትን ረቂቅ ደጋግሞ በማንበብ የሚታዩ ጉድፎችን ምሳሌ የሰዋሰው ስህተት፣ የሀሳብ አለመስማማት፣የስርዓተ ነጥብና የመሳሰሉት የሚስተካከሉበትና የሚቃኑበት ደረጃ እንደሆነ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

በመቀጠልም በገጽ 66 ላይ ያለውን ምሣሌ በማየት በተመሣሣይ አስተዋፅኦ በመንደፍ በመረጡት ርዕስ ገላጭ አንቀጽ እንዲጽፋ አዘዙ፡፡ በሚጽፋበት ጊዜ ሰው ጠይቀውና መጽሀፍ አንብበው ሀሳብ አሰባስበው አንቀጽ መጻፍ እንዳለባቸው መመሪያ ሰጡ፡፡ የምትጽፉት ከዚህ ክፍለ ጊዜ በፊት በተዋቀረውና በስምንት ቡድን ነው፡፡ መምህርቷ ሥራው ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ እንደሆነ ተናግረው ክፍለ ጊዜው ስለተጠናቀቀ ከክፍል ወጡ፡፡

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 6

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 24-7-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህርት ሁለት

የሁለተኛ ምልከታ

በመጀመሪያ የተለመደውን ሰላምታቸውን አቀረቡ። ጥቁር ሰሌዳውን አጸዱ ።ያለፈውን ትምህርት አስታወሱ። የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ። ባለፈው ትምህርታቸው በቡድን ሆናችሁ በመረጣችሁት ርዕስ ገላጭ አንቀጽ ጽፋችሁ እንድትመጡ የቤት ሥራ ሰጥቻችሁ ነበር በማለት መምህሩ አስታወሷቸው። ሁሉም ተማሪዎች ድምጻቸዉን ከፍ አድርገው መልስ ሰጡ። በመቀጠል እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት በቡድን እንዲቀመጡ አዘዙ። ተማሪዎች በቡድን ለመቀመጥ ተንጫጨ፤ ከ2 ደቂቃ በኂላ ጫጫታው ቀነሰ።

በመቀጠል መምህርቷ አንድ ቡድን ከሌላ ቡድን ጋር የጻፋትን ፅሁፍ እንዲቀያየሩ አዘዙ። ተማሪዎች የጻፉትን ጽሁፍ ተቀያየሩ። የጻፉትን አንቀጽ አንብበው፤ በአንቀጹ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ነቅሰው እንዲያወጡ አዘዙ። የተማሪዎች ድምጽ ከፍ ብሎ ተሰማ። ከፊሎች ይንጫጫሉ ግማሾቹ ደግሞ የተሰጠውን ስራ ለመስራት ይሞክራሉ።

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 6

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 25-7-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህርት ሁለት

ሶስተኛ ምልከታ

በመጀመሪያ የተለመደውን ሰላምታቸውን አቀረቡ፡፡ ጥቁር ሰሌዳውን አጸዱ ፡፡ያለፈውን ትምህርት አስታወሱ፡፡ የዕለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ባለፈው ትምህርታቸው በቡድን ሆናችሁ በመረጣችሁት ርዕስ ገላጭ አንቀጽ ጽፋችሁ እንድትመጡ የቤት ሥራ ሰጥቻችሁ ነበር በማለት መምህሩ አስታወሷቸው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ድምጻቸዉን ከፍ አድርገው መልስ ሰጡ፡፡ በመቀጠል እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት በቡድን እንዲቀመጡ አዘዙ፡፡ ተማሪዎች በቡድን ለመቀመጥ ተንጫጩ፤ ከ2 ደቂቃ በኂላ ጫጫታው ቀነሰ፡፡

በመቀጠል መምህርቷ አንድ ቡድን ከሌላ ቡድን ጋር የጻፋትን ፅሁፍ እንዲቀያየሩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎች የጻፉትን ጽሁፍ ተቀያየሩ፡፡ የጻፉትን አንቀጽ አንብበው በአንቀጹ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ነቅሰው እንዲያወጡ አዘዙ፡፡ የተማሪዎች ድምጽ ከፍ ብሎ ተሰማ፡፡ ከፊሎች ይንጫጫሉ ግማሾቹ ደግሞ የተሰጠውን ስራ ለመስራት ይሞክራሉ፡፡

መምህርቷ እየተዘዋወሩ ለተማሪዎቻቸው ድጋፍ መስጠት ጀመሩ፡፡ ከዚያም የፈቀዱላቸው 20 ደቂቃ ሲያበቃ የተቀያየሩትን ጽሁፍ እንዲመላለሱ አደረጉ፡፡ በመቀጠል በእያንዳንዱ ቡድን መሪ አማካኝነት ፅሁፉን እንዲያነቡ አደረጉ፡፡ መምህርቷ ሌላ የቡድን አባላት አስተያየት እንዲሰጡበት አደረጉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰማቸውን አስተያየት ሰጡ፡፡

በመጨረሻም የክፍለ ጊዜው ማብቂያ ደውል በመደወሉ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ በመፅሀፋቸዉ ገጽ 76 ላይ የቀረበውን ምሣሌ መሠረት በማድረግ አስተዋፅኦ እንዲነድፉና በተጨማሪም ተማሪዎች በአከባብያቸው ካዩት ነገር ርዕስ መርጠው አስተዋፅኦ በመንደፍ ከሁለት አንቀጽ ባልበለጠ አስረጂ ጽሁፍ ፅፈው እንዲመጡ ትዕዛዝ ተሰጣቸውና ሰዓቱ ስለተጠናቀቀ ተሰናብተው ወጡ፡፡

## አባሪ ሐ

### 4.2.3 በምደብ 11 የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 11

ምልከታው የተኮሄደበት ቀን 24-7-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር ሶስት

የመጀመሪያ ምልከታ

በመጀመሪያ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ የእለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ርዕስ አስተዋጽኦ አነዳደፍ ስልት በገጽ ስድሳ ስድስት የቀረበውን ምሳሌ በመመልከት ቢጋር በማዘጋጀት አንድ ሰፋ ያለ አስረጂ ጽሁፍ በመረጡት ርዕስ መፃፍ እንደሚቻል በመንገር የዕለቱን ትምህርት ገለጹ፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎች ወደ ተግባር እንዲገቡ አዘዙ፡፡

በመቀጠል የትምህርቱ ሂደት በቡድን እንደሆነ መመሪያ ሰጡ፡፡ ተማሪዎች በቡድን ለመደራጀት ተንጫጩ፡፡ በገጽ 66 የተጠቀሰውን አስተዋጽኦ በአግባቡ በማጤን በቡድናችሁ በመወያየት በመጀመሪያ ቢጋር ወይም አስተዋጽኦ እንዲጽፉ ታዘዙ፡፡ 25 ደቂቃ እንደሚሰጧቸው ነገሯቸው፡ ፡ ተማሪዎች እንደ ፍላጎታቸው ሶስትም ፣አራትም፣ ሰባትም በቡድን በቡድን በመሆን መወያየት ጀመሩ፡፡ አንዳንዶቹ የሚወያዩት የግል ውይይት ሲሆን ብዙዎቹ በቡድን ከመወያየት ጥንድ ጥንድ ሆነው ይወያዩ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ጸጥ ብለው የሚወያዩትን ያስተውሉ ነበር፡፡

መምህሩ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ ቢጋሩን /አስተዋጽኦ/ እንዴት እንደሚዘጋጁ ይመለከቱ ነበር፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች የሚወያዩት በሌላ ትምህርት ላይ በመሆኑ መምህሩ ከክፍል እንዲወጡ አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም ቅጣቱን ተቀብለው እየሳቁ ከክፍል ወጡ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ያዘጋጁትን ቢጋር እንዴት አስፋፍተው እንደሚጽፉትና እንዴት መከለስ እንዳለባቸው በጽሁፍ ውስጥ የሚታዩ ስህተቶችን የቃላት ፣የፊደል ግድፈት ፣ የሰዋሰው ስህተት፣የሀሳብ ድግግሞሽ፣ የስርአተ ነጥቦችና የመሳሰሉ ችግሮች እንዴት ማቃናትና ማስተካከል እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች ከክፍል ውስጥ በጋራ የሰሩትን ቢጋር መነሻ አድርገው እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት አንቀጽ እንዲጽፉ የቤት ሥራ ሰጧቸው፡፡ ከዚያም ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ደወል ስለተደወለ ከክፍል ለቀው ወጡ፡፡

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 11

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 26-7-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር ሶስት

ሁለተኛ ምልከታ

መምህሩ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ባለፈው ክፍለ ጊዜ የቤት ስራ ሰጥተዋቸው እንደነበረ በማስታወስ ለዛሬ ይህንኑ ትምህርት እንደሚያስኬዱ አስገንዝበው የእለቱን ትምህርት ጀመሩ፡፡ ከዚያም የቤት ስራ የሰሩና ያልሰሩ ተማሪዎችን ለመለየት እየተዘዋወሩ የተማሪዎችን ደብተር መቃኘት ጀመሩ፡፡ ያልሰሩ ተማሪዎችን ስም መዘገቡ፡፡ የሰሩ ተማሪዎች የጻፉትን ፅሁፍ እንዲያነቡ ተጠየቁ፡፡ ተማሪዎች እኔ ላንብብ በማለት ተንጫጩ፡፡

በመቀጠል መምህሩ ለአንድ ተማሪ እንዲያነብ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዉም ባለፈው ትምህርት ክፍለ ጊዜ በጋራ ያዘጋጁትን በጋር ካነበቡ በኋላ የራሱን ረቂቅ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ምንም አይነት መጋቢ ምላሽ ሳይሰጡ ቀጣይዋ ተማሪ እንድታነብ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዋ የድህረ-ገጽ ጠቀሜታ በማለት ርዕሱን ብቻ በመናገር አቋረጠች፡፡ ተማሪዎች በልጅቷ ድርጊት ሳቁ፡፡ ከዚያም መምህሩ ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ጠየቁ፡፡ ተማሪውም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰራውን ቢጋር መሰረት አድርጎ እንደጻፈው በመግለጽ ቀደም ብለው ከቀረቡት ጽሑፎች ስለአንድነት አስፈላጊነት የሚያሳይ ጥሩ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ጥሩ ነው በማለት አበረታቱት፡፡

በመጨረሻም የጻፉትን ጽሁፍ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አቃንተውና አሻሽለው እንዲጽፉና እንደሚታረምላቸው ገልጸው ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ደውል ስለተደወለ የዕለቱን ትምህርት አጠናቀው ከክፍል ወጡ፡፡

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 11

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 27-7-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር ሶስት

ሶስተኛ ምልከታ

መምህሩ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ባለፈው ክፍለ ጊዜ የቤት ስራ ሰጥተዋቸው እንደነበረ በማስታወስ ለዛሬ ይህንኑ ትምህርት እንደሚያስኬዱ አስገንዝበው የእለቱን ትምህርት ጀመሩ፡፡ ከዚያም የቤት ስራ የሰሩና ያልሰሩ ተማሪዎችን ለመለየት እየተዘዋወሩ የተማሪዎችን ደብተር መቃኘት ጀመሩ፡፡ ያልሰሩ ተማሪዎችን ስም መዘገቡ፡፡ የሰሩ ተማሪዎች የጻፉትን ፅሁፍ እንዲያነቡ ተጠየቁ፡፡ ተማሪዎች እኔ ላንብብ በማለት ተንጫጩ፡፡

በመቀጠል መምህሩ ለአንድ ተማሪ እንዲያነብ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዉም ባለፈው ትምህርት ክፍለ ጊዜ በጋራ ያዘጋጁትን ቢጋር ካነበቡ በኋላ የራሱን ረቂቅ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ምንም አይነት መጋቢ ምላሽ ሳይሰጡ ቀጣይዋ ተማሪ እንድታነብ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዋ የድህረ-ገጽ ጠቀሜታ በማለት ርዕሱን ብቻ በመናገር አቋረጠች፡፡ ተማሪዎች በልጅቷ ድርጊት ሳቁ፡፡ ከዚያም መምህሩ ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ጠየቁ፡፡ ተማሪውም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰራውን ቢጋራ መሰረት አድርጎ እንደጻፈው በመግለጽ ቀደም ብለው ከቀረቡት ጽሑፎች ስለአንድነት አስፈላጊነት የሚያሳይ ጥሩ ጽሁፍ አነበበ ፡፡ መምህሩም ጥሩ ነው በማለት አበረታቱት፡፡

በመጨረሻም የጻፉትን ጽሁፍ ለተማሪዎች ምንም አይነት ምጋቢ ምላሽ ሳይሰቷቸው ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ደውል ስለተደወለ የዕለቱን ትምህርት አጠናቀው ከክፍል ወጡ፡፡

## አባሪ መ

### 4.2.4. በምድብ 16 የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 16

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 13-8-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር አራት

የመጀመሪያ ምልከታ

መምህሩ ወደ ክፍል ሲገቡ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ ጥቁር ሰሌዳውን አጽድተው የክፍል ስራ ብለው ጻፉ፡፡ ክፍል ሶስት መጻፍ፡፡ ርዕስ ፡- አስተዋጽኦ መንደፍ የሚሉትን ሐረጋት ጻፉ ፣ ከዚያም የሚከተለውን ትዕዛዝ ጻፉ ፡፡ ከሚከተሉት ሁለት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ገላጭ ድርሰት ጻፉ፡፡ አንደኛ የሥልጣኔ ምንነት ሁለተኛ የበጎ ፈቃደኝነት አስተዋጽኦ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ደብተራቸውን አውጥተው ለመጻፍ ተዘጋጁ፡፡ መምህሩ ተማሪዎች ጽፈው የሚጨርሱበት ጊዜ 30 ደቂቃ እንደሆነ ገለጹ፡፡

ከዚያም ከተማሪዎቹ አንዱ እጁን በማውጣት በተሰጠን ጊዜ ለእራሳችን ርዕስ መርጠን እንድንጽፍ ይፍቀዱልን ሲል ጠየቀ፡፡ የተወሰኑ ተማሪዎች የተማሪው ጥያቄ ትክክል መሆኑን በማጉረምረም ገለጹ፡፡ መምህሩም አሁን የተሰጣችሁን የክፍል ስራ በሚቀጥለው ጊዜ ሰው ጠይቃችሁ ወይም መጽሐፍ አንብባችሁ ጽፋችሁ እንድትመጡ በማለት አዘዙ፡፡ ለአሁኑ ግን በምትፈልጉት ርዕስ መጻፍ አትችሉም በማለት ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ ዕድሉን አልሰጧቸውም፡፡

ስለዚህ ተማሪዎችም በተሰጣቸው ርዕስ መጻፍ ጀመሩ፡፡ የተፈቀደላቸው ሰዓት በመጠናቀቁ መምህሩ ሰዓት አልቋል ብለው ተናገሩ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች አልጨረስንም በማለት ተናገሩ መምህሩ በድጋሚ የተፈቀደው ጊዜ ማለቁን ገለጹ፡፡ በመቀጠል በቀሪው ሰዓት የፃፉትን ገላጭ ድርሰት እንዲያነቡ ጠየቁ፡፡ አንድ ተማሪ ተነስቶ ጠለፋ ጎጅ ባህል ነው ሲል ማንበብ ጀመረ፡፡ አንብቦ እንደጨረሰ ርዕሱ ጥሩ ነው በጽሁፉ ውስጥ ያለውን ድግግሞሽ በማስወገድ አያያዥ

ቃላትን ተጠቅመህ በዐረፍተነገሮች መካከል ጥብቅ ትስስር በመፍጠር ጥሩ ጽሁፍ መጻፍ ትችላለህ ሙከራው ጥሩ ነው በማለት አስተያየት ሰጡ፡፡

በመቀጠል ዕድሉ የተፈቀደላት ተማሪ የጻፈችው ጽሁፍ ርዕስ የአካባቢ እንክብካቤ ጠቀሜታ የሚል ነበር፡፡ ተማሪዋ አንብባ እንደጨረሰች መምህሩ ጥሩ ነው በማለት አበረታቷት፡፡

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 16

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 16-8-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ
የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ
መምህር አራት
ምልከታ ሁለት
መምህሩ ወደ ክፍል ሲገቡ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የቤት ሥራ ሰርተው መምጣታቸውን ጠየቁ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ሰርተናል የሚል መልስ ሰጡ፡፡ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ዝም አሉ፡፡ መምህሩም ያልሰራችሁ ተማሪዎች እጃችሁን አንሱ በማለት ጠየቁ፡፡ ጥቂት ተማሪዎች እጃቸውን አነሱ፡፡ መምህሩ ለምን እንዳልሰሩ ጠየቋቸው፡፡ የቤት ስራ የተሰጠ ዕለት በክፍል ውስጥ አለመኖራቸውን ተናገሩ፡፡ ያልሰሩ ተማሪዎችን ስም መዘገቡ፡፡

በመቀጠል የሰሩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ጠየቁ፡፡ የመጀመሪያዋ ተማሪ የጻፈችው ስለ በጎ ፈቃደኝነት ጠቀሜታ ይገልጻል፡፡ ተማሪዋ አንብባ እንደጨረሰች መምህሩ ልትጽፍበት በተነሳሽበት ርዕስ ለመጻፍ አስተዋጽኦ አውጥተሽ ብትጽፊ ኖሮ የተሻለ ጽሁፍ መጻፍ ትችያለሽ በማለት አስተያየት ሰጡ፡፡ ቀጣዩ ተማሪ ስለ ሥልጣኔ ምንነት የጻፈውን ማንበብ ጀመረ፡፡ ተማሪው ሲያነብ ድምጹን ባለማሰማቱ ተማሪዎች ተንጫጩ፡፡ መምህሩ ተማሪው ማንበቡን እንዲያቋርጥ ካደረጉ በኋላ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲያቡ አዘዙ፡፡ ተማሪውም እንደገና ማንበብ ጀመረ፡፡ አንብቦ እንደጨረሰ መምህሩ ጥሩ ነው ነገር ግን በዐረፍተ ነገር መካከል አያያዥ ቃላትን ስላልተጠቀምክ ዐረፍተ ነገሮች የእርስ በእርስ ትስስር የላቸውም፡፡

ስለዚህ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም በዐረፍተ ነገሮች መካከል ጥብቅ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ መጻፍ ተገቢ ነው፡፡ በማለት ቃላዊ መጋቤ ምላሽ ሰጡ፡፡

በመቀጠልም አንድ ተማሪ ሁለቱን ርዕስ በአንድ ላይ በማገናኘት የስልጣኔ ምንነትና በጎ ፈቃደኝነት በሚል የጻፈውን ገላጭ ጽሁፍ ማንበብ ጀመረ፡፡ ተማሪው አንብቦ እንደጨረሰ

መምህሩ ካለን ጊዜ አንጻር የሁላችሁንም ስራ ማየት ስለማንችል በትርፍ ጊዜአችሁ በክፍልና ከክፍል ውጭ እርስ በእርሳችሁ ተናበቡ በማለት አሳስበው የእለቱን ትምህርት አጠናቀው ከክፍል ወጡ፡፡

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 16

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 18-8-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ
መምህር አራት
ምልከታ ሶስት
መምህሩ ወደ ክፍል ሲገቡ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የቤት ሥራ ሰርተው መምጣታቸውን ጠየቁ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ሰርተናል የሚል መልስ ሰጡ፡፡ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ዝም አሉ፡፡ መምህሩም ያልሰራችሁ ተማሪዎች እጃችሁን አንሱ በማለት ጠየቁ፡፡ ጥቂት ተማሪዎች እጃቸውን አነሱ፡፡ መምህሩ ለምን እንዳልሰሩ ጠየቋቸው፡፡ የቤት ስራ የተሰጠ ዕለት በክፍል ውስጥ አለመኖራቸውን ተናገሩ፡፡ ያልሰሩ ተማሪዎችን ስም መዘገቡ፡፡

በመቀጠል የሰሩ ተማሪዎች እንዲያነቡ ጠየቁ፡፡ የመጀመሪያዋ ተማሪ የጻፈችው ስለ በጎ ፈቃደኝነት ጠቀሜታ ይገልጻል፡፡ ተማሪዋ አንብባ እንደጨረሰች መምህሩ ልትጽፍበት በተነሳሽበት ርዕስ ለመጻፍ አስተዋጽኦ አውጥተሽ ብትጽፊ ኖሮ የተሻለ ጽሁፍ መጻፍ ትችያለሽ በማለት አስተያየት ሰጡ፡፡ ቀጣዩ ተማሪ ስለ ሥልጣኔ ምንነት የጻፈውን ማንበብ ጀመረ፡፡ ተማሪው ሲያነብ ድምጹን ባለማሰማቱ ተማሪዎች ተንጫጩ፡፡ መምህሩ ተማሪው ማንበቡን እንዲያቋርጥ ካደረጉ በኋላ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲያነቡ አዘዙ፡፡ ተማሪውም በታዘዘው መሰረት ድምጹን ከፍ አድረጎ ማንበብ ጀመረ፡፡ መምህሩም ጽሁፉን ካዳመጡ በኋላ ጥሩ ነው በማለት አበረታቱ፡፡

በመቀጠልም አንድ ተማሪ ሁለቱን ርዕስ በአንድ ላይ በማገናኘት የስልጣኔ ምንነትና በጎ ፈቃደኝነት በሚል የጻፈውን ገላጭ ጽሁፍ ማንበብ ጀመረ፡፡ ተማሪው አንብቦ እንደጨረሰ መምህሩ ካለን ጊዜ አንጻር የሁላችሁንም ስራ ማየት ስለማልችል በትርፍ ጊዜአችሁ በክፍልና ከክፍል ውጭ እርስ በእርሳችሁ ተናበቡ በማለት አሳስበው የእለቱን ትምህርት አጠናቀው ከክፍል ወጡ፡፡

## አባሪ ሠ

### 4.2.5. በምደብ 21 የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ምልከታ

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 21

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 5-9-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር አምስት

የመጀመሪያ ምልከታ

በመጀመሪያ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ የእለቱን ትምህርት አስተዋወቁ፡፡ ርዕስ አስተዋጽኦ አነዳደፍ ስልት ፡- በገጽ ስድሳ ስድስት የቀረበውን ምሳሌ ቢ.ጋር ለተማሪዎች በማስረዳት ተማሪዎች ተመሳሳይ ቢ.ጋር በማዘጋጀት ሦስት አንቀጽ ያለው አስረጂ ጽሁፍ በመረጡት ርዕስ መፃፍ እንደሚቻል በማዘዝ የዕለቱን ትምህርት ደመደሙ፡፡ ወደ ተግባር እንዲገቡ ተማሪዎችን አዘዙ፡፡

አቀማመጣቸው በቡድን እንዲሆንና በቡድን እንዲሰሩ መመሪያ ሰጡ፡፡ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም በነበራቸው ቡድን ተደራጁ፡፡ የተማሩትን የአስተዋጽኦ አነዳደፍ በአግባቡ በማጤን በቡድናቸው በመወያየት በመጀመሪያ ቢ.ጋር ወይም አስተዋጽኦ እንዲጽፉ ታዘዙ 20 ደቂቃ እንደሚሰጧቸው ነገሯቸው፡፡ ተማሪዎች በቡድን በመሆን መወያየት ጀመሩ፡፡ ውይይታቸው ግን የተዘበራረቀ ነበር ፣ አንዳንዶቹ የሚወያዩት የግል ውይይት ሲሆን ብዙዎቹ በቡድን ሆነው በተሰጠው ተግባር አተኩረው ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ጸጥ ብለው የሚወያዩትን ያስተውሉ ነበር፡፡

መምህሩ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ ቢ.ጋሩን /አስተዋጽኦ/ እንዴት እንደሚዘጋጁ ይመለከቱ ነበር፡፡ መምህሩ የተቸገሩ ቡድኖችን ይረዱ ነበር፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ያዘጋጁትን ቢ.ጋር እንዴት አስፋፍተው እንደሚጽፉትና እንዴት መከለስ እንዳለባቸው በጽሁፍ ውስጥ የሚታዩ ስህተቶችን የቃላት ፣የፊደል ግድፈት ፣ የሰዋሰው ስህተት፣የሀሳብ ቅድድሞሽ፣

የስርአተ ነጥቦችና የመሳሰሉ ችግሮች እንዴት ማቃናትና ማስተካከል እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

በመጨረሻም ጊዜው በቂ በለመሆኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በጋራ የሰሩትን ቢጋር መነሻ አድርገው በክፍል እንዲጽፉ የታዘዙትን የቤት ሥራ እንዲሆን ሰጧቸው፡፡ ከዚያም ክፍል ለቀው ወጡ፡፡

ምልከታው የተካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 21

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 7-9-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር አምስት

ሁለተኛ ምልከታ

መምህሩ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ባለፈው ክፍለ ጊዜ የቤት ስራ ሰጥተዋቸው እንደነበረ በማስታወስ ለዛሬ ይህንኑ ትምህርት እንደሚቀጥሉ አስገንዝበው የዕለቱን ትምህርት ጀመሩ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች የጻፉትን ፅሁፍ እንዲያነቡ ተጠየቁ፡፡ ተማሪዎች እጅ በማውጣት ቅድሚያ ለማግኘት ሞከሩ፡፡ መምህሩ የመጀመሪያውን ዕድል ለአንድ ወንድ ተማሪ እንዲያነብ ሰጡ፡፡ ተማሪዉ ባለፈው ትምህርት ክፍለ ጊዜ በጋራ ያዘጋጁትን ቢጋር ካነበበ በኋላ የራሱን ረቂቅ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ምንም አይነት መጋቢ ምላሽ ሳይሰጡ ቀጣይዋ ተማሪ እንድታነብ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዋ ስለ ሥርዓተ ፆታ ያዘጋጀቺውን አነበበች፡፡ ከዚያም መምህሩ ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ጠየቁ፡፡ ተማሪውም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰራውን ቢጋር መሰረት አድርጎ እንደጻፈው በመግለጽ ቀደም ብለው ከቀረቡት ጽሑፎች ስለኢትዮጵያዊነት የሚያሳይ ጥሩ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ጥሩ ነው በማለት አበረታቱት፡፡ በተጨማሪ ለሁለት ተማሪዎች በየተራ ዕድል ሰጡ፣ ተማሪዎቹም ርዕሳቸውን፣ ቢጋራቸውንና ጽሁፋቸውን አቀረቡ መምህሩ ግን ምንም ሀሳብ አልሰጡም፡፡ በመጨረሻም የጻፉትን ጽሁፍ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አቃንተውና አሻሽለው እንዲጽፉና ሰብስበው እንደሚያዩ ገልጸው ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ተሰናብተው ወጡ፡፡

ምልከታው የካሄደበት የክፍል ደረጃ 9ኛ ምድብ 21

ምልከታው የተካሄደበት ቀን 8-9-2011

ምልከታው የተካሄደበት ክፍለ ጊዜ 5ኛ

የጊዜ ርዝማኔ 42 ደቂቃ

መምህር አምስት

ሶስተኛ ምልከታ

መምህሩ የተለመደውን ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ባለፈው ክፍለ ጊዜ የቤት ስራ ሰጥተዋቸው እንደነበረ በማስታወስ ለዛሬ ይህንኑ ትምህርት እንደሚቀጥሉ አስገንዝበው የዕለቱን ትምህርት ጀመሩ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች የጻፉትን ፅሁፍ እንዲያነቡ ተጠየቁ፡፡ ተማሪዎች እጅ በማውጣት ቅድሚያ ለማግኘት ሞከሩ፡፡ መምህሩ የመጀመሪያውን ዕድል ለአንድ ወንድ ተማሪ እንዲያነብ ሰጡ፡፡ ተማሪዉ ባለፈው ትምህርት ክፍለ ጊዜ በጋራ ያዘጋጁትን ቢጋር ካነበበ በኋላ የራሱን ረቂቅ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ምንም አይነት መጋቢ ምላሽ ሳይሰጡ ቀጣይዋ ተማሪ እንድታነብ ዕድሉን ሰጡ፡፡ ተማሪዋ ስለ ሥርዓተ ፆታ ያዘጋጀችውን አነበበች፡፡ ከዚያም መምህሩ ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ጠየቁ፡፡ ተማሪውም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰራውን ቢጋር መሰረት አድርጎ እንደጻፈው በመግለጽ ቀደም ብለው ከቀረቡት ጽሑፎች ስለኢትዮጵያዊነት የሚያሳይ ጥሩ ጽሁፍ አነበበ፡፡ መምህሩም ጥሩ ነው በማለት አበረታቱት፡፡ በተጨማሪ ለሁለት ተማሪዎች በየተራ ዕድል ሰጡ፣ ተማሪዎቹም ርዕሳቸውን፣ ቢጋራቸውንና ጽሁፋቸውን አቀረቡ መምህሩ ግን ምንም ሀሳብ ሳይሰጡ ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ተሰናብተው ወጡ፡፡

# አባሪ ረ

ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀ ቢጋር/check list/

1.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ እንድጽፉ በርዕሰ ጉዳዩ ከብጤዎቻቸው ጋር እንድወያዩ ያበረታታሉ?----------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------2.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች አንድን ነገር ተመልክተው ወይም አጥንተው ሀሳብ በማሰባሰብ ጽፈው እንድያቀርቡ ያዛሉ?-----------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------

3.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ደብዳቤ ፣ዘገባ፣የፈጠራ ሥራና ወዘተ ተወያይተው እንዲጽፉ ያበረታታሉ?----------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------4.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በማቀድ፣በማርቀቅና በማረም ሂደት በማለፍ መጻፍ እንዲችሉ በማበረታታት ያስተምራሉ?-------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------5.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ የጽህፈት ትምህርት የሚያስተምሩት አብዛኛውን ጊዜ ሂደት ላይ በማትኮር ወይስ ውጤት ተኮር ላይ በማተኮር?--------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------6.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች ጽህፈት በሚጽፉበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለተማሪዎች ይጠቁማሉ?---------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------7.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ የጽህፈት ትምህርት ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ስለሚጽፉበት ርዕስ፣ይዘትና ዓላማ ወስነው ይናገራሉ?----------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------8.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች ጽህፈትን ሲጽፉ የሚፈጽሙትን ስህተት እራሳቸው እንዲያርሙ ያለማምዷቸዋል?----------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------9.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድ ተነስተው የሚጽፉበትን ርዕስ እንዲፈልጉ ያበረታታሉ?------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------10.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ተማሪዎች ጽህፈትን ሲጽፉ ስራው የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ያሳውቃሉ?-------------------------------------------------------------------------------11.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ የጽህፈት ህጎችን የአጻጻፍ ስልቶችን ያስተምራሉ?------12.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ የአጻጻፍ ሂደትን የማቀድ፤ማርቀቅ፤መከለስና ማቃናት ተግባራትን ያስተምራሉ?------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------13.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ጽህፈትን ሲያስተምሩ በሰዋሰው ትክክለኛነት ላይ ያተኩራሉ? ------------------------------------------------------------------

--------------------------14.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ ጽህፈትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች አካላዊና ስነልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያበረታታሉ?-----------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-15.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ በጽህፈት ትምህርት ሂደት አብዛኛውን የተማሪዎችን ስህተት በማቃናት እና በማረም ላይ ያተኩራሉ?------------------------------------------------16.የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ቷ በትምህርቱ ሂደት የአጨራረስ ሂደትን ያስተምራሉ-------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ ሰ

## ለመምህራን የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በአርባ ምንጭ ዙሪያ ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የድርሰት ትምህርት አቀራረብ ተግባራዊነት ለመፈተሽ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦ ነው ፡፡ ስለዚህ ከዚህ በማስተከል በዝርዝር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ ስራ እገዛዎ እንዳይለየኝ በአክብሮትና በትህትና አደራ እላለሁ ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ውድ ጊዜዎን መስዋእት በማድረግ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ስለተባበሩኝ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስዎ፡፡

- ማሳሰቢያ
- መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም
- አጠቃላይ መመሪያ

ይህ የጽሁፍ መጠይቅ ሦስት ክፍሎች የያዘ ነው ፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ የሆነ መረጃን የሚጠይቅ ሲሆን ተከታዩ ክፍል ደግሞ ሦስት አማራጮችን የያዙ ጥያቄዎች የያዘ ነው ፡፡ የመጨረሻው ክፍል ደግሞ አጭርና ግልጽ መልስ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

**ክፍል አንድ**

1. ፆታ.....
2. ዕድሜ .....
3. የትምህርት ደረጃ.....
4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ አብይ...... ንዑስ......
5. በመምህርነት ያገለገለበት ዓመት ብዛት......
6. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም......
7. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ...... የምድብ ብዛት-----
8. የክፍለ ጊዜ ብዛት......
9. በጊዜው ሙያውን ለማሻሻል ያደረጉት ጥረት ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ይግለጹ
   - 9.1 በወርክሾፕ......
   - 9.2 በተከታታይ ኮርስ (CPD).....
   - 9.3 በሴሚናር......
   - 9.4 በሌላ.....

**ክፍል ሁለት** ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አራት አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል ፡፡ እናንተ የምትሰማሙበትን አማራጭ መልስ በተሰጠው የመልስ መስጫ ሰንጠረዥ (X) ምልክት በማኖር የመረጣችሁትን ምርጫ አመልክቱ ፡፡ አማራጭ መልሶችም፡-

3= ሁልጊዜ አደርጋለሁ 1 = አላደርግም

1 = አልፎ አልፎ አደርጋለሁ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ሁልጊዜ አደርጋለው | አልፎ አልፎ አደርጋሁ | አላደርግም |
|---|---|---|---|---|
| 2 | ተማሪዎች አንድን ነገር ተመልክተው ወይም አጥንተው ሀሳብ በማሰባሰብ ጽፈው እንዲያቀርቡ ያዛሉ? | | | |
| 4 | የጽህፈትን ትምህት የሚያስተምሩ አብዛኛው ጊዜ<br>ሀ. ሂደት ላይ በማተኮር<br>ለ. ውጤት ተኮር ላይ በማተኮር | | | |
| 5 | ተማሪዎች ፅሀፈት በሚጽፉበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለተማሪዎች ይጠቁማሉ? | | | |
| 6 | በፅሀፈት ትምህርት ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ስለሚጽፉበት ርዕስ ፤ይዘት፡ አላማና ተደራሲ ወስነው ይናገራሉ? | | | |
| 7 | ተማሪዎች ፅሀፈትን ሲጽፉ የሚፈጽሙትን ስህተት እራሳቸው እንዲያርሙ ያለማምዷቸዋል? | | | |
| 8 | ተማሪዎች ፅሀፈትን ሲጽፉ የሚፈጽሙትን ስህተት እራሳቸው እንዲያርሙ ያለማምዷቸዋል | | | |
| 9 | ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድ ተነስተው የሚጽፉበትን ርዕስ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እንዲፈልጉ ያበረታታሉ? | | | |
| 10 | ተማሪዎች ድርሰትን ሲጽፉ ስራው የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ያሳውቃሉ? | | | |
| 11 | የፅህፈት ህጎችን የአጻጻፍ ስልቶችን ያስተምራሉ? | | | |
| 12 | የአጻጻፍ ሂደትን (የማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስና ማቃናት) ተግባራትን ያስተምራሉ? | | | |
| 13 | ድርሰትን ሲያስተምሩ በሰዋሰው ትክክለኝነትን ላይ ያተኩራሉ? | | | |
| 14 | ድርሰትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች አካላዊና ስነልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያበረታታሉ? | | | |
| 15 | በፅህፈት ትምህርት ሂደት በአብዛኛው የተማሪዎችን ስህተት የማቃናት እና በማረም ላይ ያተኩራ? | | | |
| 16 | በትምህርቱ ሂደት የአጨራረስ ሂደትን ያስተምራሉ? | | | |

**ክፍል ሦስት**

በክፍል ሦስት ደረጃ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ደግሞ ክፍት ሆነው አጭርና ግልጽ መልሶች የሚፈልጉ ናቸው ። ለእነዚህ ጥያቄዎች ያለዎትን ሀሳብ ያለ ገደብ በነጻነት ከመዘርዘር እንዳይቆጠቡ አደራዬ የጠበቀ ነው ።

ከዚህ በታች ለቀረቡት ክፍት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ ።

1. ፅህፈትን ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለማስተማር የትኛው የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ተመራጭ ነው? ካለዎት ልምድ አኳያ ያብራሩ፡

   ______________________________________________

   ________________________________________

2. ለአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ሲሰለጥኑ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ለማስተማር የሚያስችል በቂ ስልጠና ስለማግኘትዎ ምን ያህል ይስማማሉ?
3. እርስዎ በሰለጠኑበት ተቋም የጽህፈት ክሂልን ለማስተማር የተሰጥዎትን ስልጠና በቂ ነው?

## አባሪ ሸ

## ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የድርሰት ትምህርት አቀራረብ ተግባራዊነት ለመፈተሸ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በማስከተል በዝርዝር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ ስራ እገዛህ/ሽ እንዳይለየኝ በአክብሮትና በትህትና አደራ እላለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ውድ ጊዜህን/ሽን መስዋእት በማድረግ ይህንን መጠይቅ ለመሙላት ስለተባበሩኝ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬ ይድረስዎ፡፡

- ማሳሰቢያ
- መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም
- አጠቃላይ መመሪያ

**ክፍል አንድ**

1. ጾታ
2. ዕድሜ
3. የትምህርት ቤቱ ስም
4. የትምህርት ደረጃ

**ክፍል ሁለት፡-** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ሦስት አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል ፡፡ እናንተ የምትስማሙበትን አማራጭ መልስ በተሰጠው የመልስ መስጫ ሰንጠረዥ (X) ምልክት በማኖር የመረጣችሁትን ምርጫ አመልክቱ ፡፡

| ተራ. ቁ | ጥያቄዎች | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የጽህፈትመልመጃዎችንበግል፣በጋራ፣ በቡድን እንድትጽፉ አዘጋጅተዉ ያቀርባሉ? | | | |
| 2. | መምህራችሁ በክፍል ዉስጥ ጽህፈትን እንድትለማመዱ በሚያስተምራችሁ ጊዜ የማስተማሪያዉ ዘዴ የመጻፍ ክሂላችዉን | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አሻሽሏል፡፡ | | | |
| 3. | መምህራችሁ በግል፣በቡድንና በቢጤ ዉይይት ተጠቅማችሁ የጽህፈት ክሂላችሁን ለማዳበር የምትችሉበትን አመቻችተዉ በማስተማራቸዉ የመጻፍ ችሎታችሁን አዳብሮላችዋል? | | | |
| 4 | አንድን ጽሁፍ ከማርቀቃችሁ በፊት ቢጋር እንድትዘጋጁ ይነግራችዋል? | | | |
| 5 | መምህራችሁ በጽህፈት ትምህርት ሂደት በራሳችሁ የመለማመድ ልምድ እንድኖራችሁ ያግዛችኋል? | | | |
| 6 | መምህራችሁ በጽህፈት ትምህርት የጽህፈት ህጎችና ልምዶችን የጽሁፍ መርሆችን ያስተምራችኋል? | | | |
| 7. | በጽህፈት ትምህርት ስለምትጽፉበት ርዕስ ፣ዓላማ፣ቅርጽ ራሳችሁ እንድትወስኑ እድሉን ይሰጣችዋል? | | | |
| 8. | በጽህፈት ትምህርት ሂደት የማሰላሰል ደረጃ ፣የማርቀቅ ደረጃ፣የመከለስ ደረጃ ተግባራትን እንድታከናዉኑ ያዛችዋል? | | | |
| 9. | ጽህፈት ከመጻፋችሁ በፊት የአጨራረስ ሂደትን ያስተማራችዋል? | | | |
| 10. | ጽህፈት ስትጽፉ የምትጨርሱበትን ጊዜ ወስነዉ ይነግሮችዋል? | | | |
| 11. | ጽህፈትን ስትማሩ የጻፋችዉትን ጽሁፍ እንደገና ደጋግማችዉ እንደትከልሱ ያበረታቷችዋል? | | | |
| 12. | በጽህፈት ሂደት በቃላት ምርጫ፣ያቀራራብ ስልት፣የቋንቋ አጠቃቀም፣ሥርዓተ ነጥቦችን ደጋግማችዉ በማየት | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እንድታርሙ ያዛችዋል? | | | |
| 13. | መምህራችሁ ለመጻፍ በመረጣችሁት ርዕስ ላይ ከቢጤዎቻችዉ ጋር የሃሳብ ልዉዉጥ እንድታደርጉ ያዛሉ፣ያበረታታሉ፣ ጽሁፋችዉን እንድታስተካክሉ ይረዳችዋል? | | | |
| 14. | መምህራችሁ ሰዉ ጠይቃችዉ ወይም ጥናት አድርጋችዉ ሃሳብ በማሰባሰብ እንድትጽፉ ያዛሉ? | | | |
| 15፣ | በጽህፈት ትምህርታችዉ ጽህፈት ከመጻፋችዉ በፊት እንድታሰላስሉ ያበረታቷችዋል | | | |
| 16. | መምህራችዉ በክፍል ዉስጥና ከክፍል ዉጭ የጽህፈት ልምምድ እንድታደርጉ በቂ መልመጃዎችን አዘጋጅተዉ ይሰጣሉ | | | |
| 17. | መምህራችዉ ሲያስተምሩ የተለያዩ የጽህፈት ስራዎችን ከቀላል ወደ ከባድ ለማሸጋገር ደረጃ በደረጃ እንድታሻሽሉ የሚያግዙ ስለመሆናቸዉ ትስማማላችዉ? | | | |
| 18. | በክፍል ዉስጥ ስለምትጠይቁት የጽህፈት አጻጻፍ ሂደት መምህራን ለጥያቄዎች ተገቢና ግልጽ ምላሽ ይሰጣሉ? | | | |